አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን
ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባባቸውን በደረጃው ሚጠበቀባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? በሊቦ ከምከም ወረዳ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት

በ
ገደማዊት አማረ

2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሃሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? በሊቦ ከምከም ወረዳ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት

በ

ሃይማኖት አማረ

2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሃሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? በሊቦ ከምከም ወረዳ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለ በተግባራዊ ስነ ልሣን አማርኛን ለማስተማር ኤም·ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ሃይማኖት አማረ

2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሃሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? በሊቦ ከምከም ወረዳ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት

በ

ሃይማኖት አማረ

2005 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም ______ ፊርማ ______

ፈታኝ ስም ______ ፊርማ ______

______ ______

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
LIBRARY
ADDIS ABABA

# ምስጋና

በመጀመሪያ ሁሉ ነገር በጊዜው እንዲፈጸም ለሚያደርግ ለልዑል እግዚአብሔር ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ምስጋና ይገባዋል።

ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ እንዴት መስራት እንዳለብኝ አቅጣጫን በማመልከት፤ የጥናቱን ረቂቅ በማረምና ገንቢ አስተያየት በመስጠት ጥናቱ አሁን ያለውን ቅርጽ እንዲይዝና በወቅቱ እንዲከናወን በማበረታታት ለፍፃሜ እንዲደርስ እገዛ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ለአቶ ደረጀ ገብሬ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ በለቦ ከምከም ወረዳ የሚገኙ የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን፣ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምራህራንና ተማሪዎችን አመሰግናለሁ።

በትምህርት ቤት ቆይታዬ ከጎኔ ሆነው አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ለጥናቱ መሳካት የበኩላቸውን ድርሻ ላበረከቱት ለአባቴ ለአቶ አማረ ኪዳኑ እንዲሁም ለጓደኞቼ ለመምህር ከንድዬ ተመስገንና ለቀኑ ጌጡ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

በመጨረሻም ጥናታዊ ጽሑፉን በኮምፒውተር በመተየብ ከትዕግስትና ከመልካም ስነ ምግባር ጋር ላጠናቀቀችልኝ ለፍሬሕይወት ምስጋናዬ ከልብ ነው።

# ማውጫ

ይዘት                                                   ገጽ


ምስጋና ............................................................................................................... i

ማውጫ ................................................................................................................. ii

የሠንጠረዥ ማውጫ ................................................................................................. vi

የአባሪ ማውጫ ..................................................................................................... vii

አጠቃሎ ................................................................................................................ viii

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ................................................................................................................ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................................................................................ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ................................................................................... 4

1.3. የጥናቱ ዓላማ ................................................................................................... 5

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ .............................................................................................. 6

1.5 የጥናቱ ወሰን ...................................................................................................... 7

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት ....................................................................................................... 8

2.1 የጽሕፈት ትምህርት እሳቤ ................................................................................... 8

2.1.1 ጽሕፈት ምንድን ነው? ...................................................................................... 8

2.1.2 የጽሕፈት ትምህርት አላማ .................................................................................. 9

2.1.3 የጽሕፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉ ተላውጦዎች ........................................ 12

2.1.3.1 ሥነ-ልቦናዊ ባሕርይ ........................................................................................ 13

2.1.3.2 ሥነ-ልሳናዊ ባሕርይ ........................................................................................ 13

2.1.3.3 አእምሮታዊ ባሕርይ ........................................................................................ 14

2.2 የጽሕፈት ትምህርት እርማት አሰጣጥ መንገዶች ..................................................... 14

2.2.1 በመምህር የሚደረግ እርማት..........14

2.2.2 በብጤ የሚደረግ እርማት..........16

2.2.3 በራስ የሚደረግ እርማት..........16

2.3 ስህተትን የማስተማሪያ ስልቶች..........17

2.4 ሐሳብን /ስሜትን/ በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ መመዘኛዎች..........19

2.4.1 የቋንቋ አጠቃቀም..........19

2.4.2 መደበኛ ቃላት..........20

2.4.3 የቋንቋ አወቃቀር..........21

2.4.4 የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም..........21

2.4.5 ተነባቢነት..........22

2.5 ጽሑፋዊ ተግባቦትን የሚያውኩ የቃላት አጠቃቀም መልኮች..........24

2.5.1 የቃላትና ሐረጋት ድግግሞሽና ድረታ..........25

2.5.2 የተሰለቹ ቃላትና አገላለጾች..........25

2.5.3 የተውሶ ቃላት..........26

2.6 አንቀጽ..........26

2.6.1 የአንቀጽ ባሕርያት..........27

2.6.1.1 የአንቀጽ አንድነት..........27

2.6.1.2 የአንቀጽ ቅንብር (ጉልህነት)..........28

2.6.1.3 የአንቀጽ ውህደት(ግጥምጥምነት)..........29

2.7 ስነዶች..........30

2.7.1 የመማር አጥጋቢ ብቃት..........30

2.7.2 ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጀው መርሐ-ትምህርት ..............................31

2.7.3 የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት..........................................32

2.8 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት..............................................................33

ምዕራፍ ሦስት

የአጠናን ዘዴ.........................................................................................35

3.1 የናሙና አመራረጥ.....................................................................35

3.1.1.የጥናቱ አካባቢ አመራረጥ..............................................35

3.1.2.የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ...................................35

3.1.3.የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ......................................36

3.1.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ......................................36

3.1.5 .የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ .......................................36

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች...........................................37

3.2.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና ..........................................37

3.2.2 ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ .................................38

3.3 የመረጃ አተናተን ......................................................................39

ምዕራፍ አራት

የመረጃዎች ትንተናና ውጤት ..................................................................40

4.1 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና...................................40

4.2 ከተማሪዎች የችሎታ መለኪያ ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና......................52

4.2.1 አንቀጽ..............................................................................52

4.2.1.1 የንጥብ አሰጣጥና የውጤት አቀራረብ ስልት........................52

4.2.1.2 የፊደል ግድፈት ፣ የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ

የሚታይባቸው አንቀጾች ትንተና.......................................54

4.2.1.3 የቅንብር ጉድለት የሚታይባቸው አንቀጾች ትንተና ...............66
4.2.1.4 የሐሳብ አንድነትን ያልጠበቁ አንቀጾች ትንተና........................70
4.2.1.5 የሥርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችግር የሚታይባቸው አንቀጾች ትንተና.......................................................................74
4.2.1.6 የሰዋስዋዊ አገባብ ሥህተት የሚታይባቸው አንቀጾች ትንተና......79
4.2.2 የሥርዓተ-ነጥቦች አገባብ.........................................................82

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች......................................................................84
5.1 ማጠቃለያ...................................................................................84
5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች......................................................................86
ዋቢ ምንጮች (References)....................................................................87
አባሪዎች.....................................................................................................90

## የሠንጠረዥ ማውጫ

**ገጽ**


ሠንጠረዥ አንድ፡- የናሙና ትምህርት ቤቶች፣ የመማሪያ ክፍሎችና በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎችን የሚያሳይ መረጃ ...... 37

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የመምህራን ዳራዊ መግለጫ ...... 41

ሠንጠረዥ ሦስት፡- የመማሪያ መጻሕፍቱ አቀራረብ ጽሕፈትን ለማስተማር እና የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር ያለውን ብቃት የሚያሳይ መረጃ ...... 42

ሠንጠረዥ አራት፡- ተጠኝ ተማሪዎች ጽሕፈትን ለመማርና ክሒሎን ለማዳበር ያላቸውን ፍላጎት የሚያሳይ መረጃ ...... 43

ሠንጠረዥ አምስት፡- ተጠኝ ተማሪዎቹ የሚሰጣቸውን የጽሕፈት ስራ ትኩረት ሰጥተው መስራትና እንደገና የማስተካከል ልምድን የሚያሳይ መረጃ ...... 44

ሠንጠረዥ ስድስት፡- የስምንተኛ ክፍል መምህራን ጽሕፈትን ለማስተማርና የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር የሚያደርጉት እገዛ የሚያሳይ መረጃ ...... 45

ሠንጠረዥ ሰባት፡- መምህራን ጽሕፈት ተኮር ተግባራትን ለማለማመድ የሚያደርጉትን እገዛ የሚያሳይ መረጃ ...... 47

ሠንጠረዥ ስምንት፡- ተማሪዎች አንቀጽና ዓረፍተ ነገር በሚጽፉበት ጊዜ ጎልተው የሚታዩ ስህተቶችን የሚያሳይ መረጃ ...... 48

ሠንጠረዥ ዘጠኝ፡- መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸውን የጽህፈት መልመጃዎች የአስተራረም ሁኔታና የተማሪዎቹ ስህተትን የማረም ልምድን የሚያሳይ መረጃ ...... 50

ሠንጠረዥ አስር፡- ተጠኝ ተማሪዎቹ የጻፏቸው አንቀጾች ብዛትና የአቀራረብ ስህተት አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ ...... 53

ሠንጠረዥ አስራ አንድ፡- የተጠኝ ተማሪዎች ስርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማወቅ የስርዓተ ነጥብ ማሟላት ጥያቄ (ፈተና) የተገኘው ውጤት ...... 82

## የአባሪ ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| አባሪ 1:- በመምህራን የሚመለስ የጽሑፍ መጠይቅ | 90 |
| አባሪ 2:- የተጠኝ ተማሪዎች የችሎታ መለኪያ ፈተና | 96 |
| አባሪ 3:- የተጠኝ ተማሪዎች የችሎታ መለኪያ ፈተና ውጤት | 98 |
| አባሪ 4:- የእጅ ጽሑፍ ተነባቢነት የሌላቸው አንቀጾች ማሳያ | 101 |

# አጠቃሎ

የጥናቱ ዓላማ በሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በደረጃው የሚጠበቅባቸውን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ አዳብረዋል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። ጥናቱ የተከተለው አይነታዊ ምርምር(qualitative research) ሲሆን አቀራረቡም ገላጭ ነው። በደቡብ ጎንደር ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ በሊቦ ከምከም ወረዳ የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል። በዚህ ወረዳ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥም ለትራንስፖርት ምቹ የሆኑ አራት ትምህርት ቤቶች በተራ የዕጣ ናሙና ተመርጠዋል። እነዚህም ትምህርት ቤቶች አበባዬን የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት፣ አላቦ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት፣ አዲስ ዘመን የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤትና ይፋግ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ናቸው። በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው በጥቅል ናሙና ዘዴ ተመርጠው የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል። በተመረጡት ትምህርት ቤቶችም 16 የመማሪያ ክፍሎች የሚገኙ ሲሆን የዕጣ ናሙና በመጠቀም ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የአንድ ክፍል ተማሪዎችን ከሁሉም ትምህርት ቤቶች ደግሞ የአራት ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪ በማድረግ የችሎታ መለኪያ ፈተና ተሰጥቷቸዋል። ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በስራ ላይ የዋሉት የጽሁፍ መጠይቅና የችሎታ መለኪያ ፈተና ሲሆኑ በእነዚህ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎችም ተተንትነዋል። በጥናቱ የተደረሰበት ውጤት እንደሚያሳየው ተጠኚ ተማሪዎቹ በተነባቢ የእጅ ጽሑፍ፣ ሰዋስዋዊ ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ፣ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም አንድ ሃሳብ ያለው አንቀጽ የመጻፍ ችሎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ ይጠቁማል። ከእነዚህ ውጤቶች በመነሳትም ጥቆማዎች ቀርበዋል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሃሳብን አድማስ ለማስፋት ትምህርት ያስፈልጋል። ማናቸውም ትምህርት ደግሞ በመሰረቱ የቋንቋ ትምህርት ነው። ምክንያቱም ማንም ሰው ቋንቋው ካልገባው የትምህርቱን ፍሬ ሃሳብ ለመጨበጥ ስለማይችል ነው። የቋንቋ ችሎታ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመልመድ ወይም በመማር የምናገኘው ነው።

ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች አንዱ የተማሪዎቹን የጽሕፈት ችሎታ ማዳበር ነው። በስርዓት የተዋቀረና ሙሉ መልዕክት ያዘለ ጽሑፍንም ሆነ አረፍተ-ነገርን ለመጻፍ ጸሐፊው የጽሕፈት ክሂል ሊኖረው ይገባል። እንዲህ አይነት እውቀት ደግሞ ሊገኝ የሚችለው እንደ ማዳመጥና መናገር ከማህበረሰቡ ሳይሆን ከትምህርት ቤት ወይም ከአስተማሪው ነው። ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድም ከዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ጀምሮ ጽሕፈት ተኮር ትምህርት እንደሚሰጥ ይታወቃል።

ጽሕፈት በማዳመጥ ወይም በማንበብ የተገኘን ነገር በማስታወሻ መልክ ለመጻፊያነት አመቺ በሆነ ነገር ላይ ማስፈር ወይም በጽሑፍ የቀረበን ነገር መገልበጥ፣ ሆሄያቱንና ሆሄያቱ የወከላቸውን ድምጾች የመለየትና የማዛመድ ችሎታን ይጠይቃል። ማንኛውም አካሉና አእምሮ ጤነኛ የሆነ ሰው መደበኛ ባልሆነ መንገድ በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ በመልመድ ሊናገር ይችላል። ነገር ግን ሁሉም ሰው በቋንቋው እንዴት መጻፍ እንዳለበት ለማወቅ የግድ መማር ይኖርበታ (Rievers 1981፣ 291-94)።

እንደ Celce-Murcia (1991:236) አገላለጽም ተማሪዎች የፊደልን ቅርጽ በመለየት ቃላትን መስርተው፣ የቃላትን ምርጫና አጠቃቀም በማወቅ ሃሳባቸውን በተገቢ ቃላትና ዓረፍተ-ነገሮች ማስተሳሰር የሚችሉበትን የተግባቦት ስርዓት እንዲያውቁ ጽሕፈትን ማስተማር ያስፈልጋል።

Byren (1988:23) ደግሞ ንግግርን ያለምንም ትምህርት ልንለምድ እንችላለን፣ በጽሕፈት ግን ከብዙ ልምምድ በኋላም ቢሆን ዝቅተኛ ችሎታ ብቻ ሳይሆን የሚኖረን ዝቅተኛ አጠቃቀም

ጭምር ነው። ስለዚህም ጽሕፈትን ለመልመድ አስቸጋሪና አገልግሎቱም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ክሒል በመሆኑ ጽሕፈትን መማር ማስተማር እንደሚገባን ይገልጻሉ።

ጽሕፈትን ከሁል ጊዜውም በበለጠ ሁኔታ መማርና ጥሩ አድርጎ መጻፍ መቻል ተፈላጊ ክሒል መሆኑን Kelly and Deborah፣(1998፡ 2) ሲገልጹ በአለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች መረጃ የሚለዋወጡት፣ የሚግባቡት ወዘተ በጽሕፈት እንደሆነ፤ በዚህ ክሒል ደግሞ መልዕክትን ግልጽ ለማድረግ ጥሩ የጽሕፈት ክሒል ሊኖረን እንደሚገባ ያስረዳሉ።

አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ለመግባባት በሚጽፍበት ጊዜ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ ሀሳቦችን ማቀናበርና ትክክለኛ አገባቡን ጠብቆ ማስፈር መቻል አለበት። ይህን ካደረገ ደግሞ ውጤታማ ተግባቦትን ይፈጥራል። ውጤታማ ጽሕፈትን ለማከናወን ደግሞ የቋንቋውን ሰዋስው፣ ፊደላትን ከነዘራቸው፣ ስርዓተ ነጥቦችንና አገባቡን ወዘተ. ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። ስርዓቱን የጠበቀና አግባብነት ያለው ጽሑፍ ከጻፍን ተግባቦቱ ቀላልና ግልጽ ይሆናል። አንባቢም መልዕክቱን በግልጽ ይረዳናል (Edwards, 1999)።

ከሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ መጻፍ በጣም አስቸጋሪና ውስብስብ፣ ብዙ ልምምድን የሚጠይቅ ክሒል ነው። በአእምሮ ያሰቡትን ነገር ስርዓት አስይዞ እና ለአንባቢዎች ግልጽ ሆኖ እንዲነበብ አድርጎ መጻፍ ከፍተኛ ዝግጅትን ይጠይቃል። አንድን ነገር ለወደፊት ትውልድ ሳይረሳ እንዲተላለፍ ለማድረግ ጽሕፈት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ጽሕፈት በተጓዳኝ መልኩ አንድናነብ ስለሚያደርገን የማንበብ ክሂላችን እንድናዳብር ይረዳናል። የተማሪዎች የጽሕፈት ክሒል ዝቅተኛ መሆን ደግሞ ከዝቅተኛ የክፍል ደረጃ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ድረስ በውጤትም ሆነ ባላቸው የእውቀት ችሎታ ላይ ችግር ሲፈጥር ይታያል። ይህንን በተመለከተም ደረጀ (2007፣2) ባቀረቡት ናሙናዊ ጥናት፡-

> ... ፊልገውም ሆነ ተገድደው ወደ ትምህርቱ ክፍሉ የሚመጡ ተማሪዎች ከአማካይ በላይ የሚሆኑት መነሻውንና መድረሻውን ያገናዘበ አንድ ወጥና ግልጽ ሃሳብ የያዘ ዓረፍተ-ነገር ለማዋቀር ሲቸገሩ አይቻለሁ። ካጋጠሙኝ ተማሪዎች እኩሌታ ግምት የሚሰጣቸው ወግ ያለው አንድ አንቀጽ አቀናብረው መጻፍ ሲሳናቸው ማየት የዘወትር እውነታ መሆኑን አስተውያለሁ። አሁን በተለይ ከሶስት ዓመታት ወዲህ፣ በአንድ ክፍል ከሚያጋጥሙኝ ተማሪዎች ውስጥ ሩብ ያህሉ ዘወትር የምንጠቀምባቸውን የአማርኛ ፊደሉች ከነዘርዝር ቅርጻቸው ሳይሆን መነሻቸውን (በተለምዶ ሀ ግዕዝ፣ ለግዕዝ ወዘተ. የሚባሉትን) ለይተው መጻፍ ሲቸገሩ ልብ ብያለሁ።

በማለት ገልጸዋል።ጥሩ ጽሑፍ ለመጻፍ ቃላትን በወረቀት ላይ ማስፈር ብቻ በቂ አይደለም። የሚደረደሩት ቃላት ለአንባቢ ስሜት በሚሰጥ መልኩ መደራጀት አለባቸው። ቃላትን ስርዓት

ባለው መልኩና ትርጉም እንዲይዙ አድርጎ ለመጻፍ ሰዋስዋዊ ስርዓትና ስርዓተ-ነጥቦችን አሟልቶ መጻፍ ያስፈልጋል። ይህም የቃላትን ጥርቅም ትርጉም እንዲኖረውና አንባቢ በቀላሉ እንዲረዳው ያስችላል።

የመጀመሪያ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃ እና የዩኒቨርሲቲ መምህራን ፈተናዎችን በሚያርሙበት ወቅት የተማሪዎችን ችግር ከመግለጽ ይልቅ ውጤት የመቀነስ አዝማሚያ ይታይባቸዋል። ተማሪዎቹም ትክክል አለመሆናቸውን እንጅ ትክክለኛው አጻጻፍ ምን አይነት እንደሆነ ሳያውቁት ያልፋሉ። በአጠቃላይ ተማሪዎች በክፍል ስራ ጊዜም ሆነ በፈተና ስህተታቸውን በግልጽ ስለማይነገሩ እና እንዴት ማሻሻል እንዳለባቸው ስለማያውቁ የችግሩ አሳሳቢነት ወደ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሲደርሱም አብሮ መዝለቁ የማይቀር ጉዳይ ነው (Herrero, 2007) ።

የተማሪዎች የጽሕፈት ክሒል ችግር በተለያየ ምክንያት ሊመጣ ይችላል። እነዚህም ችግሮች በመንስኤ፣ በአይነት፣ በመጠንና ችግሩን ለማስተካከል በሚወስደው ጊዜ ይወሰናሉ። አንዳንድ ተማሪዎች ከቋንቋ ውሱንነት የተነሳ ሐሳባቸውን የመግለጽ ችግር ሲገጥማቸው ሌሎቹ ደግሞ ቃላትን አዋቅሮ የመጻፍ፣ ተነባቢ የእጅ ጽሑፍ ፣ የስርዓተ ነጥብና የሰዋስዋዊ ስርአት አጠቃቀም ችግር ይታይባቸዋል። ተማሪዎች የጽሕፈት ክሒላቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ እንዴት ማቀድ ፣ መጻፍ እና ማስተካከል እንዳለባቸው መረዳት አስፈላጊ ነው (Edwarrds, 1999)።

እንደሚታወቀው አብዛኛው የስራ ዘርፍ የጽሕፈት ክሒልን የሚጠይቅ ነው። የግልም ሆነ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተቀጣሪዎቻቸው ጥሩ የጽሕፈት ችሎታ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ። ሁሉም መስሪያ ቤቶች ወርሃዊ አሊያም ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባሉ። ይህን ለማዘጋጀት ደግሞ ሪፖርት በስርዓት አቀናብሮ ጽፎ የሚያቀርብ ሰው ያስፈልጋል። ይህን የሰው ሐይል ለማፍራት ደግሞ ከታችኛው የትምህርት እርከን ጀምሮ ተማሪዎች በጽሕፈት ክሒላቸው የበቁ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።

በቅርብ ጊዜ የወጡ ዘገባዎች እንደሚገልጹት አብዛኞቹ የግልና የመንግስት ቀጣሪዎች የጽሕፈት ክሒልን እንደ ዋና መመልመያ እየተጠቀሙበትና የስራ እድገት ለማግኘትም እንደዋና መስፈርት እያዩት መጥተዋል። ለምሳሌ፡ በአሜሪካን ሐገር ውስጥ የተካሄደ አንድ ጥናት እንዳመለከተው በ4ኛ፣ በ8ኛ እና በ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በተካሄደ የጽሕፈት ክሒል መመዘኛ ፈተና ከጠቅላላው ተፈታኞች ውስጥ ከ22 - 26% የሚሆኑት ተማሪዎች ብቻ

አጥጋቢ ውጤት ሲያመጡ አብዛኞቹ ግን ዝቅተኛ የጽሕፈት ክሒል እንዳላቸው አሳይቷል። በአጠቃላይ ሲታይም 72% የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ 69% የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች እና 77% የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሕፈት ክሒል መመዘኛ መስፈርትን ሳያሟሉ ቀርተዋል (perskey, 2003)።

ይህ ጥናት እንደሚያሳያው በርካታ ተማሪዎች በጽሕፈት ክሒላቸው ደካማ እንደሆኑና ይህም አፋጣኝ የሆነ የማብቃት ስራ መስራት እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

ጽሕፈት ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ሲነጻጸርም አስቸጋሪ ሆኖ ይታያል። ይህም ማለት በጽሕፈት ጊዜ ጽንሰ ሐሳቡን ከማሰብ ጀምሮ፣ በወረቀት ማስፈር፣ እንደገና የሃሳብ ቅደም ተከተሉን አስተካክሎ መጻፍ፣ ሰዋስዋዊ ስርዓቱን ጠብቆና ስርዓተ ነጥቦችን አሟልቶ መጻፍን ይጠይቃል። በዚህም ምክንያት ብዙ ተማሪዎች ከሌሎች ክሒሎች ይልቅ ሐሳብን በጽሑፍ የማቅረብ ችግር ሲገጥማቸው ይታያል። ደረጀ (2007፣3) ችግሩ ከትምህርት ቤት አልፎ በተለያዩ የሙያ መስኮች ላይም እየተንጸባረቀ መሆኑን ሲገልጹ "ችግሩ ከትምህርት ቤት አልፎም በየእለቱ በሚያጋጥሙን ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና መጻሕፍትም ውስጥ በጉልህ እየታየ ነው" ብለዋል።

የጽሕፈት ክሒል ለስራ ማመልከቻ ከመጻፍ ጀምሮ ለተለያዩ ጉዳዮች የሚሰጠው ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው። በጥናታዊ ጽሑፍ ዙሪያ ብንመለከት አንድ አጥኚ ጽሑፉ በአማካሪውና በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ግልጽና ማራኪ እንዲሁም ሰዋስዋዊ ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ እና መልዕክቱ አንባቢያንን በማያሻማ መንገድ መጻፍ አለበት።ይህ ካልሆነ ግን አንባቢ መልዕክቱን ሳይረዳ ይቀርና ስራው ውድቅ ይሆናል ማለት ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የጽሕፈት ክሒልን በተመለከተ በተለያዩ ዘመናት ጥናቶች ተካሒደዋል። ጥናቶቹም የተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ችሎታ የሚገኝበትን ገጽታ ከተለያዩ አቅጣጫ የመረመሩ ናቸው። እነዚህም፡ ከክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ምልከታ፣ከመምህራን የማስተማር ዘዴና አቀራረብ፣ ከመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ይዘትና ቅንብር፣ከተማሪዎች የመማር ፍላጎትና ለቋንቋው ካላቸው አመለካከት እና ተማሪዎች ከሚጽፉት ድርሰትና የስህተት ምንጮች አርማት

አንጻር የተጠኑ ናቸው (ደረጀ 2007)። እነዚህ ጥናቶችም ትኩረታቸው በሁለተኛ ደረጃና በኮሌጅ ተማሪዎች ላይ ነው ።

ይሁን እንጅ ደረጀ (2007) ላይ በመጀመሪያ ደረጃ በመጀመሪያው እርከን (4ኛ) ክፍል ላይ ካቀረቡት ናሙናዊ ጥናት በስተቀር በዚህ አይነት ርዕስ የተጠና ጥናት አላጋጠመኝም። ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱን በማካሂድበት አካባቢ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ የተካሄደ ጥናት ባለመኖሩ ጥናቱን ለማጥናት አነሳሳኝ።

የአንድ ሰው የጽሕፈት ክሂል መሰረት መያዝ የሚጀምረውም ከታችኛው የትምህርት እርከን ነው። አንድ ሰው ትምህርት ቤት ሲገባ የሆሄያትን ቅርፅና ዘሮች መለየት ይጀምራል። እየቆየም ቀስ በቀስ ባለ ሁለት እና ሦስት ሆሄ ቃላትን መጻፍ ይጀምራል (perskey, 2003) ።

ተማሪዎች ጥሩ ጸሐፊ እንዲሆኑ ብዙ መጻፍ አለባቸው። አንድ ጸሀፊም አንድ ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን የመግባቢያ መሳሪዎች በሙሉ መጠቀም ስለማይችል ጽሕፈትን ማስተማር ያስፈልጋል። ከማስተማር ባሻገርም ተማሪዎች የደረሱበትን ደረጃ ገምግሞ አስተያየት መስጠት ተገቢ ነው (Hedge 1988 ፣145) ።

በዚህም የጽሕፈት ክሂል መሰረት መያዝ ከሚጀምርበት ከታችኛው እርከን በመነሳት በመጀመሪያው ደረጃ ሁለተኛው እርከን የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት በ8ኛ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ላይ ጥናቱን አካሂጀበታለሁ።

### 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በደረጃው የሚጠበቅባቸውን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ አዳብረዋል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። ይህን አጠቃላይ አላማ መሰረት በማድረግም ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት። እነዚህም፤

ሀ ተማሪዎች የፊደል ቅርጽን በወጉ ጠብቀው በተነባቢ የእጅ ጽሑፍ ሃሳባቸውን ማቅረብ አለማቅረባቸውን መፈተሽ፤

ለ በሚጽፏቸው ጽሑፎች ውስጥ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ማወቅ፤

ሐ. በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን አንቀጽ መጻፍ አለመጻፋቸውን መለየት፤

መ. ስዋስዋዊ ስርዓቱንና የሃሳብ ቅደም ተከተልን አስተካክለው መጻፍ አለመጻፋቸውን መለየት

ሠ. ለተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሒል መዳበር ወይም ዝቅተኛ መሆን መንስኤ የሆኑ ምክንያቶችን ማወቅ የሚሉት የዚህ ጥናት ዝርዝር አላማዎች ናቸው ።

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት አብይ አላማ በሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በደረጃው የሚጠበቅባቸውን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ አዳብረዋል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው ።በመሆኑም ይህ ጥናት ከሚከተሉት ነጥቦች አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነው፤

- በዚህ ጥናት ላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ እና ዝርዝር አላማዎች መሠረት በማድረግ ተጠኝ ተማሪዎች በሚገኙበት የክፍል ደረጃ ላይ ያላቸውን የጽሕፈት ክሒል ብቃት መኖር አለመኖራቸውን ለማወቅ ያስችላል፤
- የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ያሉበትን የጽሕፈት ክሒል ደረጃ ስለሚያሳይ ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራን የመማር-ማስተማር ስልትን ለመቀየስ ያስችላል፤
- የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችና መምህራን ለጽሕፈት ክሒል ትምህርት ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል፤
- የመማሪያ መጽሐፍ፤ መርሐ-ትምህርትና ማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የጽሕፈት ክሒል ያለውን ሚና ተገንዝበው በመልመጃ ዝግጅት ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል፤
- ለጽሕፈት ክሒልም ሆነ ሌሎች ጥናቶችን ለሚያካሂድ አጥኝ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ጥናት እንዲያካሂድ ያነሳሳል ተብሎ ይታሰባል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን በ2005 ዓ.ም. በደቡብ ጐንደር ዞን ሊቦ ከምከም ወረዳ ካሉት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው። ይህ ጥናት ከቋንቋ ክሒሎች ውስጥ የጽሕፈት ክሒልን ብቻ የሚመለከት ነው። ከዚህ ውጭ ያሉትን ተማሪዎችም ሆነ የቋንቋ ክሂሎች አይመለከትም። ምክንያቱም ከጊዜ እና ከገንዘብ እጥረት አኳያ ሁሉንም ማካተት ስለማይቻል ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የጽሕፈት ትምህርት እሳቤ

### 2.1.1. ጽሕፈት ምንድን ነው?

ጽሕፈት ከንግግር ዘግየት ብሎ የመጣ በሰው ልጅ የስልጣኔ እድገት የተገኘ የንግግር ወኪል ነው፡፡ ሰው የድምፅ ምልክቶችን በፊደል በመወከል ሃሳቡን የሚገልፅበት መሳሪያው ነው፡፡ ጽሕፈት የቃላት አጠቃቀምን፣ የሃሳብ ጥልቀትን የሚጠይቅና ምርመራዊ ይዘት ያለው ስሜትን በሚገነባ ሁኔታ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ጽሕፈት በእይታዊ (Visual) ትዕምርቶች (Symbols) ውክልና በመገልገል ሰዎች ሃሳብ የሚለዋወጡበትና ተራክቦ የሚመሰርቱበት ተግባቦታዊ መሳሪያ ነው፡፡ በመተሳሰሪያ ስልቱ ዕይታዊ፣ በአካላዊ ትግበራው አፍላቂ (Productive) በተግባቦታዊ ባሕሪውም ርቱዕ (Active) ክሒል ነው (Harmer፣ 1991)፡፡

ጽሕፈት አዲስ ግኝትን፣ ሃሳብን፣ እውቀትን ወዘተ. የመሳሰሉትን በፊደል መልእክትን ለማስተላለፍ፡ የምንጠቀምበት የቋንቋ ወኪል ነው ፡፡ Byren (1988፣ 147) ስለ ጽሕፈት ሲገልጹ አንድ አይነት ድምጾችን እንዲወክል በማድረግ የቋንቋው ህግና ስርዓት በሚፈቅደው መሰረት ሃሳባችንን በምልክት ወክለን የምናስተላልፍበትና አንባቢዎች ጽሑፉን አንብበው አንዳች መልዕክት የሚያገኙበት ነው፡፡ ስርዓታቸውን የጠበቁና እርስ በርሳቸው ትስስር ያላቸውን ነገሮች ለማፍለቅ የሚያገለግል ክሒል ጽሕፈት ይባላል፡፡ በዚህም የጽሕፈት ክሒል አፍላቂ ክሒል ይባላል ይላሉ፡፡

Nunan (1989፣ 36)፣ Rivers (1981፣ 291 - 94) ስለጽሕፈት ምንነት ጽሕፈት በማዳመጥ ወይም በማንበብ የተገኘን ነገር በማስታወሻ መልክ ለመጻፊያነት አመቺ በሆነ ነገር ላይ ማስፈር ወይም በጽሑፍ የቀረበን ነገር መገልበጥ ነው፡፡ በዚህም ሆሄያቱንና ሆሄያቱ የወከላቸውን ድምጾች የመለየትና የማዛመድ ችሎታን ይጠይቃል፡፡ ጽሕፈት በመደበኛ አውድ ውስጥ የሚዳብር ነው፡፡ ማንኛውም አካሉና አእምሮው ጤነኛ የሆነ ሰው መደበኛ ባልሆነ መንገድ በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ በመልመድ ሊናገር ይችላል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሰው በቋንቋው እንዴት መጻፍ እንዳለበት ለማወቅ የግድ መማር ይኖርበታል በማለት ይገልፃሉ፡፡

በሌላ በኩል Raimes (1983፣14) ጽሕፈት በርካታ ነገሮችን ከግንዛቤ በማስገባት እንደሚከወን ይገልፃሉ። በተጨማሪም ጽሕፈት ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁና እርስ በርስ ቁርኝት ያላቸው አረፍተ ነገሮችን በማመንጨት ሃሳብን በጽሑፍ መግለፅ የሚያስችል ክሒል ነው ይላሉ።

Widdowson (1978፣61) ጽሕፈት ዓረፍተ-ነገሮችን እንደባቡር ፍርጎዎች ቀጣጥሎ ከመደርደር የበለጠ ያለፈውን ለመመርመር ቀጣዩ በብቃት የሚገለጽበትን ዘዴ ለማሰብ ረጅም ጊዜ የሚባክንበት ተግባር መሆኑን ይገልጻሉ።

ጽሕፈት ለንግግር ድምጾች በተወከሉ ምልክቶች አማካኝነት ሃሳብን በወረቀት ላይ ለመግለጽ በማስቻሉ ለተማረ ሰው እንደ አንድ ምልክት የሚቆጠር ሰው ሰራሽ መገልገያ ነው። ክሒሉን በማስተማር የማዳበር ተግባር የሚመለከተውም ትምህርት ቤትን በቻ ነው (Raimes 1983)።

ከላይ የቀረቡትን ሃሳቦች መሰረት አድርገን የጽሕፈትን ምንነት ስንመለከት ጽሕፈት በማንኛውም ለመጻፊያነት አመቺ በሆነ ነገር ላይ በምልክቶች አማካኝነት ድምጾችን በመወከል በየደረጃው በቃላት፣ በዓረፍተ-ነገሮች፣ በአንቀጽ ወዘተ. የቀረበ ሰዎች ለመግባቢያነት የሚጠቀሙበት አእምሮአዊና ተግባቦታዊ ክሒልን ማበልፀጊያና መሰረት ያደረገ ጥበብ ነው ማለት ይቻላል።

### 2.1.2 የጽሕፈት ትምህርት ዓላማ

የጽሑፍ ተግባቦት ለማካሄድና ሃሳቡን በትክክል ለመግለፅ ጽሕፈትን መማርና ክሒሉን ማዳበር አስፈላጊ መሆኑ አያከራክርም። ለተግባቦት የሚያበቁ የጽሕፈት ችሎታዎችን ወይም ክሒሎችን ለማዳበርም መደበኛ ትምህርትን መከታተልና ጽሕፈትን በተግባር መለማመድ ያስፈልጋል። ተማሪው የጽሕፈት ችሎታ አዳብሯል የሚባለውም የታላሚውን ቋንቋ ፊደል ቅርጽ ከመለየት አንስቶ የሚጽፍበትን አላማ፣ የሚጽፍለትን አንባቢና የሚከተለውን የአጻጻፍ ስልት ለይቶ መጻፍ እንዳለበት ጠንቅቆ ሲያውቅ ነው (ሰይድ 1993፣ 17) ።

ጽሕፈት ሰዎችን ከማግባባቱ ወይም የቦታና የጊዜ ውሱንነትን አልፎ ከመሄዱ በተጨማሪ የትምህርት መማሪያ፣ የእውቀት መቅሰሚያና የሃሳብ ማሳያ ሆኖ የማገልገል ፋይዳዎች አሉት። ጽሕፈትን የመማሩ አላማም ተማሪው የፈርጀ ብዙ አገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ ክሒሉን ማዳበር ነው (ሰይድ፣ 1993) ።

ጽሕፈትን መማር ሁለት አላማዎች አሉት። የመጀመሪያው አላማ ጽሕፈትን በግብነት በማስተማር የጽሑፍ ተግባቦታዊ ክሕሎት፣ ርቱዕነት (Fluency) እና ትክክለኛነትን (Accuracy) ማለማመድ ሲሆን ሁለተኛው አላማ ደግሞ የታላሚውን ቋንቋ ስነ-ልሳናዊ ክፍሎች ማለትም የቃላት፣ የሰዋስው ወዘተ. ችሎታ ማስተማር ነው (Raimes 1983፣3) ።

እንደ Raimes (1983፣4) ገለጻ፣ ተማሪዎች ጽሕፈትን የሚማሩባቸው አላማዎች ዓረፍተ-ነገር ከመጻፍ በዘለለ መልኩ ሊታዩ ይገባቸዋል በማለት አላማው የሚያካትታቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ይዘረዝራሉ፣

- ከአንባቢ ጋር ለመግባባት
- በዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞች የሚታዩ ክስተቶችን መዝግቦ ለማቆየት
- በቋንቋው የሚጻፉ የጽሑፍ ስራዎችን ለተማሪዎች እንግዳ እንዳይሆኑ ለማስቻል
- እውቀትን ለማዳበር፣ እና
- በቋንቋው ውስጥ ያሉ የጽሑፍ ውህድ አሃዶችን በይበልጥ በአገልግሎት ለመጠቀም የሚሉት ናቸው።

ለማዳበር ይረዳል Heaton (1991፣135) በበኩላቸው ጽሕፈትን መማር የተለያዩ የጽሕፈት ንዑሳን ክሒሎችን(ተገቢነት ያላቸው አረፍተ ነገሮች የመጻፍ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ ለግልጋሎት የማዋል፣ ተቀባይነት ያለው ሃሳብ የመምረጥ የማመንጨትና አስፋፍቶ የማቅረብ፣ ተፈላጊውን ሃሳብ ለማስተላለፍ ተገቢ የሆነ የአጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ፣ የዓረፍተ-ነገርና የአንቀጽ አወቃቀር ስርዓትን ጠብቆ የመጻፍ፣ የተለመደና መደበኛ ቋንቋን የመጠቀም ወዘተ.) ይላሉ።

Byrne (1988፣16-17) ም ጽሕፈትን የመማር ማስተማርን አላማ ከስነ ትምህርታዊ (Pedagogical) እሴቱ አኳያ ሲገልፁ የጽሑፍ ፈተናን ለመስራት፣ ሌሎች ክሒሎችን ለመማርና በንባብ የሚከናወኑ የመማሪያ እውዶችን ለመፍጠር እንደሚያገለግል ገልጸዋል። በተጨማሪም ትምህርቱ ተማሪዎችን በገሃዱ አለም ተግባቦት ለሚሰራበት የጽሑፍ ቅርፅ ግንዛቤና አገልግሎት ስለሚያዘጋጃቸው ክሒሉን ማዳበር አስፈላጊ መሆኑን አፅንኦት ይሰጡታል።

የጽሕፈት ትምህርት አላማ (Brandly 1994፣ 169) ሲገልጹ የጽሕፈት ትምህርት አላማ ከግለሰባዊና ማህበረሰዊ ጠቀሜታው አኳያም ይታያል። በዚህ መሰረት ጽሕፈትን መማር

ለግለሰቡ አመለካከቱን ለመግለጽና ለመደገፍ፣ አእምሮአዊ ተግባራትን ለማከናወንና የተጻፉ ሰነዶችን ለመመርመር፣ ለማህበረሰቡም የጽሑፍ ቋንቋ መረጃ ለመያዝ፣ የስነ-ጽሑፍ ስራዎችንና ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለማጠራቀም ያገለግላል ይላሉ ።

እነ Lee (1997፣ 73-76) የጽሕፈት ትምህርት አላማን አስመልክተው ሲገለጹ ደግሞ፣ ከሁሉም በፊት ለተማሪዎች ጽሕፈትን የምናስተምርበት ዋነኛው አላማ ተማሪዎች በስልጣኔ እየዳበረ ከመጣው የአለማችን ሁኔታ ጋር ተጣጥመው እንደሄዱ ለማድረግ ነው። የትምህርቱ አላማም ይህንን የጽሕፈት ትምህርት ከግብ ለማድረስ የሚያግዝና በማስተማር ስልቶች ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባዋል በማለት ይገልጻሉ። በተጨማሪም ይህ የጽሕፈት ትምህርት አላማ በሦስት አቅጣጫዎች ሊታይ እንደሚገባው ይገልጻሉ።

ሀ. ስዋዊ የሆኑ ፍላጐቶችን የማሟላት አላማ፡- በዚህ ውስጥ የእርስ በርስ ሃሳብን የመለዋወጥ ሁኔታዎችና ነገሮችን ማከናወን ያካትታል። ለምሳሌ፡- ለብዕር ጓደኛ ደብዳቤ መፃፍ የመሳሰሉትን ያካትታል።

ለ. እውቀት ተኮር አላማዎች፡- በዚህ ውስጥ መረጃዎችን የመተርጐም፣ የመጠቀም፣ ሃሳቦችን አስፋፍቶ የመግለጽ እና በተግባር በመጠቀም ችግሮችን የመፍታት ሁኔታዎች ይካተታሉ። ለምሳሌ፡- ሪፖርት መጻፍ

ሐ. ልምድን የሚመለከቱ አላማዎች፡- በዚህ ውስጥ እውነተኛ ለሆነና ምናባዊ ለሆኑ ልምዶች ምላሽና ማብራሪያዎችን መስጠት ይካተታል። ለምሳሌ፡- ግጥም መጻፍ የመሳሰሉትን ከዚህ ውስጥ የመደባሉ።

ከላይ ከተዘረዘሩት ምሁራን ሃሳብ የምንረዳው የጽሕፈት ክሂል ትምህርታዊ እና ስነ-ልቡናዊ የሆኑ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ሲሆን ይህን በትምህርታቸው አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት፣ የባህል ቅርሶችን ለተከታይ ትውልድ ለማቆየት፣ የህበረተሰቡን የእውቀት ክምችን ለመጭው ትውልድ ለማቆየት፣ የተለያዩ ህዝባዊና መንግስታዊ ተግባራትን ለማስተላለፍ፣ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ከቦታ ወደ ቦታ ለማስተላለፍ ያለውን ጠቀሜታ በጉልህ ያሳያሉ።

### 2.1.3 የጽሕፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉ ተላውጦዎች

ከሁሉም የቋንቋ ክሒሎች ውስጥ መጻፍ አስቸጋሪና ውስብስብ፣ ብዙ ልምምድን የሚጠይቅ ክሒል ነው። በአእምሮ ያሰቡትን ነገር ስርዓት አስይዞ እና ለአንባቢዎች ግልጽ ሆኖ እንዲነበብ አድርጎ መጻፍ ከፍተኛ ዝግጅትን ይጠይቃል (perskey,2003) ።

ጽሕፈት ባሉት ባህሪያቱ የተነሳ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊዳበር የሚችል ክሒል ባለመሆኑ የእድሜ ልክ ጉዞ ነው (Barr and Barbara፣1997) ። በዚህም መሰረት ሰፊ የልምምድ ጊዜ ስለሚያስፈልገው ጊዜ የሚወስድ ክሒል ነው ማለት ይቻላል።

የጽሕፈት ትምህርት አእምሯዊ የሆነና በተግባር የሚያከናውኑት በመሆኑ ለማስተማርም ሆነ ለመማር አስቸጋሪ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ምሁራን (Nunan 1989፣ እና Kroll 1990) ይገልፃሉ። ምሁራኑ እንደሚገልፁት አፋቸውን በቋንቋቸው ለፈቱትም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑት ተማሪዎች ጽሕፈትን መማርና ክሒሉን በብቃት ማዳበር አስቸጋሪ የሚያደርጉት በርካታ ሁኔታዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል የክሒሉ የባህሪው ውስብስብነት፣ አእምሮአዊ ተግባር መሆኑ፣ ለመጻፍ ብዙ ጊዜ መፍጀቱ፣ ጸሐፊው በአንድ ጊዜ በርካታ ሁኔታዎችን ትኩረት ሰጥቶ የሚጽፍ መሆኑ፣ ከከፍተኛ ጥረትና ድካም በኋላም ተማሪዎች አጥጋቢ ውጤት አለማስመዝገባቸው ተጠቃሾች ናቸው።

የሺው (1996፣21) "ጽሕፈት በርካታ ሰብዓዊ አገልግሎቶች አሉት። መገልገል ደግሞ የሰው ልጅ ፋንታ ነው። ታዲያ ስንጠቀምም በበቂ ጥንቃቄ መሆን አለበት። ምክንያቱም የጽሕፈት ተግባቦት በተለያዩ ችግሮች ሳቢያ እንቅፋቶች ስለሚበዙበት ከመልዕክት ተቀባዩ ይልቅ መልዕክት አፍላቂው የበለጠ ሃላፊነት አለበት"።

ከዚህ የምንረዳው በጽሕፈት መልዕክትን በምናስተላልፍበት ጊዜ ጥንቃቄና ትኩረት ሰጥተን መልዕክት ተቀባያችን ሊረዳን በሚችለው መንገድና የጽሕፈት ህግን በጠበቀ መልኩ ሃሳባችንን ማስተላለፍ አለብን። ነገር ግን ይህንን ጥንቃቄ ሳናደርግ ከቀረን እንዲተላለፍ የተፈለገው ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ሳይተላለፍ ወይም መልዕክት ተቀባያችን መልዕክቱን ሳይረዳ ይቀርና በጽሑፍ ሊተላለፍ የተፈለገው ቁም ነገር ሳይተላለፍ ሊቀር ይችላል ማለት ነው።

ከዚህ ጽሑፍ መረዳት የሚቻለውም ማንኛውም የተጻፈ ነገር ሊያግባባን እንደማይችል ነው። የማያግባባበት ምክንያት ደግሞ በጽሑፍ ሂደት ወቅት ብዙ ችግሮች መኖራቸውና የጽሑፍ መልዕክት በግድፈት ሊታወክ ይችላልና ነው።

ሌሎች ጽሕፈትን አስቸጋሪ የሚያደርጉት ባህሪያቱ ደግሞ ስነ-ልቦናዊ፣ ስነ-ልሳናዊና አእምሮአዊ ገፅታዎቹ ናቸው (Raimes 1983, Pincas 1982, Hedge 1988 Reid 1993)። እነዚህ ባህሪያቱ ከዚህ በታች በአጭሩ ቀርበዋል።

### 2.1.3.1. ሥነ-ልቦናዊ ባሕርይ

በጽሕፈት ክንውን ወቅት አንባቢን ማሰብ የማይቀር ተግባር ነው። መልዕክቱ ለአንባቢው እንዲደርሰው ለማድረግ ጸሐፊው ይጨነቃል። Hedge (1988፣5) "የጽሕፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች ቁና ቁና መተንፈሻ፤ እግራቸውን ማፋተጊያና እርሳሳቸውን ማፐኪያ የስቃይ ጊዜ ነው።" በማለት ጽሕፈት በቀላሉ የሚታይ ክሒል አለመሆኑን ይገልጻሉ።ይህም ጽሕፈት ባለው ስነ-ልቦናዊ ባህሪው ምን ያህል አስጨናቂ እንደሆነ ያስገነዝባል።

ንግግር በፊት ለፊት መስተጋብር የሚከወን የሀሳብ መግለጫ መንገድ በመሆኑ የወዲያው ምላሽ ይገኛል። ጽሕፈት ግን የግል ተግባር በመሆኑ የፊት ለፊት መስተጋብር አይኖረውም በዚህም ምክንያት የወዲያው ሞጋቤ ምላሽ የማግኘት እድል (ሁኔት) የለውም። ይህ ደግሞ ጸሐፊው ላይ ውስጣዊ መረበሽን ይፈጥራል። (Richards 1990፣ 100-101) ።

### 2.1.3.2. ሥነ-ልሳናዊ ባሕርይ

ስነ-ልሳን ቋንቋ የሚጠናበት ሳይንስ በመሆኑ የአንድ ቋንቋ ውስጣዊና ውጨዊ ገፅታ ይመረመርበታል። በጽሕፈት ክሒል ረገድም የስነ-ልሳን እውቀት አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። ምክንያቱም ሃሳብን በጽሕፈት አማካኝነት አሻሚነት ሳይኖረው መግለፅ የሚቻለው የቋንቋውን መዋቅር በማጥናት በመሆኑ ነው። ተቀባይነት ያለው የሃሳብ አሰዳደር እንዲገኝ የቋንቋውን ህግጋት ማወቅ ያስፈልጋል። ስለዚህ የቋንቋን ስርዓት ከአጠቃቀሙ ጋር አስማምቶ በማቅረብ በጽሑፍ መግባባት ሊገኝ ይችላል። በጽሑፍ ውስጥ የተዋጣ ተግባቦትን ለማግኘት በንግግር ውስጥ አልባሌ መስለው የምናልፋቸውን መዋቅሮች ሳይቀሩ ማጥናትና መልመድ ይገባናል (Hedge 1988)።

በጽሕፈት ጊዜ በንግግር እንደሚታየው የተሳታፊዎች ግንኙነት ተግባቦቱን የማያስቀጥል አይሆንም። መልዕክቱ በጸሐፊው እውቀት ላይ ይመሰረታል። ስለዚህ አንድ ጽሑፍ የሚያቀርብ ሰው ሀሳቡን እሱ በተረዳው፣ በሚፈልገው መልኩ ለማስተላለፍ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ማወቅ ይጠበቅበታል (Byrne 1988፣ 4) ።

### 2.1.3.3 አእምሮታዊ ባሕርይ

ጽሕፈት የአእምሮን እንቅስቃሴ የሚጠይቅ በመሆኑ አእምሮታዊ ባህሪ አለው። የጽሑፍ ስራ የግንዛቤን መዳበር ይፈልጋል። Moore (1995፣35) "መጻፍ ማለት ማሰብ ማለት ነው" ይላሉ። ከዚህም መረዳት የሚቻለው በመጠኑም ቢሆን ሳይታሰብበት የሚከናወን የጽሕፈት ተግባር አለመኖሩን ነው።

ስርዓትና ደንብን የጠበቀ፣ የተቀናጀና ግልፅ የሆነ ጽሑፍ ማዘጋጀት እጅግ አድካሚና ከፍተኛ የአእምሮ ብስለትን፣ እውቀትንና ልምድን የሚጠይቅ ስራ ነው። Reid (1993፣ 116) ደግሞ "የጽሕፈት ትምህርት እጅን፣ አይንና አእምሮን በማቀናጀት (በማስተባበር በማስተሳሰር) በተገቢ ትዕምርታዊ ወኪሎች አማካይነት የግል ወይም የጋራ ገጠመኝን የማካፈል ችሎታን የሚጠይቅ ተግባር ነው" በማለት ለጽሕፈት ትምህርት አእምሮታዊ ችሎታ ያለውን ድርሻ ይገልፃሉ።

## 2.2 የጽሕፈት ትምህርት እርማት አሰጣጥ መንገዶች

ተማሪዎች በጽሕፈት ትምህርት ክሒሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ጽሕፈታቸውን በተደጋጋሚ ማረምና ስህተታቸውን በየደረጃው በመንገር እንዲያስተካክሉ ማድረግ ያስፈልጋል (Celce-Murcia 1991፣ 256) ። አዘውትሮ የሚጽፍ ተማሪ የሚጽፈውን ይዘት እየከለሰ ይመረምራል የአገላለፅ ስልቱን ያዳብራል፣ የራሱን ሀሳብ ማደራጀት ይማራል። ነገር ግን ስህተታቸውን ካላረምናቸው በየደረጃው በመጠቆም እንዲያስተካክሉ ካላደረግናቸው የጽሕፈት ክሂልን ማስተማር አመርቂ አይሆንም (Celce-Murcia 1991) ።

### 2.2.1 በመምህር የሚደረግ እርማት

መምህራን የተማሪዎቻቸውን ጽሕፈት ከማረማቸው በፊት መቼ ይታረም? እንዴት ይታረም? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው። በንግግር ወቅት የምንጠቀምባቸውን የማረሚያ ስልቶች በጽሑፍ ወቅት አንጠቀምባቸውም። የተዋጣለት አገላለጽ ከትክክለኛ አገላለጽ የተለየ

ነውና። ትክክለኛነት የሚለካው ከሰዋስው፣ ከፊደል፣ ከቋንቋ አጠቃቀም ወዘተ. አንጻር ነው (Byren፣ 1988፣ 123)።

የተማሪዎቹ ሐሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ የሚዳብረው መምህራን በሚሰጡት ንድፈ ሃሳባዊ ትምህርት ብቻ አይደለም። ንድፈ ሀሳብ ባላሰለሰ ልምምድ ካልታገዘ የጽሕፈትን ችሎታ ማዳበር ያዳግታል። ያለመሰልቸት መጻፍን፣ መሰረዝ መደለዝን፣ የተጻፉትን ደግሞ ደጋግሞ በማንበብ የጽሕፈት ክሒልን ማሳደግ ይቻላል። አማርኛ ቋንቋን በመማር ማስተማር የረጅም ጊዜ ታሪክ ውስጥም የተማሪዎችን የጽሕፈት ችሎታ ለማዳበር የተደረገው ጥረት ሙሉ በሙሉ ስምሯል ማለት አይቻልም። ለምን ቢባል ለተማሪዎች የራስ ልምምድ ትኩረት አለመስጠት ሊሆን ይችላል (በድሉ፣ 1996)።

ተማሪዎች የተሳሳቱትን የስህተት አይነትና ያሳዩት መሻሻል ሊነገራቸው ይገባል። መምህሩ አንድ ጽሑፍ ችግር እንዳለበት ከጠቆመ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚሻሻልበትን መንገድም ማመልከት አለበት። ተማሪዎች ምን ያህል የጽሕፈት ክሒላቸውን እንዳሻሻሉ የሚመረምሩበትን የመቆጣጠሪያ ዝርዝር (Checklist) ሊሰጣቸው ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ መምህሩ የተለያዩ አማራጭ የማረሚያ ዘዴዎችን፣ ስህተቱ ጽሑፉን ለመረዳት ከሚያደርሰው የችግር ስፋት አንፃር፣ ከተማሪዎች የስብዕና ልዩነት፣ ከማርክ መጠኑ፣ ከጊዜው ስፋት፣ ከተማሪዎች እድሜ፣ የጽሕፈት ዕድገት ደረጃ፣ ከመምህሩ ፍላጐትና ከጽሑፉ አላማ አንጻር ሊወስን እንደሚችል ይገልጻሉ (Hedge፣ 1988፣ 149)።

ከእነዚህ ጽሕፈትን የማረሚያ ስልቶች ውስጥ ሁሉንም ስህተት ማረም (Correct all the mistakes)፣ ስህተትን መርጦ ማረም (Correct mistakes selectively)፣ እና ስህተቱን በማሳየት ተማሪዎች እንዲያርሙት ማድረግ በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሒል ለማዳበር በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ እንዲጽፉ የሚያደርግ ልምምድ መኖር አለበት። በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ሁሉም መምህራን ተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሒላቸውን እንዲያዳብሩ እድሉን ማመቻቸትና ማበረታታት አለባቸው። ገንቢ የሆነና አስተማሪ ሂስ በመስጠት ተማሪዎቹ ከስህተታቸው እንዲማሩ ማድረግ ዋናው የመምህራን ግዴታ ነው። ተማሪዎቹ በመጀመሪያ ስለሚጽፉት ነገር በደንብ እንዲያስቡ፣ ከዛም ያሰቡትን በሙሉ በወረቀት ላይ እንዲያሰፍሩ፣ በመጨረሻም የጻፉትን ሃሳብ በስርዓት አዋቅረው

እና አቀናብረው እንዲጽፉ በማገዝ የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሒል ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲሻሻል ማድረግ ይቻላል (pollington and et al. 2001) ።

### 2.2.2 በብጤ የሚደረግ እርማት

የብጤ እርማት የሚባለው ተማሪዎች እርስ በርስ የሚያደርጉት የእርማት መንገድ ነው። ዘዴው በተለይ የተማሪ ቁጥር ብዙ በሆነበት ቦታ እና ጊዜ ተመራጭነቱ የጐላ ነው። በዚህ ዘዴ መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን በቡድን ይከፍላቸዋል። በመቀጠልም በቡድኑ መሪ አማካኝነት የእርስ በርስ እርማት እንዲሰጡ ማድረግ ይቻላል። ምክንያቱም መምህራን የሁሉም ተማሪ ጽሑፍ አርመው ስለማይጨርሱ በሌሎች ተማሪዎች አማካኝነት የሚረዳዱበትን መንገድ ያመቻቻሉ። ተማሪዎች ግን በራሳቸው ስልጣን የጓደኞቻቸውን ጽሑፍ እንዲያርሙና ነጥብ እንዲሰጡ ማድረግ ውጤታማ አይደለም። ነገር ግን ግልጽ በሆነ መመሪያ እና ትዕዛዝ መሰረት እንዲያርሙ ማድረግ ጠቀሜታው የጐላ መሆኑን (Raimes 1983፣ 148) ያስረዳሉ።

እርማት ማለት ተማሪዎችን የበለጠ ትክክል እንዲሆኑና መደበኛ ቋንቋ እንዲጠቀሙ የምንረዳበት እንጅ ቅጣት ወይም ትችት የምናቀርብበት ተደርጐ መታየት እንደሌለበት ከገለጹ በኋላ ተማሪዎች በቡድን መስራታቸው አንዱ የአንዱን ስራ ስለሚያርም አንዱ ከሌላው የመማር እድል ያገኛል (Edge፣ 1989፣ 50-54) ።

### 2.2.3 በራስ የሚደረግ እርማት

እንደ Kelly and Deborah (1998፣ 74) አገላለጽ ተማሪዎች የራሳቸውን ጽሑፍ በሚያርሙበት ጊዜ የራሳቸውን የመቆጣጠሪያ ዝርዝር (Checklist) መጠቀም ያለባቸው ሲሆን ራሳቸውን ሊጠይቁ ከሚችሏቸው ጥያቄዎች ውስጥ የሚከተሉትን ይዘረዝራሉ፤

- ለማለት የፈለግሁትን ነጥብ ይረዱኛል?
- እንዱን ነጥብ ተያያዥነት ባላቸው ሃሳቦች አብራርቼዋለሁ?
- ሁሉም ሃሳቦቼና የሰጠኋቸው ምሳሌዎች የተያያዙና ለመረዳት የማያስቸግሩ ናቸው? እና
- የተጠቀምኩባቸው ቃላት ውሱንና ግልጽ ናቸው በማለት ይገልፃሉ።

Edge (1989፣ 52) ደግሞ መምህሩ በዚህ ደረጃ ስህተተን ማረም እንደሌለበት ነገር ግን ስህተት እንዳለ መጠቆምና ተማሪዎች ራሳቸው የራሳቸውን ጽሑፍ እንደያርሙ ዕድል ልንሰጣቸው ይገባል። በራስ የሚደረግን እርማት ተግባራዊ ለማድረግም የጻፉትን ጽሑፍ በተመለከተ ትምህርት ከመስጠታችን በፊት ምልክት የተደረገበትን ጽሑፍ እንዲያዩት የተወሰነ ደቂቃ እንስጣቸዋልን፡ ቀጥሎ ስለጻፉት ነገር የተወሰነ ትምህርት በመስጠት በጽሑፋቸው ውስጥ በጣም ትኩረት ሰጥተው ሊመለከቱት የሚገባቸውን አስፈላጊ ነገር እናሳያቸዋለን። በአጠቃላይ መምህሩ የተማሪዎችን ስህተት በማስመር ወይም ከወረቀቱ ላይ ፍንጭ በመስጠት ወይም ሁለቱንም አብሮ በመጠቀም ተማሪዎች የራሳቸውን ስህተት እንዲለዩና እንዲያርሙ በማድረግ ሊረዳቸው እንደሚችል ሀሳብ ያቀርባሉ።

## 2.3 ጽሕፈትን የማስተማሪያ ስልቶች

የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል ለማሻሻል የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም ይቻላል። ብዙ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ተማሪዎች የጽሕፈት ክሒላቸውን ለማዳበር ቢያንስ በሳምንት አራት ጊዜ መጻፍ እንዳለባቸው ይናገራሉ።ተማሪዎችን የጽሕፈት ክሒል ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል።የማስተማሪያ ዘዴዎች እንደ መምህሩ እምነት፣ የማስተማር ስልትና የእውቀት ደረጃ ሊለያይ ይችላል። Pollington and et al. (2001; 262) እንደገለጹት፣ ጽሕፈትን ለማሻሻል ግልጽ የሆነ ህግና ስርዓት የለም።የሁሉንም ተማሪዎች የጽሕፈት ክሒል ለማሻሻል አንድ አይነት ዘዴ መጠቀም ውጤታማ አያደርግም።ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በእለቱ ትምህርት ዙሪያ ሃሳባቸውን እንዲጽፉና ለመምህሩ እንዲያሳዩ በማድረግ የጽሕፈት ክሒላቸውን ማሳደግ ይችላሉ።

ጽሕፈትን ለማስተማር ስዕሎችን፣ ፎቶግራፎችን፣ ፖስተሮችን፣ ቻርቶችን፣ ጋዜጦችን፣ ዲያግራሞችን፣ ካርታዎችን፣ ማስታወቂያዎችን ወዘተ. በመጠቀም ማስተማር እንደምንችል Raimes (1983፣ 7) ይገልፃሉ። በተለይም ስዕሎችን መጠቀም ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ስዕሎችን መመልከት ይወዳል። ስለዚህ እነዚህን ስዕሎች ክፍል ውስጥ አምጥተን መጠቀማችን የተማሪዎችን አስተሳሰብ ለማነቃቃት ይጠቅማል።

Pincas (1982፣ 5-7) መምህራን ጽሕፈትን ለማስተማር ሦስት አማራጭ መንገዶች አሏቸው ይላሉ፤

ሀ. መምህራን የራሳቸውን ጽሑፍ ያዘጋጃሉ። ይህ ግን ጊዜ የሚፈጅና እውቀትን የሚጠይቅ ስራ ነው።

ለ. መምህራን የታተሙ የጽሕፈት ማስተማሪያዎችን ያመጡና ከራሳቸው የቋንቋ ማስተማር አላማ ጋር በማዛመድ ሊጠቀሙ ይችላሉ። ይህ አማራጭ በማስተማር ሂደት ውስጥ ለሚገጥመን ችግር ብዙ ተስማሚ መፍትሔዎችን ሊያቀርብልን ይችላል። እና

ሐ. አንዳንዶች ደግሞ የተወሰኑ ጽሑፎችን ከተለያዩ ምንጮች ሲወስዱ የተወሰኑትን ደግሞ ራሳቸው ሊያዘጋጇቸው ይችላሉ። ይህ ዘዴ በአብዛኛው በመምህራን የተለመደና የሚተገበር የማስተማሪያ ዘዴ ነው በማለት ይገልፃሉ።

Byren (1988፣ 20-23) በበኩላቸው አራት አጠቃላይ ጽሕፈትን የማስተማሪያ መርሆዎች እንዳሉ ይናገራሉ። እነሱም፡-

1. ትክክለኛነት ላይ ማተኮር (focus on accuracy)

በዚህ ዘዴ ማተኮር በጽሑፍ ስራዎች ላይ ስህተቶች በብዛት ይገኛሉ። ምክንያቱም በከፍተኛ ደረጃ እርማት ላይ ትኩረት ስለሚሰጥ ነው። ተማሪዎች የተለያዩ የዓረፍተ-ነገር አይነቶችንና መልመጃዎችን እንዲጽፉና እንዲያቀናጁ ይማራሉ፤ጥሩ ምክርም ይሰጣቸዋል። በዚህ ስልት ተማሪዎች የሚፈልጉትን ሁሉ እንዲጽፉ የሚፈቀድላቸው ከሆነ ስህተት ይሰራሉ ተብሎ ይታሰባል። ስለዚህ ይህ የማስተማሪያ ዘዴ የቁጥጥርን አስፈላጊነት ያሰምርበታል። በመጨረሻም የቁጥጥሩ መጠን እየቀነሰ በመሄድ ተማሪዎች ስሕተት የሌለበት ዓረፍተ-ነገር ይጽፋሉ።

2. በብቃት ላይ ማተኮር (focus on fluency)

ይህ ጽሕፈትን የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ስህተት እንሰራለን ብለው ሳይጨነቁ በፍጥነት እስከቻሉ ድረስ እንዲጽፉ የሚደረግበት ነው። በዚህ መንገድ ተማሪዎች እየጻፉ መሆናቸውን ራሳቸው ስለሚረዱ መጻፍ የፈለጉትን ነገር ይጽፋሉ። በመጨረሻም ጽሕፈት አስደሳች የህይወት ተሞክሮ ይሆናል።

3. ውህድ አሃድ ተኮር (focus on text)

ይህ ጽሕፈትን የማስተማሪያ መርሕ ደግሞ ለአንድ የጽሑፍ ክፍል ዋና መሰፈርቱ አንቀጽ ነው ይላል፤ እናም ለተማሪዎች አንቀጽን እንዴት እንደምንመሰርትና እንደምናደራጅ ማስተማር አለብን ይላል። አንቀጽን ለመመስረትም የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም እንደምንችል ይናገራሉ፡

- ከተዘበራረቁ ዓረፍተ-ነገሮች አንቀጽ መመስረት
- ከሞዴል አንቀጽ አቻ አንቀጽ መጻፍ፣
- ከመንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገር አንቀጽ መመስረት እንችላለን ይላሉ።

ይህ የአቀራረብ ዘዴ በጽሕፈት ትምህርት ማዕከላዊ ችግር የሆነውን ከዓረፍተ-ነገር በላይ ሀሳብን በትክክል መግለጽ አለመቻልን ያስወግዳል።

4. ዓላማ ተኮር (focus on purpose)

ይህ ጽሕፈትን የማስተማሪያ መርህ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በዓላማ እንዲጽፉ ለማድረግ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ያስችላል። ይህን ማድረግ ደግሞ ቀላል ተግባር ነው። ለምሳሌ፡- በክፍል ውስጥ አንድ ተማሪ ለሌላው እንዲጽፍ ማድረግ ወይም ጽሕፈትን በሚና ነጠቃ ውስጥ መጠቀም ነው። ይሁን እንጅ ይህ አቀራረብ እንደ ጽሑፋዊ ተክሕኖት ሁሉ በጽሑፍ ቋንቋ ጊዜ የሚገጥማቸውን የተወሰኑ ችግሮች ለማቃለል ባይችልም ጽሕፈት እንዴት የመግባቢያ ቅርጽ እንደሆነ ለማሳየትና ተማሪዎች እንዲጽፉ ለማነቃቃት የሚያስችል ዘዴ ነው።

## 2.4 ሐሳብን /ስሜትን/ በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ መመዘኛዎች

ጽሕፈት ሃሳብን ለመግለጽና ለተደራሲ መልዕክትን ለማስተላለፍ ይጠቅማል። በመሆኑም ሃሳብ ወይም መልዕክት ለጽሕፈት ስራ በጣም ወሳኝ ነው። ጸሐፊው መልዕክቱን ለተደራሲው በጥሩ ሁኔታ ለማድረስ ደግሞ ከፊደል አጠቃቀም ጀምሮ ትክክለኛ ስርዓተ ነጥብ፣ ሰዋስውና ጥንቃቄ የተሞላበት የቃላት መረጣ ማድረግ አለበት (አለማየሁ 1998፣27) ።

### 2.4.1 የቋንቋ አጠቃቀም

ጸሐፊው በጽሕፈት ወቅት የሚጠቀምበት ቋንቋ መደበኛና በንግግር ጊዜ ከሚጠቀምበት ቋንቋ የተለየ መሆን አለበት። ይህ ማለት ግን በንግግር ጊዜ የሚጠቀምባቸውን ቃላት መገልገል

የለበትም ለማለት ሳይሆን ጽሕፈት በአካል እንቅስቃሴ፣ በድምጽ ቅላጼ ወዘተ. የማይታገዝ ከሒል በመሆኑ ጸሐፊው ሃሳቡን በትክክል ለማስተላለፍ የሚጠቀምባቸው ቃላት በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሊታወቁ የሚችሉ ቢሆኑ የበለጠ የተሻለ ነው ለማለት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጸሐፊው የሚጠቀምባቸው ዓረፍተ-ነገሮች የቋንቋ አወቃቀር ስርዓት የተስተካከለ የአንቀጽ አደረጃጀቱ ያማረና የሀሳብ ፍሰቱ የተዋጣለት መሆን ይኖርበታል (አለማየሁ 1998፣ 27) ፡፡

Ur (1996: 163) በጽሕፈት ጊዜ ከንግግር የበለጠ ከፍተኛ የሆነ መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም የሚታይበት መሆኑን ከገለጹ በኋላ ሃሳባችንን በጽሑፍ በምንገልጽበት ጊዜ ለአውዱ ተስማሚ የሆኑ፣ ለዛ ያላቸውንና ምስል ከሳች የሆኑ ቃላትን መርጦ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡

## 2.4.2 መደበኛ ቃላት

መደበኛ ቃላት ማለት በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ በሰፋት የሚታወቁ ማለትም በስብሰባ፣ በሬዲዮ፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔት ወዘተ. የምንገለገልባቸው የጽሑፍ ቋንቋ ናቸው፡፡ የንግግር ቋንቋ ኢ-መደበኛ ቃላት ብቻ ናቸው ማለት ባይቻልም ብዙ ጊዜ ኢ-መደበኛ ቃላትን የምንጠቀምባቸው ለንግግር ነው፡፡

Trimmer and Mccrimmon (1988፣ 213-216) በበኩላቸው የቃላት ምርጫን በተመለከተ ጸሐፊዎች በጽሑፋቸው አውድ ውስጥ የሚጠቀሙባቸውን ትክክለኛ ቃላት ከመዝገበ ቃላትም ቢሆን ማግኘት አይችሉም፡፡ ስለዚህም የትኛው ቃልና ፍቺ ከጽሑፋቸው አውድ ጋር ሊሄድ እንደሚችል ለመወሰን የቃላትን ተገቢነት፣ ውሱንነትና ምስል ከሳችነት መመርመር እንዳለባቸው ይጠቁማሉ፡፡

ተገቢነት ሲባል ቃላት ጸሐፊው ከመረጠው ርዕስ፣ አንባቢ እና አላማ ጋር የሚስማሙ ከሆነ ተገቢ ቃላት ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ከቃላት ምርጫችን በተጨማሪ በጽሑፍ ድምፀት (Tone) እና ስልት (style) ላይም ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡ የቃላት መርጫ፣ ድምፀትና ስልት ለአንድ ጽሑፍ ተገቢ የሆነ አውድ ለመፍጠርና መደበኛነትን ለመላበስ የጸሐፊውን ውሳኔ የሚሹ ነገሮች መሆናቸውን ያብራራሉ (Timmer and McCrimmon 1998 213-216)፡፡

### 2.4.3 የቋንቋ አወቃቀር

ይህ ርዕስ የሚመለከተው ሰዋስውን ይሆናል። ተማሪዎች በጽሑፍ ሃሳባቸውን ለአንባቢያን ለማስተላለፍ ሲሞክሩ ቋንቋው የሚፈቅደውን ትክክለኛውን ስርዓት መከተል አለባቸው። ለዚህም ነው ባዬ (1987፣8) "ከማንኛውም የክህሎት ትምህርት በስተጀርባ ማንኛውም የቋንቋ ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባ ጥልቅ የሆነ እውቀት አለ። ይኸውም ሰዋስው ሲሆን... የአንድን ቋንቋ ስርዓት ከድምፅ አስካሉ እስከ ሀገር አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው" በማለት የሚናገሩት። እንግዲህ ተማሪዎች በጽሑፋቸው ውስጥ የሚጠቀሙበት ቃል፣ ሀረግና ዓረፍተ-ነገር በቁጥር፣ በፆታ፣ በመደብ የተስተካከለና የቋንቋውን ስርዓት የተከተለ ከሆነ ጠቀሜታው የጐላ መሆኑን የቋንቋውን አጠቃቀም ከነስርዓቱ የሚያውቅ ሰው መኪና አነዳድና የመኪና አካላትን አሰራር እንደሚያውቅ መካኒክ ሹፌር የሚቆጠር ነው በማለት አስፈላጊነቱን ያስምሩበታል (ባዬ፣ 1987፣ 10)።

ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ዓረፍተ-ነገር ውስጥ የሚገኙ ሁለት ወይም ከሁለት የበለጡ ቃላትና ሀረጋት መዋቅራዊ አቻዊነታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ሁሉም ተዋቃሪዎች ተመሳሳይ የሆነ ቅርፅና ሰዋስዋዊ አገልግሎት ሊኖራቸው እንደሚገባ ይገልጻሉ (Trimmer and McCrimmon፣ 1988፣189) ።

### 2.4.4 የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም

ስርዓተ ነጥቦች በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ይኸውም ቃልን ከቃል ከመለየት አንስቶ እያንዳንዱ ዓረፍተ-ነገር ያለውን ድምፀት ለመለየትና ሃሳብን በትክክል ለማስተላለፍ የላቀ ድርሻ አላቸው።

ሥርዓተ ነጥቦችን በተመለከተ ዮናስ አድማሱና ሌሎች /1966፣ 356/ እንዲህ ይገልጻሉ፤

> የተጻፈን ነገር በትርጓሜው መሰረት ለአንባቢ ግልጽ በሆነ መንገድ በትክክል ለማገበብ የሚረዱ ልዩ ልዩ ምልክቶች ያስፈልጋሉ። በንግግር ጊዜ ተናጋሪው ለሰሚው ድምጹን ከፍና ዝቅ በማድረግ፣ ዝግ፣ ቆም በማለትና በሰውነትም እንቅስቃሴዎች የፈለገውን ነገር ለማስረዳት ይችላል። በጽሑፍ ግን፣ በነዚህ ዘዴዎች መጠቀም ስለማይቻል ሌሎች ለአይን የሚታዩ ምልክቶች ያስፈልጋሉ። እነዚህም ምልክቶች በጽሑፍ ሰፍረው ተከታትለው የሚመጡት ቃላትና ሀረጎች እርስ በርሳቸው ምን ግንኙነት እንዳላቸው እያመለከቱ ጽሑፉን በማያሻማ መንገድ አንብቦ ለመረዳት ይጠቅማሉ።

አማረ /1976/ ደግሞ የሥርዓተ ነጥቦችን ሚና በተመለከተ የሚከተለውን ገልጸዋል፤

> በጽሑፍ ውስጥ የሚገቡ ነጥቦችና ምልክቶች ዓይነተኛ ተግባር የቃላት፣ የሀረጎች፣ የዓረፍተ ነገሮች አሰላለፍ፣ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት በመከተል፣ በጽሑፍ የሰፈረውን መልዕክት ያለምንም መድበስበስ፣ በአንድ አፍታ የንባብ እይታ ለአንባቢው እንዲከሰትለት ማገዝ ነው። አንድን መልዕክት በወረቀት ላይ በሰፈሩ ቃላት አማካይነት ለአንባቢ ማስተላለፍ በሚደረገው ጥረት ነጥቦችንና የተለያዩ ምልክቶችን በተገቢ ስፍራቸው ላይ ማዋልን ማወቅ መልዕክትን አደምኖ ሳይሆን አፍክቶ ለማቅረብ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ምንም እንኳ እንደ ፊደሎች ሁሉ የስርዓተ ነጥቦችን አጠቃቀም በተመለከተም ፍፁም ወጥ የሆነ ስርዓት ባይኖርም አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸው ነጥቦች አሉ። ስለዚህም የስርዓተ ነጥቦችን አጠቃቀም በተመለከተ ተማሪዎቻችንን መርዳት ያለብን ግትር የሆነ ህግ በመያዝ ሳይሆን በአንባቢያችን ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ እንዲለዩ በማድረግ ማበረታታት እንዳለብን ይገልፃሉ (Byren፣ 1988፣16)።

## 2.4.5 ተነባቢነት

ተነባቢነት ሲባል ከጽሑፍ አጠቃላይ ውጫዊ ገፅታ ማለትም ከሆሄያት መጠን፣ መስመር አጠባበቅ፣ ከቀኝና ግራ ህዳግ አጠባበቅ፣ ከአንቀጽ አጀማመር ወዘተ. ጀምሮ ውስጣዊ ገጽታ እስከምንለው ማለትም የቃላትን መረጣ፣ የአገላለጽ ውበትን፣ የዓረፍተ-ነገሮችን ሰዋስዋዊነት፣ የሀሳብ ፍሰት እና የይዘት ተገቢነት የሚሉትን ነገሮች ሁሉ ይመለከታል (Byren፣ 1988፣ 17)።

Trimmer and Mccrimmon (1988፣ 219) በበኩላቸው በጣም እምቅ ሃሳብ የያዙ ቃላትን እና ያልተለመዱ እንግዳ ቃላትን በጽሑፋችን ውስጥ መጠቀም እንደሌለብን ይገልጻሉ።

በጽሑፍ የሚቀርብ ሐሳብ ተቀባይነት የሚኖረው ለማስተላለፍ የሚፈልገውን መልዕክት ለማንፀባረቅ የሚችሉ ቃላት መርጦ በመጠቀም አያይዞም አቀናብሮ በትክክል የመግለጽ፣ የማስረዳት ወዘተ. ችሎታ ሲኖር ነው። እንዲሁም ማንኛውም ጽሑፍ የሚገነባው ቃላትን በሀረግ፣ ሀገጎችን በዓረፍተ ነገርና ዓረፍተ-ነገሮችን በአንቀጽ አቀናብሮ በማቅረብ ስለሆነ በተለይ ዓረፍተ-ነገርና አንቀጽ የመጻፍ ልምድን ማጐልበቱ ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል።

Heaton (1991፣ 135) እንደገለጹት፣ የጽሕፈት ክሒሎች ውስብስብ በመሆናቸው ጽሕፈትን ማስተማሩም ሆነ ክሒሉን ማዳበሩ ያስቸግራል፣ምክንያቱም የሰዋስዋዊ አገባቦችን ጠብቆ

ቃላትን በአረፍተ ነገሮች አሳክቶ የማቅረብ ልምድ መኖር ብቻ ሳይሆን ተገቢ የሆኑና ሚዛናዊነትን የጠበቁ ሃሳቦችን የማፍለቅ ችሎታን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ ሃሳብን /ስሜትን/ በትክክል በጽሑፍ ለማስተላለፍ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን የጽሕፈት ክሒሎች በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ እንደሚቻል በማመልከት Heaton እንደሚከተለው አቅርበውታል፤

1. ትክክለኛና ተገቢ የሆነ ዓረፍተ-ነገሮች የመጻፍ፣
2. ለጽሑፍ ቋንቋ አስፈላጊ የሆኑ ስርዓተ-ነጥቦች አገልግሎት ተረድቶ የመጠቀም፣
3. ተቀባይነት ያለው ሃሳብ ማቅረብና አስፋፍቶ የመግለጽ፣
4. ለማስተላለፍ እንደሚፈለገው ሃሳብ ይዘት ተገቢነት ያላቸውን የአጻጻፍ ስርዓቶችን (writing styles) ተከትሎ የዓረፍተ-ነገርን ትክክለኛ አሰካከና የአንቀጽ አወቃቀር ስልት ጠብቆ የመጻፍና ተቀባይነት ባለው መደበኛ ቋንቋ የመጠቀም፣
5. ጽሑፍ ለማንና ለምን አላማ እንደሚቀርብ ወስኖ የማቅረብ፣ ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሃሳብ ለመግለጽ ተገቢና ተስማሚ የሆኑ ቃላት መርጦ የመጠቀም፣ እንዲሁም የሃሳብ ሚዛናዊ አቀራረብን ጠብቆ ድርጊቶችን በቅደም ተከተላቸው አቀናብሮ የመግለጽ ችሎታ ናቸው፡፡

እነዚህ ክሂሎች (writing Skills) ሃሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታን ለመለካት ወሳኝነት አላቸው፡፡ ስለዚህ አረፍተ ነገርና አንቀጽ የመጻፍ ብቃትን ለመለካት፡-

- የቃላት አገባብና የአገባብ ቅርጽ ተረድቶ የመጠቀም፣
- የሰዋስዋዊ ተገባብ ትክክለኛነት የመጠበቅ፣
- በስርዓተ-ነጥቦች በአግባቡ የመጠቀም፣
- የአጻጻፍ ስርዓቶችን ተከትሎ አስፈላጊና ተገቢ የሆኑ ዝርዝር ሃሳቦችን የማስፈር፣
- የሀሳብ ሚዛናዊ አቀራረብ የመጠበቅና ሃሳብን ወስኖ በግልጽ የማቅረብ የሚያያዝና አቀናብሮ በትክክል የማስተላለፍ ችሎታን መመዘን ያስፈልጋል Heaton (1991)፡፡

በዚህ መሰረት ተጠኝዎቹ አንቀፅ እንዲጽፉ ፈተና በመስጠት ሐሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታቸው ይመዘናል፡፡

## 2.5 ጽሑፋዊ ተግባቦትን የሚያውኩ የቃላት አጠቃቀም መልኮች

ቃላት ሃሳብን ማስተላለፍ፣ ማመስጠር፣ መልክን፣ እንቅስቃሴን፣ ቀለምን፣ ሁኔታን በምናብ ለማሳየት፣ ጥልቅ የሆነ ስሜትን አግዝፎ ለማውጣት ወዘተ. ያግዛሉ /የሻው 1996፣ 28-29/።

ከዚህ በተጨማሪም ቃላት ባይኖሩ ኖሮ ሀረጎችን፣ ዓረፍተ-ነገሮችንና አንቀጾችን ለመገንባት አንችልም ነበር። ይሁን እንጅ ይህን ሁሉ ጠቀሜታ ያላቸው ቃላት በጥንቃቄና በተገቢው መንገድ ካልተጠቀምንባቸው ጽሑፋዊ ተግባቦትን እንደሚያውኩ መገመት አያዳግትም።ይህን በተመለከተ አማረ 1976 እንዲህ ይገልጻሉ፣

> በጽሑፍ የሰፈረ ሃሳብ በጽሑፍ በመገለጡ ብቻ የመግባቢያ መሳሪያ ሊሆን አይችልም። በምንናገረው ቋንቋ የሰፈሩ አንዳንድ ሀሳቦች እንኳን፣ የፍቺአቸውን እጅና እግር ለመለየት ብዙ ጊዜ ይሳነናል። ይህ ከሚሆንበት ምክንያቶች ዋናዎቹ በጽሑፍ የቀረበው ሀሳብ በማናውቃቸው ቃላት የተቀናበረ ሲሆን ወይም ደግሞ ቃላቱ ራሳቸው የተሳከሩበት ሁኔታ ሀሳቡን በማጉላት ፈንታ የሚያዳምኑ ሲሆንና የጸሐፊው የሃሳብ አቀራረብ የማይጥምና የማይስብ ሆኖ ሲገኝ የመልእክቱን ተቀባይ ፍላጎት በማገታት ሃሳቡን እንዳይቀስም ያግዱታል። አንድ ሃሳብ በጽሑፍ በሚገለጥበት ጊዜ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት እክሎች ነጻ ካልሆነ የመግባቢያ መሳሪያነቱ እምብዛም ይሆናል /አማረ 1976፣ 11/።

ከዚህ ጽሑፍ የምንረዳው አንድን ሃሳብ በጽሑፍ በምናሰፍርበት ጊዜ የቃላት አጠቃቀማችን ሃሳቡን አጉልቶና አግዝፎ  እንጅ አደብዝዞና አደምኖ የሚያሳይ መሆን እንደሌለበት ነው። በዚህም ቃላትን በጥንቃቄ ካልተጠቀምንባቸው የሚያስተላልፉት ሀሳብ ለአንባቢው ግርታንና መደናገርን የሚፈጥር ይሆናል።

Ur (1996፣63) በበኩላቸው ስለ ቃላት አጠቃቀም እንዲህ ይላሉ። በጽሕፈት ጊዜ ከንግግር የበለጠ ከፍተኛ የሆነ መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም የሚስተዋልበት መሆኑን ከገለጹ በኋላ ሃሳባችንን በጽሑፍ በምንገልጽበት ጊዜ ለአውዱ ተስማሚ የሆኑ፣ ለዛ ያላቸውንና ምስል ከሳች የሆኑ ቃላትን መርጦ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ (Ur 1996:63)።

ከዚህ በተጨማሪም Kelly and Deborach (1998፣ 69) በጽሑፎችን ውስጥ የምንጠቀምባቸው ቃላት አንባቢያችን ሃሳባችንን እንዲረዳልን ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ቀጥተኛ ሚና ስላላቸው የምንጠቀምባቸው ቃላት ውስን (Specific) ተገቢነት (appropriateness) እና ምስል ከሳችነት (imagnery) የተላበሱ መሆን እንዳለባቸው ይገልፃሉ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምሁራን ቃላት ያላቸውን ጠቀሜታና አስፈላጊነት ቢገልጹም በጥንቃቄና በአግባቡ ጥቅም ላይ ካልዋሉ ጽሑፋዊ ተግባቦትን አደጋ ላይ እንደሚጥሉ አጽንኦት በመስጠት ገልጸዋል። ከዚህ በመቀጠልም ጽሑፋዊ ተግባቦትን የሚያውኩ የቃላት አጠቃቀም መልኮችን እናያለን።

## 2.5.1 የቃላትና ሐረጋት ድግግሞሽና ድረታ

ድግግሞሽና ድረታ ጽሑፋዊ ተግባቦትን የሚያውኩ የቃላት አጠቃቀም መልኮች ሲሆኑ በአንድ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙት ቃላት በተደጋጋሚና በሚያሰለች ሁኔታ ከሚገባው በላይ መጠቀም ያመለክታል። ይህን በተመለከተ የሻው /1996፣ 51/ እንዲህ ይገልጹታል። "ቃላትን መደጋገም ጠቃሚ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ለጽሑፍም ሆነ ለንግግር ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረው ይሆናል። ነገር ግን ከሚገባው በላይ /በሚያሰለች መልኩ/ መመናቸክ /ሙዝዝ ማለት/ ግን ግልጽ የሆነውን ነገር እየመላለሱ መንገር ወይም አንድ ቃል ወይም አገላለጽ ላይ ክንችር ብሎ መጣበቅ ስራችንን አላዋቂ የዋለበት ያደርጋል" በማለት ይገልጻሉ።

አንድ ቃል በራሱ የሚፈለገውን ትርጉም ማስተላለፍ እየቻለ ሌሎች ተጨማሪ ቃላትን የምንጠቀም ከሆነ የሐሳቡን ብሩህነት ከማጉላት ይልቅ እንዲደበዝዝ ስለሚያደርግ እንዲህ አይነት ቃላትን በመደጋገም መጠቀም አላስፈላጊ ነው።

## 2.5.2 የተሰለቹ ቃላትና አገላለጾች

ብዙ ተማሪዎች በጽሕፈት ጊዜ ከሚገጥማቸው ችግሮች ውስጥ አንዱ የቃላት እጥረት ወይም ቃላትን በተገቢው ቦታ መርጦ የማስቀመጡ ነገር ነው።

Trimmer and Mccrimmon (1988፣ 230) የተሰለቹ ቃላት ማለት በአንድ ወቅት ማራኪነትን የተላበሱ አባባሎች የነበሩ፣ ለብዙ ጊዜ የተገለገልንባቸው ትኩስነታቸውንና ሃይላቸውን ያጡ ቃላት ወይም ሀረጋት ናቸው በማለት ይገልጻሉ።

በተጨማሪም የሻው (1996፣ 69) Gartiside (1981) ን በመጥቀስ የተሰለቹ የቋንቋ ቅንጣቶች የሚመለከታቸው ተዘውትረው ከመነገር የተነሳ ወዛቸው ምጥጥ ተደርጎ እንዳለቀ ነገሮች ሲሆኑ ሰው ያለውን ስሜትና ሐሳብ ብቻ ሙጥኝ የምንል እንጂ፣ በራሳቸው አዳዲስና ያልነፈሰባቸው አገላለጾችን የመፍጠር ብቃት/ ጸጋ የጎደለን ያደርጉናል በማለት ይገልጹታል።

### 2.5.3 የተውሶ ቃላት

የተውሰ ቃላት ማለት አንድ ቋንቋ ከሌላው ቋንቋ የሚዋሳቸው ቃላት ማለት ሲሆን በቋንቋችን (በምንጽፈው ቋንቋ) ውስጥ እነዚህን ቃላት መጠቀም የምንችለው የምንጽፈው ቋንቋ የራሱን ነገር መግለጽ ሳይችል ሲቀር ነው። ነገር ግን በምንጽፍበት ቋንቋ ሃሳባችንን መግለጽ እየቻልን አላስፈላጊ የሆነ የውጭ ቃል መጠቀም የለብንም።

## 2.6 አንቀጽ

አንቀጽ ማለት አንድ ሃሳብ ብቻ የሚተላለፍበት የጽሑፍ ክፍል ነው። አንቀጽን የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ አገላለፆች የገለጿቸው ሲሆን ከዚህ ቀጥለን እናያቸዋለን።

"አንቀጽ ማለት አንድ ዓረፍተ-ነገር ወይም በቁጥር ከአንድ የበለጡና በሃሳብ ተዛምዶ የተሰናሰሉ ዓረፍተ-ነገሮች የሰፈሩበት በአንድ ድርሰት ውስጥ ተካተው ሲቀርቡ የሚገባቸው ነጥቦች በተመጠነና ራሱን በቻለ ሁኔታ የሚያራምድ የጽሑፍ አካል ነው" /አማረ 1976፣ 90-91/።

"አንቀጽ ማለት ከልዩ ልዩ ዓረፍተ ነገሮች የተሰራ፣ ስለአንድ ሃሳብ ብቻ የሚያወጋ፣ የሚተርክ፣ የሚያትት፣ ወዘተ. አነስተኛ ጽሑፍ ነው" ዮናስ እና ሌሎች /1966፣ 27/።

Kelly and Deborah (1988፣ 33) በበኩላቸው የአንቀጽን ሚና "አንድን ወግ (Essay) ለመገንባት የሚያስችል ጡብ ነው" በማለት ይገልጻሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው አንቀጽ የምንለው ነገር በአንድ ሃሳብ ላይ ብቻ የሚያጠነጥን፣ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን የያዘ፣ ዝርዝሮቹ ዓረፍተ-ነገሮች ዋናውን ሃሳብ የሚያብራሩና የሚደግፉ እርስ በርስ ትስስር ያላቸውን ዓረፍተ-ነገሮች የያዘ የጽሑፍ ክፍል ነው።

አንቀጽን በጽሑፋችን ውስጥ የሚንጠቀምበት ምክንያት በተመለከተ አማረ 1976፣ 90 እንዲህ ይገልጹታል፤

> አንቀጽ የአንባቢ ዓይን ድካም እንዳይሰማው ወይም ከማንበቡ በፊት በሚያየው ጥቅጥቅ ያለ የፊደል ደን እንዳይሰለች ተብሎ ብቻ የሚዘጋጅ አይደለም። አንቀጽን ለአንባቢ እየዓንታን ከመፍጠር የላቀና መሰረታዊ የሆነ አላማ አለው። ይህም መሰረታዊ አላማ የጽሑፍ ስጋና ደም የሆነውን ሃሳብ ይመለከታል። በሌላ አነጋገር ድርሰትን በአንቀጽ

መከፋፈል የሚያስፈልግበት ምክንያት በቅደም ተከተል የሚቀርቡት ሃሳቦች የተለየ /በአት/ ቦታ እንዲራቸውና በሌላ ፍሬ ሃሳብ ጣልቃ ገብነት ሳይድፈነፈኑ በሚገባ ዳብረውና ጎልተው እንዲወጡ ለማድረግ ነው /አማረ 1976፤ 90/።

ስለ አንቀጽ ምንነትና ጠቀሜታ ከላይ በአጭሩ ለመግለጽ ተሞክሯል። ቀጥሎ ደግሞ ስለባህርያቱ እናነሳለን።

## 2.6.1 የአንቀጽ ባሕርያት

የአንቀጽን ባህሪያት ወይም የተዋጣ አንቀጽ መስፈርትን የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ ቃላት ቢገልጿቸውም በሦስት ከፋፍለው ይመድቧቸዋል። እነዚህም ምሁራን ደረጀ /1996፤55/ "ዋና ዋናዎቹ የአንቀጽ ባህሪያት የሚባሉት ሦስት ናቸው። እነዚህም የአንቀጽ አንድነት፣ ውህደትና አጽንኦት ናቸው" በማለት ይገልጻሉ።

Trimmer and Mccrimmon /1998፣ 159/ በበኩላቸው "አንድ የተዋጣለት አንቀጽ አራት ተፈላጊ ነገሮችን ማሟላት አለበት። እነሱም አንድነት፣ ሙሉነት፣ ቅንብርና ተያያዥነት ናቸው" በማለት ይገልጻሉ።

በተጨማሪም የሻው /1996፣ 173-179/ "የተዋጣ የአንቀጽ መስፈርት ሦስት ሲሆኑ እነዚህም የአንቀጽ አንድነት፣ ምልዓት እና ጥምረት ናቸው" በማለት ይዘረዝሯቸዋል።

ከዚህ ጽሑፍ የምንረዳው አንቀጽን አንቀጽ ከሚያሰኙት ነገሮች ውስጥ አንድነት፣ ተያያዥነትና ጉልህነት ዋነኞቹ መሆናቸውን ነው።

ከላይ ባየናቸው ጽሑፎች ውስጥ የተለያዩ ምሁራን የአንቀጽን ባህሪያት ወይም የተዋጣ አንቀጽ መስፈርትን በሦስት እንደከፈሏቸው አይተናል። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ እያንዳንዱን በተናጠል ለማየት እንሞክራለን።

### 2.6.1.1 የአንቀጽ አንድነት

የአንቀጽ አንድነት ሲባል በአንቀጽ ውስጥ ያሉት ዓረፍተ ነገሮች ከጭብጡ ሳይወጡ በስርዓት የተዋቀረውን ጽሑፍ ማተት/ መዘርዘር ሲችሉ ነው። ሲታተትም ስርዓትና ወግ ባላቸው ቃላትና ሀረጋት እንደየአግባብነታቸው መስደር ነው።

አንቀጽ አንድነት አለው ሲባል በአንቀጽ ውስጥ አንድ መንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገር ብቻ አለ ማለታችን ነው። ይኸውም በአንቀጽ ውስጥ ያሉት ዓረፍተ-ነገሮች በሙሉ ስለ አንድ ጉዳይ ብቻ እንደሚያብራሩ ይገልጻሉ (kelly and Deborah፣ 1998፣ 57፤ Trimmer and McCrimmon፣ 1988፣ 159)።

መንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገር ማለት በአንቀጹ ውስጥ ያለውን ዋና ሃሳብ የያዘ ዓረፍተ-ነገር ማለት ነው። ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ዋናውን ሃሳብ የሚያሳዩ ሁለት ዓረፍተ-ነገሮችን ማግኘት የምንችል ቢሆንም ብዙ ጊዜ ግን መንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገር የሚገልጸው በነጠላ ዓረፍተ-ነገር መሆኑን ነው። (Trimmer and McCrimmon 1988፣ 163፤ Kelly and Deborah፣ 1998፣54)።

## 2.6.1.2 የአንቀጽ ቅንብር /ጉልህነት/

ቅንብር ወይም ጉልህነት ከአንቀጽ ባህሪያት ሁለተኛው ሲሆን ይህን በተመለከተም የተለያዩ ምሁራንን ሀሳብ ለማየት እንሞክር።

አንቀጽ ጉልህነት አለው ሲባል ለመንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገር ድጋፍ የሚሰጡ ሃሳቦች (ዓረፍተ-ነገሮች) እንደ ክብደት ደረጃቸው ከአብይ ወደ ንዑስ ወይም ከንዑስ ወደ አቢይ ሃሳብ በቅደም ተከተል ቀርበዋል ማለት ነው (አለማየሁ፣ 1998፣32)።

አደረጃጀትን በምንመረምርበት ጊዜ ከአጠቃላይ ወደ ውስን ወይም ከውስን ወደ አጠቃላይ አልያም ከዋና ዋና ጠቃሚ ሃሳቦች ወደ ዝርዝር ሃሳቦች ወይም በተገላቢጦሽ የምናደርገውን እንቅስቃሴ ይመለከታል። ተማሪዎችን በአደረጃጀት ላይ የሚገጥማቸው አንዱ ችግር በዋና ዓረፍተ-ነገር (topic) እና በዝርዝር ሀሳቦች (supporter) መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አለመቻል ነው። አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች አጠቃላይነት ያላቸውን ዓረፍተ-ነገሮች ብቻ ይጽፋሉ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ሁሉም ዓረፍተ-ነገሮች ዝርዝር ሀሳብ የያዙና አንድም አጠቃላይነት የሚታይበት ዓረፍተ-ነገር የማይኖርበት ጽሑፍ ይጽፋሉ (Raimes፣ 1983፣ 123፣ Trimmer and McCrimmon 1988፣ 168)።

Kelly and Deborah (1998፣ 65) በበኩላቸው ጸሐፊው ሃሳቡን የሚያደራጅበት መንገድ በአንባቢው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ከጠቆመ በኋላ ሦስት የተለመዱ ሃሳብን የማደራጃ ዘዴዎች መኖራቸውን ይገልጻሉ። እነሱም በጊዜ ቅደም ተከተል፣ ከሚገኝበት ቦታ እና

ከጠቀሜታ አንጻር በአንድ አንቀጽ ውስጥ የሚገኙትን ዓረፍተ-ነገሮች ማደራጀት እንደሚቻል ያብራራሉ።

ደረጀ /1996፣ 62/ ደግሞ "የሃሳብ ጉልህነት የሚገኝባቸው ስልቶች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ በአንቀጹ መጨረሻ ላይ ኃይለ ቃሉ የያዘውን ዋና ሀሳብ በቀጥታ ወይም በሌላ አባባል መድገም፣ ተፈላጊውን ሀሳብ የያዘው አቢይ ሀረግ ወይም ዓረፍተ-ነገር ከሌላው የጽሑፍ አካል ጎልቶ ይታይ ዘንድ በማድመቅ ወይም ከስሩ በማስመር አጽንኦትን ማመልከት ይቻላል" በማለት የሀሳብ ጉልህነት የሚገኝባቸውን ስልቶች ይጠቁማሉ።

### 2.6.1.3 የአንቀጽ ውህደት /ግጥምጥምነት/

አንድ አንቀጽ ዝምድና ወይም ጥምረት አለው ሲባል በውስጡ የሚገኙት ዓረፍተ-ነገሮች እርስ በእርስ የተያያዙና አንባቢው በቀላሉ ከአንድ ዓረፍተ-ነገር ወደ ሌላው በመጓዝ አንቀጹን በተከታታይ እንደሚመጡ የተለያዩ ዓረፍተ-ነገሮች ሳይሆን ተያያዥነት እንዳላቸው በመቁጠር እንዲያነብ ያስችላል ማለት ነው (Trimmer & McCrimmon 1988፣ 168፤ Kelly & Deborah 1998፣ 59)።

Kelly & Deborah በመቀጠልም አንድ ጽሑፍ ተያያዥነቱን እንዲጠብቅ መሸጋገሪያ ቃላት (transitions) እና የሃሳብ ወይም የዓረፍተ-ነገር አደረጃጀት ጠቃሚ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ጸሐፊው ለአንባቢው በዓረፍተ-ነገሮችና በአንቀጾች መካከል ያለውን ግንኙነት በግልጽ ማስተመጥ አለበት። አንድ ሰው ጥሩ የቋንቋ ችሎታ እያለው አያያዥ ቃላትን በትክክል ካልተጠቀመ ተቀባይነት ያለው አንቀጽ ወይም ወግ (essay) መጻፍ አይችልም።

አንድ አንቀጽ ከአንድ ሃሳብ በላይ ባይዝ ይመረጣል። ለምሳሌ አንድን ዓረፍተ-ነገር ስንጽፍ በ'እና' 'በሌላ መልኩ' ወዘተ. በመሳሰሉት አያያዥ ቃላት በመጠቀም ሁለት ሃሳቦችን በአንድ ዓረፍተ-ነገር መግለጽ አይመከርም።' ዓረፍተ-ነገር ሲጻፍም በተገቢው መልኩ ሰዋስዋዊ ስርዓቱን(የቃላት አሰካክ፣ ስርዓተ-ነጥብ) ወዘተ. የጠበቀ መሆን አለበት። ቀላልና ግልጽ የሆኑ ቃላት መጠቀምም አንዱ የጽሑፍን ዋጋ ከፍ የሚያደርግ ነው (Fenton,2003) ።

የአንቀጽ ውህደትን ለመጠበቅ ደረጀ /1996፣ 58/ እንዲህ ይገልጹታል። "የአንድ አንቀጽ ውህደት ከሚጠበቅባቸው ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹ፣ የመሸጋገሪያ ሀረጎች፣ የዓረፍተ-ነገሮች

አቻዊነት ወይም ትይዩነት፣ ቁልፍ ቃላትን መድገም የመሳሰሉት ናቸው" በማለት የአንቀጽ ውህደትን ማስገኛ ዘዴዎችን ይጠቁማሉ።

## 2.7 ሰነዶች

በዚህ ርዕስ ስር ለዚህ ጥናት መሠረታዊ የሆኑ ሰነዶችን ማለትም፣ በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል (5-8) ማጠናቀቂያ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በመማር ከየክፍል ደረጃው የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃትና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው መርሐ-ትምህርት ውስጥ የሚገኙ የጽሕፈት ትምህርት ይዘቶች እንዲሁም የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት የያዟቸው የጽሕፈት ትምህርቶች ይዳሰሳሉ።

### 2.7.1 በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው ሳይክል /ከ5-8/ ማጠናቀቂያ የአፍ መፍቻ ቋንቋን በመማር ከየክፍል ደረጃው የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

በዚህ ሰነድ ውስጥ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብ፣ በመጻፍ፣ በሰዋስው እና በስነ-ጽሑፍ የሚጠበቀውን የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ በዝርዝር ያቀረበ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያለውን የ8ኛ ክፍል የጽሕፈት ክሂል ብቃት በዝርዝር እናያለን፣

- በሚሰጧቸው ርዕስ አጭር ጽሑፍ መጻፍ እንዲችሉ መረጃዎችን አሰባስበው ዋናና ዝርዝር ነገሮችን ያካተተ አስተዋፅኦ ማዘጋጀት፣
- የተማሩዋቸውን ስርዓተ-ነጥቦች፣ ትዕምርተ አንክሮ፣ ሥላቅ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ቅንፍ፣ ወዘተ. በተገቢ ስፍራቸው እያስገቡ መጻፍ፣
- በትምህርት ቤታቸው የሚካሄዱ ስብሰባዎችንና ውይይቶችን ቃለ ጉባኤ መያዝ፣
- በሚሰጧቸው ርዕስ ጉዳዮች ላይ ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን በማግኘት /በማሰባሰብ/ የሃሳብ ፍሰቱን የጠበቀ መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ ያለው አጭር ጽሑፍ መጻፍ፣
- ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ በሚሰጣቸው መስፈርት ጽሑፍ ማረም፣
- የቃል ጽሑፍ መጻፍ፣
- ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ሐሳብን በጽሑፍ መግለጽ፣
- ማስታወሻዎችን አስፋፍተው መጻፍ፣

- አንድን ሀሳብ በተለያዩ ቃላት መግለጽ፣
- አጫጭር ማስታወሻዎችን ማስፋፋት፣ /ገጽ 4/፡፡

ከላይ ከቀረቡት ዝርዝር ሃሳቦች የምንገነዘበው ተማሪዎች 8ኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ በጽሕፈት ክሒል ረገድ ያላቸው ብቃት ከፍተኛ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ በዚህም ሃሳባቸውን በጽሑፍ ለመግለጽ የሚያስችል እውቀት እንደሚኖራቸው ይገመታል፡፡

## 2.7.2 ለስምንተኛ /8ኛ/ ክፍል የተዘጋጀው መርሐ-ትምህርት

በስምንተኛ ክፍል መርሐ-ትምህርት ውስጥም የጽሕፈት ችሎታ ለማዳበር ያበቃሉ ተብለው ከተዘረዘሩት ነጥቦች የሚከተሉት ይገኙበታል፤

- ሥርዓተ-ነጥቦችን በአግባቡ መጠቀም፡- የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ሥርዓተ- ነጥቦችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማድረግ እስካሁን የተማሯቸውን ስርዓተ-ነጥቦች በተለይም ነጠብጣብ፣ ድርብ ሰረዝ፣ ትዕምርተ አንክሮና ስላቅን በተለያዩ ጽሑፎች እያስገቡ ማለማመድ፣ ለቋንቋው ተናጋሪ አዲስ ሆነው ያልተለመዱ ከሌላ ቋንቋ የተወሰዱ ቃላትንና ሀረጎችን በአረፍተ ነገር ውስጥ በጥቅስ ምልክት ለይተው እንዲያስቀምጡ በማለማመድ እንዲጽፉ የማያዙ መመሪያዎች ይገኛሉ፡፡
- በምሳሌና በማስረጃ የዳበረ አንቀጽ መጻፍ፡- ይህን ለማስቻል የሀሳብ ቅደም ተከተላቸው የተዛባ አረፍተ ነገሮችን በማቅረብ በአንድ አንቀጽ አስተካክለው እንዲጽፉ በማድረግ፣ የተለያዩ መንደርደሪያና ዝርዝር ሀሳቦችን አደባልቆ በመስጠት እያንዳንዱን መንደርደሪያ ከነዝርዝሮቹ እንዲለዩና የተለያዩ አንቀጾችን እንዲጽፉ፣ አንድ አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር እንዳለው ሁሉ መደምደሚያ ዓረፍተ-ነገር የሚኖረው መሆኑን ገልጾ ለተለያዩ አንቀጾች መደምደሚያ እንዲሰጡ በማድረግ፣ አንድን ጉዳይ የሚመለከቱ ሁለት ተቃራኒ መንደረደሪያ ዓረፍተ ነገሮችን በመስጠት ሀሳቡን የሚያጎሉ በምሳሌና በመረጃ የተደገፉ ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን እየጨመሩ የተሟላ አንቀጽ እንዲጽፉ ማለማመድ እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡
- የሌላን ሰው ሕይወት ታሪክ መጻፍ፡- ይህን ለማዳበርም የሕይወት ታሪክ ስለሚጻፍለት ሰው በቂና አሳማኝ መረጃዎችን መሰብሰብና ከስሜታዊ አስተያየትና አመለካከት ነጻ ሆነው ተነባቢ የሆነ ጽሑፍ ማቅረብ፣ በግለሰቡ የሕይወት ታሪክ መካተት የሚገባቸውን

ዋና ዋና መሰረቶች በመስጠት እንዲለማመዱ የሚያደርጉ ምሳሌዎች በመስጠት እንዲያለማምዱ የሚያዙ መመሪያዎች ይገኛሉ፡፡

- የተለያዩ ውይይቶችን ቃለ ጉባኤ መያዝ፦ ይህን ለማስቻልም የቃለ ጉባኤ ምንነትና የአዘገጃጀት ሁኔታ እንዲገልጹ በማድረግ ማጠናከር፣ በቃለ ጉባኤ አያያዝ ወቅት ትኩረትን የሚሹ ጉዳዮችን እንዲገልጹ አድርጎ በምሳሌ ማብራሪያ መስጠት፣ የተለያዩ ውይይቶችን በማካሄድ ቃለ ጉባኤዎችን በቡድን እንዲያዘጋጁ በማድረግ ማለማመድ
- ጽሑፍን አርሞ መጻፍ፦ ይህን የጽሕፈት ክህሎት ለማስቻልም ቀደም ብለው የጻፉትን በተመለከተ ከስርዓተ-ነጥብ፣ ከፊደላት ግድፈት፣ ከቃላት ምርጫ፣ ከሃሳብ ውህደት አኳያ ጓደኞቻቸው በሚሰጧቸው አስተያየት መሰረት እንዲያርሙ በማድረግ ማጠናከር፣ የጓደኞቻቸውን ጽሑፍ ካረሙ በኋላ ለማረሚያ የሰጡትን አስተያየት በጽሑፍ እንዲያቀርቡ በማድረግ ማለማመድ የሚሉት በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የጽሕፈትን ችሎታ ለማዳበር ያበቃሉ ተብለው ከተዘረዘሩት ተግባሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 2.7.3 የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት

የአፍ መፍቻ ቋንቋን በመማር ከየክፍል ደረጃው የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃትም ሆነ ለደረጃው በተዘጋጀው መርሐ-ትምህርት ውስጥ የጽሕፈት ክሒል ብቃትን በተመለከተ ከቀረቡት ዝርዝር ጉዳዮች እንደምንረዳው የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በተነባቢ የእጅ ጽሑፍ አንቀጽ፣ ቃለ ጉባኤ፣ የሌላ ሰው የሕይወት ታሪክ በተመረጡ ቃላት፣ ስሜትን ሊያጎሉ /ሊያንጸባርቁ/ የሚችሉ ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀም እና የሐሳብ አንድነት ያላቸው ጽሑፎችን መጻፍ እንደሚችሉ ነው፡፡ ይህ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ደግሞ በተማሪዎቹ መማሪያ መጽሐፍ እና ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን የጽሕፈት ትምህርት ይዘቶች እናያለን፡፡

በስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የጽሕፈት ትምህርት አላማዎችን ከግብ ለማድረስ ይረዳሉ ተብለው ከተጠቀሱት የጽሕፈት ትምህርት ይዘቶች ውስጥ የተለያዩ ዓረፍተ-ነገሮችን በመስጠት ተገቢውን ስርዓተ-ነጥብ እንዲያስቀምጡ ማዘዝ፣ ስዕሎችን በመመልከት ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ አንቀጾችን መጻፍ፣ የሌላን ሰው የሕይወት ታሪክ መጻፍ፣ የግለሰብና የመስሪያ ቤት ደብዳቤ መጻፍ፣ አንድን የተከናወነ ጉዞ በማስደመጥ ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ እና የመስክ ጉብኝት እንዲያካሂዱ በማድረግ ቃለ ጉባኤ መያዝን እንዲለማመዱ የሚያግዙ መልመጃዎችና ጽሑፎች ይገኛሉ፡፡

በማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥም በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የተገለጹትን የጽሕፈት ትምህርት መልመጃዎችና ትዕዛዞች እንዴትና ምን በማድረግ ልምምድ ሊደረግባቸው እንደሚገባ ማብራሪያዎች፣ መመሪያዎችና ሞዴል ጽሑፎች ይገኛሉ።

ከዚህ በላይ ባየናቸው ሰነዶች የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በተነባቢ የእጅ ጽሑፍ ሃሳባቸውን በጽሑፍ ለመግለጽ ምንም አይነት ችግር ሊፈጠርባቸው እንደማይችል በማመን በሊቦ ከምከም ወረዳ የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሃሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከላይ የተዘረዘሩትን ሰነዶች በመመርኮዝ ጥያቄ በማዘጋጀት ያላቸውን የጽሕፈት ክሂል ብቃት ለማወቅ ጥናት ተካሂዷል። በዚህም በተተኳሪው የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ቢያንስ፣ቢያንስ በተነባቢ የእጅ ጽሁፍ፣ በተመረጡ ቃላትና አገላለጾች፣ አስፈላጊውን ስርዓተ ነጥብ በማሟላት በአንድ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን አንቀጽ መጻፍ ይችላሉ ብሎ መገመት ይቻላል።

## 2.8 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የጽሕፈት ክሂልን በተመለከተ በተለያዩ ዘመናት ጥናቶች ተካሂደዋል። በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል ተብለው የተዳሰሱት ቀደምት ጥናቶች የሚከተሉት ናቸው፤

1ኛ.ክፍሌ ሃብተማሪያም (1986)፣ "የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ" በሚል ርዕስ የኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ ጥናት አቅርበዋል። የጥናታቸው አላማ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ አቀናብረው ለመግለጽ ያላቸውን ችሎታ ማጥናት ነው። በመጨረሻም በጥናታቸው የደረሱበት ውጤት ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ ለመግለፅና ጥርት ባለ መልኩ ለማስተላለፍ ተገቢ ቃላትን የመምረጥ፣ ሰዋስዋዊ አገባብን የመጠበቅ፣ ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ የመጠቀም ወዘተ. ችሎታቸው አነስተኛ መሆኑን አመልክተዋል። ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ከክፍሌ ሃብተማሪያም ጥናታዊ ጽሑፍ ጋር የሚያመሳስለው ነገር ጥናቱ ያተኮረው በጽሕፈት ክሒል ብቃት ላይ መሆኑ ነው። በዚህም ተመሳሳይ የሆኑ የጽሕፈት ትምህርት አሳቤዎች እና የጽሕፈት መመዘኛ መስፈርቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ከዚህ ባሻገር ሁለቱ ጥናታዊ ጽሑፎች ያሏቸው መሠረታዊ ልዩነቶች፦

1. የክፍሌ ሃብተማሪያም ጥናታዊ ጽሑፍ ያተኮረው በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ግን በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ መሆኑ፤

2. ሁለቱ ጥናቶች ካሏቸው አላማዎች የተነሳ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶቹም በተወሰነ ደረጃ ልዩነት አሏቸው፡፡ ክፍሌ ሃብተማሪያም የጥናቱን ተተኳሪ ተማሪዎች ዓረፍተ-ነገር እንዲሰሩ እና አንቀጽ እንዲጽፉ በማድረግ መረጃቸውን ሲሰበስቡ በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ግን በናሙና ለተወሰዱት ተማሪዎች አምስት ርዕሶችን በመስጠት አንዱን መርጠው አንቀጽ እንዲጽፉ በማድረግና አምስት ስርዓተ ነጥብ የሌላቸው ዓረፍተ-ነገሮችን በመስጠት ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ እንዲያሟሉ በማዘዝ ነው፡፡

2ኛ.ደረጀ ገብሬ (2007)"የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሃሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? በሦስት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የተደረገ ናሙናዊ ጥናት" በሚል ርዕስ ኢትዮጵያን ጆርናል ኦፍ ኢዱኬሽን ላይ ያሳተሙት ጥናታዊ ጽሑፍ ሌላው ተጠቃሽ ስራ ነው፡፡ የጥናታቸው አላማ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች በደረጃው የሚጠበቅባቸውን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ አዳብረዋል ወይ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው፡፡ በመጨረሻም በጥናታቸው የደረሱበት ውጤት ተማሪዎቹ የሚጠበቅባቸውን ያህል የጽሕፈት ክሂል ብቃት እንደሌላቸው አመልክተዋል፡፡ በዚህም የፊደል ትርጉን ጠብቆ በተነባቢ የእጅ ጽሑፍ ማቅረብ እና አንድ ሃሳብ ያለው የተሟላ አንቀጽ መጻፍ ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸውና የተማሪዎቹ ችሎታ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ከደረጀ ገብሬ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነገር በጽሕፈት ክሒል ላይ ማተኮሩ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን ሁለቱ ጥናቶች ያሏቸው መሠረታዊ ልዩነቶች፡-

የደረጀ ገብሬ ጥናት ያተኮረው በ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ግን በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

ከክፍል ደረጃቸው በተጨማሪ በጊዜና በቦታም የተለያዩ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የተከተለው አይነታዊ የምርምር ዘዴን ሲሆን አቀራረቡም ገላጭ ነው። በዚህ ምዕራፍ ስር ለዚህ ጥናት የተመረጡ አካባቢዎችና ትምህርት ቤቶች፣ የክፍል ደረጃ፣ ተማሪዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነት እንዲሁም መረጃዎቹ የተተነተኑበት ስልት ቀጥለው ይቀርባሉ።

## 3.1 የናሙና አመራረጥ

### 3.1.1 የጥናቱ አካባቢ አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው አካባቢ በአማራ ክልል መስተዳድር ደቡብ ጎንደር ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የሊቦ ከምከም ወረዳ ነው። ከአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ሊቦ ከምከም ወረዳ የተመረጠበት ምክንያት አጥኝዋ ተወልዳ ያደገችበት፣ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ማንኛውንም መረጃ ለማግኘት በማመቸቱ ፣እንዲሁም በዚህ አካባቢ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ጥናት ተደርጎ ባለመገኘቱ ነው።

### 3.1.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል በሊቦ ከምከም ወረዳ ሰባ (70) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ 49 ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ - 4ኛ፣ ከ1ኛ - 5ኛ እና ከ1ኛ- 6ኛ ክፍል የሚያስተምሩ ሲሆን ሃያ አንድ (21) ትምህርት ቤቶች ደግሞ ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ ናቸው። ከእነዚህ ሃያ አንድ (21) ትምህርት ቤቶች መካከል ደግሞ ለትራንስፖርት አመቺ የሆኑ 13 ትምህርት ቤቶች ዝርዝር ከተዘጋጀ በኋላ በቀላል የእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ አራት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። እነዚህም ትምህርት ቤቶች አዲስ ዘመን የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት፣ አላቦ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት፣ አባባዬን የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት እና ይፋግ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ናቸው።

### 3.1.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገበት የክፍል ደረጃ 8ኛ ክፍል ነው፡፡ የክፍል ደረጃው ስምንተኛ ክፍል እንዲሆን የተደረገው አላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ የ8ኛ ክፍል የጥናቱ ማተኮሪያ የሆነውም ተማሪዎቹ የመጀመሪያ ደረጃን ትምህርት በሚያጠቃልሉበት የመጨረሻ እርከን ላይ በመገኘታቸው በጽሕፈት ክሒል ረገድ በደረጃው የሚጠበቀውን ችሎታ ያሟላሉ ተብሎ ስለተገመተ ነው፡፡

### 3.1.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ በተካተቱት አራት ትምህርት ቤቶች ስምንተኛ ክፍልን የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር አነስተኛ ነው፡፡ በዚህም በእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች ከሁለት በላይ መምህራን የሉም፡፡ በአዲስ ዘመን እና በአላባ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለቱ ትምህርት ቤቶች አንድ፣ አንድ መምህራን የተገኙ ሲሆን በአበባዬን እና በይፋግ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለት ትምህርት ቤቶች ደግሞ ሁለት፣ሁለት መምህራን በጠቅላላው ስድስት መምህራን በጥናቱ ተካተዋል፡፡

### 3.1.5 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

የተመረጡት መምህራን ከሚያስምሩባቸው 16 የመማሪያ ክፍሎች መካከል በእጣ ናሙና ¼ የሚሆኑት 4 የመማሪያ ክፍሎች ለጥናቱ ስራ ላይ ውለዋል፡፡ በእነዚህ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች እና የመማሪያ ክፍሎች በእያንዳንዱ ምድብ (ሴክሽን) በአማካይ 45 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ መረጃው በተሰበሰበበት ወቅት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተገኙት የአንድ ሴክሽን (ክፍል) ተማሪዎች ተወስደዋል፡፡እነሱም በአማካይ 40 ሲሆኑ ከአራቱ ትምህርት ቤቶች 160 ተማሪዎች በናሙናነት ተመርጠዋል፡፡

ሠንጠረዥ 1፦ የናሙና ትምህርት ቤቶች፣ የመማሪያ ክፍሎችና በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች ብዛት

| ተ.ቁ | የናሙና ት/ቤቶች | የመማሪያ ክፍሎች ብዛት | የተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት | ለናሙና የተመረጡት ክፍሎች | በተጠኝነት የተመረጡት ተማሪዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ ዘመን የመ/ደ/ሙ/ሳ ት/ቤት | 4 | 176 | 1 | 40 |
| 2 | አላቦ የመ/ደ/ሙ/ሳ ት/ቤት | 3 | 117 | 1 | 40 |
| 3 | አበባዬን የመ/ደ/ሙ/ሳ ት/ቤት | 5 | 220 | 1 | 40 |
| 4 | ይፋግ የመ/ደ/ሙ/ሳ ት/ቤት | 4 | 173 | 1 | 40 |
| | ድምር | 16 | 686 | 4 | 160 |

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በሊቦ ከምከም ወረዳ የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ተጠኝ ተማሪዎች በአማርኛ ሃሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። በመሆኑም አጥኝዋ ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት ሁለት ዘዴዎችን ተጠቅማለች። ይኸውም 1ኛ፦ የችሎታ መለኪያ ፈተና ማለትም፦ ስምንተኛ ክፍል ሆነው በናሙናነት የተወሰዱትን ተማሪዎች አንቀጽ ማስጻፍ እና ስርዓተ-ነጥብ የጎደላቸው ዓረፍተ ነገሮችን በመስጠት ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ እንዲያሟሉ በማድረግ ሲሆን 2ኛ፦ ደግሞ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች መምህራንን የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት ነው።

### 3.2.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና

በተተኳሪው የክፍል ደረጃ የሚገኙትን ተማሪዎች ያላቸውን የጽሕፈት ክሒል ብቃት ለማረጋገጥ የተዘጋጀው የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መርጠው የሚጽፉት አንድ አጭር አንቀጽ እና ተገቢ ስርዓተ ነጥብን ማሟላት የሚያስፈልጋቸው አምስት ዓረፍተ-ነገሮችን በማዘጋጀት ለተማሪዎቹ በፈተና መልክ ተሰጥተዋል።

የዚህ ፈተና አዘገጃጀትም በመጀመሪያ የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ እና መርሐ ትምህርቱን በማየት በአጥኝዋ አምስት የሚሆኑ የአንቀጽ ርዕሶች በመምረጥ ተማሪዎቹ ከአምስቱ ርዕሶች ውስጥ አንዱን ብቻ በመውሰድ አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ ተደረገ። እንዲሁም አምስት ስርዓተ ነጥብ የሌላቸው ዓረፍተ-ነገሮችን በመስጠት ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታቸው እንደሚሏሉ የሚያዙ ጥያቄዎች ተሰጡ። እነዚህ ፈተናዎች ቀደም ሲል በአማካሪ መምህርና በሌሎች የድሕረ ምረቃ ተማሪዎች ተገምግመው ፈተናው ለታቀደላቸው ተማሪዎች ታድለዋል።

በጥናቱ በተካተቱት ተማሪዎች ፈተናው ተሰርቶ ከተመለሰ በኋላ ጽሑፎቹ የሚታረሙበት ጽሕፈትን የመመዘኛ ነጥቦች ተዘጋጁ።እነሱም፦ መንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገርን በግልጽ ከማቅረብ፣ ከቃላት አመራረጥ፣ መደበኛ ቃል ከመጠቀም፣ ሰዋስዋዊ አገባብን ትክክለኛነት ከመጠበቅ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ ከመጠቀም፣ አንፃር የሚመዘኑ ናቸው። የማረሚያ ቅጹን ለአራሚዎቹ በግልጽ በመንገርና በማስረዳት የረጅም ዓመት የማስተማር ልምድ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህር እና አንድ የድሕረ ምረቃ ተማሪ በእርማቱ ተሳትፈዋል። የሁለቱ አራሚዎች ውጤትም ተቀራራቢነት ያለው በመሆኑ እንዳለ ተወስዷል። ስርዓተ ነጥብ የጎደላቸውን በተማሪዎቹ የተሟሉትን አምስት ዓረፍተ ነገሮችም በአጥኝዋ ታርመዋል።

### 3.2.2 ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የጽሑፍ መጠይቅ ነው። የጽሑፍ መጠይቁ ከተማሪዎች የፈተና ውጤት የተገኙትን መረጃዎች ጥንካሬና ድክመት ለመለየት የሚያግዝ ሲሆን በሦስት ክፍሎች የተከፈለ ነው። በክፍል አንድ ስለመምህራኑ አጠቃላይ መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉ አስር ጥያቄዎችን፣ በክፍል ሁለት አራት አማራጮች ያሏቸው ሃያ ዝግ ጥያቄዎችን፣ እና በክፍል ሦስት ስድስት ክፍት ጥያቄዎችን ናቸው። እነሱም በአማካሪ መምህርና በሁለት የድሕረ ምረቃ ተማሪዎች ተገምግመው የማሻሻያ ሐሳብ ተሰጥተውባቸውና ማስተካከያዎች ተደርገውባቸው በጥናቱ በተካተቱ መምህራን እንዲሞሉ ተደርጓል። በመጠይቆቹም ስለ መማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች፣ ስለመምህራኑ የጽሕፈት ትምህርት አሰጣጥና ትኩረት፣ ተማሪዎቹ ስላላቸው የጽሕፈት ትምህርት ፍላጎትና ብቃት ወዘተ. መረጃ ለማግኘት ተችሏል።

## 3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በሁለቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ማለትም በችሎታ መለኪያ ፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም አጥኚዋ ትንታኔ ሰጥታለች።

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃዎች ትንተናና ውጤት

በምዕራፍ አንድ 1.3 ላይ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሊቦ ከምከም ወረዳ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሃሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። በዚህም መሠረት ይህ ጥናት የሚፈትሻቸው ንዑሳን አላማዎች፡-

- ተማሪዎች የፊደል ቅርጽን በወጉ ጠብቀው በተነባቢ የእጅ ጽሑፍ ሃሳባቸውን ለማቅረብ አለማቅረባቸውን መፈተሽ፤
- በዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ማወቅ፤
- በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን አንቀጽ መጻፍ አለመጻፋቸውን መለየት፤
- ሰዋስዋዊ ስርዓቱንና የሃሳብ ቅደም ተከተልን አስተካክለው መጻፍ አለመጻፋቸውን መለየት፤ የሚሉት ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም በጥናቱ አላማ ለተነሱት ነጥቦች ምላሽ ለመገኘት ከተማሪዎች አንቀጽ የማስጻፍ፤ ተገቢ ስርዓተ ነጥብ ማሟላት እና ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ተተንትነዋል።

## 4.1. ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የጽሑፍ መጠይቁ የመጀመሪያው ክፍል ጥያቄዎች ስለ መምህራኑ ዳራ ለማወቅ የቀረቡ ናቸው። መጠይቁ የታደለው ለናሙናነት በተወሰዱት አራት ትምህርት ቤቶች ሲሆን በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ስድስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል።

ሠንጠረዥ 2፡- የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጾታ | እድሜ | የት/ት ደረጃ | የሰለጠኑበት የት/ት አይነት | | የአገልግሎት ዘመን | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | አቢይ | ንዑስ | 8ኛ ክፍል | ጠቅላላ |
| 1 | ሴ | 28 | የመጀመሪያ ዲግሪ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 3 ዓመት | 8 ዓመት |
| 2 | ወ | 32 | ዲፕሎማ | " | " | 7 ዓመት | 8ዓመት |
| 3 | ወ | 46 | ዲፕሎማ | " | " | 3 ዓመት | 26 ዓመት |
| 4 | ወ | 50 | ዲፕሎማ | " | " | 7 ዓመት | 30 ዓመት |
| 5 | ወ | 50 | ዲፕሎማ | " | " | 1 ዓመት | 30 ዓመት |
| 6 | ሴ | 39 | ዲፕሎማ | " | " | 6 ዓመት | 14 ዓመት |

ከላይ ከቀረበው የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ መግለጫ ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው በናሙና ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍልን ከሚያስተምሩ ስድስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ወንዶች ናቸው። እድሜያቸውን ስንመለከት የሁሉም ተጠኝ መምህራን እድሜ ከ28-50 ባለው ውስጥ እንደሚገኙ መረጃው ይጠቁማል። በጥናቱ የተሳተፉት መምህራን ከአንዲት መምህር በስተቀር ሁሉም የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ ነው። አንዲት መምህር ግን የመጀመሪያ ዲግሪ አላቸው። የሰለጠኑበትን የትምህርት አይነት ስንመለከት ሁሉም አማርኛን በአቢይነት እንግሊዝኛን ደግሞ በንዑስ የትምህርት አይነትነት ያጠኑ ናቸው። የአገልግሎት ዘመናቸውን በምናይበት ጊዜ ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመናቸው ከ8 ዓመት- 30 ዓመት ሲሆን 8ኛ ክፍልን አማርኛ በማስተማር ደግሞ ከ1 ዓመት - 7 ዓመት እንደሆነ መረጃው ይጠቁማል።

በአጠቃላይ የመምህራኑን ዳራዊ ሁኔታ ስንመለከት አብዛኞቹ ዲፕሎማ ቢሆኑም ጠቅላላ የአገልግሎት ዘናቸው 8 ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግሎት ያላቸው በመሆኑ ትምህርቱ የሚሰጠው በቂ ችሎታና የዳበረ ልምድ ባላቸው መምህራን መሆኑን መገመት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 3፡- የመማሪያ መጻሕፍቱ አቀራረብ ጽሕፈትን ለማስተማር እና የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር ያለው ብቃት

| ተ.ቁ | መጠይቅ | መልስ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 1 | የመማሪያ መጽሐፍቱ አቀራረብ ጽሕፈትን ለማስተማር ይረዳል | በአብዛኛው | - | - |
| | | በከፊል | 4 | 66.6% |
| | | በመጠኑ | 2 | 33.3% |
| 2 | በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት | በጣም ከፍተኛ | - | - |
| | | ከፍተኛ | - | - |
| | | መካከለኛ | 3 | 50% |
| | | አነስተኛ | 3 | 50% |

የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን በተመለከተ መምህራኑ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ፡-

የመማሪያ መጻሕፍቱ አቀራረብ ጽሕፈትን ለማስተማር ይረዳል? ተብለው ሲጠየቁ የመለሱት መልስ በከፊል ነው በማለት የመለሱት መምህራን 66.67% ሲሆኑ በመጠኑ በማለት የመለሱት ደግሞ 33.3% ያህል ናቸው። ይህም በከፊል በማለት የመለሱት መምህራን ቁጥር ከፍተኛውን ደረጃ ይዟል። በመጠኑ ይረዳል ካሉት ጋር ሲነጻጸርም 33.3% ያህል ብልጫ አለው። በዚህም የመማሪያ መጽሐፉ ጽሕፈትን ለማስተማር ችግር ያለበት መሆኑን ይጠቁማል።

ከዚህ በተጨማሪም የመማሪያ መጻሕፍቱ የጽሕፈት ትምህርት ይዘትና አቀራረብ አላማውን ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል? ተብለው ለተጠየቁት ከፍት ጥያቄ የሰጡት መልስ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች የጽሕፈት ክሒሎን ለማዳበር ያላቸው ሚና ዝቅተኛ ነው፤ ተስቦሽ ጽሑፎችም የሉትም። በዚህም በስርዓተ ትምህርት ኮሚቴ እና በመምህራን ተገምግሞ እንዲሻሻል አስተያየት ቢሰጥበትም እስካሁን ምንም አይነት ለውጥ እንዳልመጣ ገልጸዋል።

በተራ ቁጥር ሁለት ደግሞ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያላቸውን ብቃት በተመለከተ ለተጠየቁት ጥያቄ መካከለኛ ነው በማለት የመለሱት 50% ያህል ሲሆኑ ከፍተኛ ነው በማለት የመለሱትም በተመሳሳይ 50% ያህሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ መረጃው ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡- የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ጽሕፈትን ለመማርና ክሂሉን ለማዳበር ያላቸው ፍላጎት፤

| ተ.ቁ | መጠይቅ | መልስ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ተማሪዎችዎ የአማርኛን ጽሕፈት ለመማር ያላቸው ፍላጎት | በጣም ከፍተኛ | 1 | 16.67 |
| | | ከፍተኛ | 1 | 16.67 |
| | | በመካከለኛ | 1 | 16.67 |
| | | አነስተኛ | 3 | 50% |
| 2 | ተማሪዎችም የጽሕፈት መልመጃዎችን ለመስራት ያላቸው ፍላጎት | በጣም ከፍተኛ | | |
| | | ከፍተኛ | 1 | 16.67 |
| | | መካከለኛ | 1 | 16.67 |
| | | አነስተኛ | 4 | 66.67 |

የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ጽሕፈትን ለመማርና ክሂሉን ለማዳበር ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ ነው በማለት የመለሱት መምህራን ቁጥር ከፍተኛውን ደረጃ ይዟል፡፡ በጣም ከፍተኛ ነው እና ከፍተኛ ነው በማለት ከመለሱት መምህራን ቁጥር ጋር ሲነጻጸርም ከመቶ 16.67% ያህል ብልጫ አለው፡፡ ስለዚህ ጽሕፈትን ለመማር ያላቸው ፍላጎት በዝቅተኛ ደረጀ ላይ እንዳለ ያብቁማል፡፡

የጽሕፈት መልመጃዎችን ለመስራት ያላቸው ፍላጎት መካከለኛ ነው፣ እና ከፍተኛ ነው በማለት የመለሱት መምህራን ቁጥር እያንዳንዳቸው 16.6 ፐርሰንት የያዙ ሲሆን አነስተኛ ነው በማለት የመለሱት 66.67% ያህል ነው፡፡ በዚህም ጽሕፈትን ለመማርና የጽሕፈት መልመጃዎችን ለመስራት ያላቸው ፍላጎት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ለማለት ያስችላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዎችም ጽሕፈትን ለመማር ወይም ክሒሉን ለማዳበር ያላቸውን ፍላጎት ወይም ዝንባሌ እንዴት ይገልጹታል? ተብለው ለተጠየቁት ክፍት ጥያቄ የሰጡት መልስ የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ፍላጎት እንዳላቸው፣ የቤት እና የክፍል መልመጃዎችንም በጥንቃቄ እንደማይሰሩ ጠቅሰዋል። ከዚህም በተጨማሪ አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመሆኑ የመናቅና የእናውቀዋለን የሚል ምክንያት በመፍጠር ከሌሎች የትምህርት አይነቶች አንጻር ዝቅተኛ ስሜት እና ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል።

በመሆኑም በሚማሩበት ጊዜ የሚይዟቸውን ፍሬ ሀሳቦች በትክክል ስለማይጽፉ መልሰው ለማንበብ ይቸገራሉ። የሺው (1996፣ 16) የተጻፈ ነገር ማለት በኃይሮግሊፊካዊ ነቁጦች የተሞላ ቀስ (በድን ነገር) ነው። ጸሐፊው ጠንቃቃ ካልሆነ በስተቀር፣ ወተት የመሰለው ወረቀት በቀለም ስለተዥጎረጎረ ብቻ መልእክት አይተላለፍም። ምክንያቱም በጽሁፍ ግንኙነት ጊዜ በርከት ያሉ ተግባቦት አዋኪ ጉዳዩች አሉና ነው በማለት የጉዳዩን አሳሳቢነት ያመለክታሉ። በተጨማሪም Norrish (1983) ለስህተቶች መከሰት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፤ ከነዚህም መካከል ተነሳሽነት ማጣትና የማስተማር ዘዴ ድክመቶች ናቸው ከሚሉት ሀሳቦች ጋር ይስማማል።

ሠንጠረዥ 5፦ የሚሰጣቸውን የጽሕፈት ስራ ትኩረት ሰጥተው የመሰራትና እንደገና የማስተካከል ልምድ፣

| ተ.ቁ | መጠይቅ | መልስ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | እርስዎ ጽሕፈትን በተመለከተ የሚሰጧቸውን የክፍልና የቤት ስራዎች ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩት ተማሪዎች ቁጥር | በጣም ከፍተኛ | 1 | 16.67 |
| | | ከፍተኛ | 1 | 16.67 |
| | | መካከለኛ | 4 | 66.67 |
| | | አነስተኛ | - | - |
| 2 | ተማሪዎቹ የጻፉትን ነገር መልሰው የማስተካከል ልምዳቸው | በጣም ከፍተኛ | 1 | 16.67 |
| | | ከፍተኛ | 1 | 16.67 |
| | | መካከለኛ | 1 | 16.67 |
| | | አነስተኛ | 3 | 50 |

የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት መልመጃዎች ትኩረት ሰጥረው የሚሰሩት ተማሪዎች ቁጥር መካከለኛ ነው በማለት የመለሱት ከመቶ 66.67% የሚሆኑት መላሾች ሲሆኑ በጣም ከፍተኛ ነው እና ከፍተኛ ነው ያሉት ደግሞ እያንዳንዳቸው ከመቶ 16.67 ፐርሰንት የሚሆኑት መላሾች ናቸው። በመሆኑም መካከለኛ ብለው የመለሱት በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ነው ብለው ከመለሱት ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ በጣም የጎላ ነው። ስለዚህ የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት መልመጃዎች ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩት ተማሪዎች ቁጥር መካከለኛ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሰናል።

እንዲሁም የጻፉትን ነገር መልሰው የማስተካከል ልምዳቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ መረጃው ይጠቁማል። ይህም በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ እና መካከለኛ ነው በማለት የመለሱት እያንዳንዳቸው 16.67% ያህል ሲሆኑ አነስተኛ ነው በማለት የመለሱት ደግሞ 50% ያህል ናቸው። ይህም አነስተኛ ነው በማለት ከመለሱት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አለው።

Edge (1989:52) መምህሩ ስህተት እንዳለ በመጠቆምና የራሳቸውን ጽሁፍ እንዲያርሙ እድል በመስጠት ተማሪዎቹ የጻፉትን ነገር መልሰው የማስተካከል ልምዳቸውን ማሻሻል እንዲችሉ መርዳት እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል።

ሠንጠረዥ 6፡- መምህራን ጽሕፈትን ለማስተማር የሚያደርጉት ጥረትና የመጻፍ ችሎታቸውን

ለማዳበር የሚያደርጉት እገዛ

| ተ.ቁ | መጠይቅ | መልስ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | እርስዎ ጽሕፈትን ለማስተማር የሚያደርጉት ጥረት | በጣም ከፍተኛ<br>ከፍተኛ<br>መካከለኛ<br>አነስተኛ | 2<br>3<br>1<br>- | 33.3%<br>50%<br>16.67% |
| 2 | የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር የሚረዱ መልመጃዎችን ይሰጣሉ? | ሁል ጊዜ<br>አብዛኛውን ጊዜ<br>አልፎ አልፎ<br>በጥቂቱ | 3<br>2<br>1<br>- | 50%<br>33.3<br>16.67<br>- |
| 3 | የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ወይም ለማዳበር የሚያደርጉት ድጋፍ | በጣም ከፍተኛ<br>ከፍተኛ<br>መካከለኛ<br>አነስተኛ | -<br>4<br>2<br>- | -<br>66.67<br>33.3<br>- |

መምህራን ጽሕፈትን ለማስተማር የሚያደርጉትን ጥረት በተመለከተ ለተጠየቀው ጥያቄ ከፍተኛ ነው በማለት የመለሱት 50% ፣ በጣም ከፍተኛ ነው በማለት የመለሱት 33.3% ያህል እና በመካከለኛ ደረጃ ጽሕፈትን ለማስተማር ጥረት እናደርጋለን ያሉት ደግሞ 16.67 ያህል ናቸው።

በሌላ መልኩ የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር የሚረዱ መልመጃዎችን ይሰጣሉ? ተብለው ለተጠየቁት የሰጡት መልስ 50% ያህሉ ሁል ግዜ፣ 33.3% ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ እና 16.67% አልፎ አልፎ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ወይም ለማዳበር የሚያደርጉትን እገዛ በተመለከተ ለተጠየቁት ጥያቄ ከፍተኛ ነው በማለት የመለሱት 66.67% ያህል ሲሆኑ መካከለኛ ነው በማለት የመለሱት ደግሞ 33.3% ያህል ናቸው። በአጠቃላይ መምህራን ጽሕፈትን ለማስተማር የሚያደርጉትን ጥረትና የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት እገዛ ጥሩ እንደሆነ ከመረጃው ማየት ይቻላል።

Pollington and et al.(2001) እንደሚገልፁት የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል ለማዳበር በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ እንዲጽፉ ማድረግ ይገባል። በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ሁሉም መምህራን ተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሒላቸውን እንዲያዳብሩ እድሉን ማመቻቸትና ማበረታታት አለባቸው በማለት ይገልጻሉ። በዚህም መምህራን የተማሪዎችን የዕህፈት ክሒል ለማዳበር የሚያደርጉትን እገዛ ያበረታታል።

ሠንጠረዥ 7፦ መምህራን ጽህፈት ተኮር ተግባራትን ለማለማመድ የሚያደርጉትን እገዛ

| ተ.ቁ | መጠይቅ | መልስ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ለተማሪዎች ስለ አማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ተግባራዊ ልምምድ ያደርጋሉ? | ሁል ጊዜ | 2 | 33.3% |
| | | አብዛኛውን ጊዜ | 3 | 50% |
| | | አልፎ አልፎ | 1 | 16.67% |
| | | በጭራሽ | - | - |
| 2 | ተማሪዎችዎ ስለ አንቀጽ አጻጻፍ ስርዓት ተግባራዊ ልምምድ ያደርጋሉ? | ሁል ጊዜ | 2 | 33.3% |
| | | አብዛኛውን ጊዜ | 2 | 33.3% |
| | | አልፎ አልፎ | 2 | 33.3% |
| | | በጭራሽ | - | - |
| 3 | ለተማሪዎችዎ የቃላትን ምርጫና አጠቃቀምን በተመለከተ ተግባራዊ ልምምድ ያደርጋሉ? | ሁል ጊዜ | 3 | 50 % |
| | | አብዛኛውን ጊዜ | 1 | 16.67 % |
| | | አልፎ አልፎ | 2 | 33.3 % |
| | | በጭራሽ | - | - |
| 4 | ለተማሪዎችዎ የተለያዩ የሥርዓተ ነጥቦችን አገልግሎት እና አጠቃቀም ያለማምዳሉ? | ሁል ጊዜ | 3 | 50% |
| | | አብዛኛውን ጊዜ | 2 | 33.3% |
| | | አልፎ አልፎ | 1 | 16.67% |
| | | በጭራሽ | - | - |

በሰንጠረዥ 7 እንደሚታየው መምህራኑ ጽሕፈት ተኮር ተግባራትን ለማለማመድ የሚያደርጉትን ጥረት በተመለከተ የሰጡትን ምላሽ በምናይበት ጊዜ ስለ ሰዋስዋዊ ስርዓት አልፎ አልፎ እንደሚያለማምዷቸው የገለጹት 16.67% ያህል፣ አብዛኛውን ጊዜ እናለማምዳቸዋለን ያሉት ደግሞ 50% ያህል እና ሁል ጊዜ እናለማምዳቸዋለን ያሉት ደግሞ 33.3% ያህሉ ናቸው፡፡

ተማሪዎችን ስለ አንቀጽ አጻጻፍ ስርዓት ተግባራዊ ልምምድ ያደርጋሉ? ተብለው ለተጠየቁት አብዛኛውን ጊዜ እና ሁልጊዜ ልምምድ እናደርጋለን ያሉት እያንዳንዳቸው 33.3% ያህል ሲሆኑ አልፎ አልፎ በማለት የመለሱትም እንዲሁ 33.3% ያህል ናቸው።

የቃላት ምርጫና አጠቃቀምን በተመለከተ አልፎ አልፎ ልምምድ እናደርጋለን በማለት የመለሱት 33.3%፣ አብዛኛውን ጊዜ ልምምድ እናደርጋለን ያሉት 16.67% ያህል እና ሁል ጊዜ እናለማምዳቸዋለን ያሉት ደግሞ 50% ያህል ናቸው።

በመጨረሻም የተለያዩ የሥርዓተ ነጥቦችን አገልግሎትና አጠቃቀምን በተመለከተ ሁል ጊዜ ተግባራዊ ልምምድ እናደርጋለን በማለት የመለሱ 50%፣ አብዛኛውን ጊዜ 33.3% እና አልፎ አልፎ ልምምድ እናደርጋለን በማለት የመለሱት ደግሞ 16.67% ያህል ናቸው።

በአጠቃላይ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጉት ጽህፈት ተኮር ልምምድ ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል።

ሠንጠረዥ 8፦ ተማሪዎቹ አንቀጽና ዓረፍተ-ነገር በሚጽፉበት ጊዜ ጎልተው የሚታዩ ስህተቶች

| መለስ | መጠይቅ | | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ተማሪዎቹ ዓረፍተ-ነገር በሚሰሩበት ጊዜ ጎልተው የሚታዩት ስህተቶች | - ተስማሚና ተገቢ የሆኑ ቃላት አለመጠቀም | 1 | 16.67% |
| | | - በቋንቋው ህጎችና ስርዓተ ነጥቦች በአግባቡ አለመጠቀም | 2 | 33.3% |
| | | - አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላትና ሀገጋት መደጋገም | 1 | 16.67% |
| | | - የቃላትን ወይም የሀገጎችን አገባብ ጠብቀው አለመጻፍ | 2 | 33.3% |
| 2 | ተማሪዎቹ አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ ጎልተው የሚታዩ ስህተቶች | - የሀሳብን አንድነት አይጠብቁም | 1 | 16.67% |
| | | - በአንቀጽ ውስጥ ያሉት ዓ.ነገሮች የአንቀጹን ዋና ሀሳብ ብቻ እንዲያብራሩ አድርጎ አለመጻፍ | 1 | 16.67% |
| | | - የአንቀጹን ሀሳብ ተያያዥነት እንዲኖረው አለማድረግ | 1 | 16.67% |
| | | - በቋንቋው ህጎችና ስርዓተ ነጥቦች በአግባቡ አለመጠቀም | 3 | 50% |

ተማሪዎቹ አንቀጽና ዓረፍተ ነገር በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በተመለከተ ለተጠየቁት ጥያቄ፦ ተማሪዎች ዓረፍተ ነገር በሚሰሩበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ብዙ

ቢሆኑም ጎልተው የሚታዩትን ስህተቶች ለመጠቆም ሞክረዋል። በዚህም ተገቢና ተስማሚ ቃላትን አይጠቀሙም በማለት የመለሱት 16.67%፣ በቋንቋው ህጎችና ስርዓተ ነጥቦች አይጠቀሙም ያሉት 33.3%፣ የቃላትና ሀረጋት መደጋገም 16.67% እና የቃላትን ወይም የሀገጎችን አገባብ ጠብቀው አይጽፉም በማለት የመለሱት ደግሞ 33.3% ያህል ናቸው። ይህ አሀዝ ከተሰጡት አማራጭ ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ስህተቶችን የሚወክል ይሁን እንጅ ተማሪዎቹ ዓረፍተ ነገር በሚሰሩበት ጊዜ ከነዚህ ውጭ ሌላ ካለ ይጠቀስ በሚል በተተወ ክፍት ቦታ የመለሱት ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽን አስማምቶ ያለመጠቀም ችግር እንዳለባቸው በተጨማሪነት ገልጸዋል።

በሠንጠረዥ 8 ተራ ቁጥር 2 ተማሪዎቹ አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ ጎልተው የሚታዩ ስህተቶችን በተመለከተ ለተጠየቁት ጥያቄ የመለሷቸው መልሶች የሀሳብን አንድነት አይጠብቁም በማለት የመለሱት 16.67%፣ በአንቀጽ ውስጥ ያሉት ዓረፍተ ነገሮች የአንቀጹን ዋና ሀሳብ ብቻ እንዲያብራሩ አድርጎ አለመጻፍ 16.67% ፣ የአንቀጹን ሀሳብ ተያያዥነት እንዲኖረው አለማድረግ እንዲሁ 16.67% እና በቋንቋው ህጎችና ስርዓተ ነጥቦች አለመጠቀም በማለት የመለሱት 50% ያህል ናቸው። በዚህም ተጠኝ ተማሪዎቹ አንቀጹና ዓረፍተ ነገር በሚጽፉበት ጊዜ ጎልተው የሚታዩት ስህተቶች ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ በቋንቋው ህጎችና ስርዓተ ነጥቦች አለመጠቀም ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል።

ይህን በተመለከተ Fenton, (2003) በጽሑፍ የሚቀርብ ሀሳብ ተቀባይነት የሚኖረው ለማስተላለፍ የሚፈለገውን መልዕክት ለማንፀባረቅ የሚችሉ ቃላት መርጦ በመጠቀም፣ አያያዥና አቀናብሮ በትክክል የመግለጽ፣ የማስረዳት ወዘተ. ችሎታ ሲኖር ነው። እንዲሁም ማንኛውም ጽሑፍ የሚገነባው ቃላትን በሀረግ፣ ሀረጎችን በዓረፍተ-ነገርና ዓረፍተ-ነገሮችን በአንቀጽ አቀናብሮ በማቅረብ ስለሆነ ዓረፍተ-ነገርና አንቀጽ የመጻፍ ልምድን ማጎልበት ይገባል በማለት ይገልጻሉ።

ከዚህ በተጨማሪ በክፍል ሦስት ተማሪዎቹ አንቀጽና ዓረፍተ-ነገር በሚጽፉበት ጊዜ ለማፈጸሟቸው የተለያዩ ስህተቶች ዋንኛ ምክንያቶች ናቸው የሚሏቸውን ይግለጹ? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት መልስ ባለፉት የክፍል ደረጃዎች ከክፍል ወደ ክፍል ሲዘዋወሩ በብቃት አለመዘዋወራቸው እንደሆነ አትኩሮት ሰጥተው ጠቅሰዋል።

ሠንጠረዥ 9፦ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸውን የጽህፈት መልመጃዎች የአስተራረም ሁኔታና የተማሪዎቹ ስህተትን የማረም ልምድ

| ተ.ቁ | መጠይቅ | መልስ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | እርስዎ ለተማሪዎችዎ የሚሰጧቸውን የጽሕፈት መልመጃዎች ተከታትለው ያርማሉ? | ሁል ጊዜ | - | - |
| | | አብዛኛውን ጊዜ | - | - |
| | | አልፎ አልፎ | 4 | 66.67% |
| | | በጥቂቱ | 2 | 33.3% |
| 2 | እርስዎ እርማቱን የሚያካሂዱት እንዴት ነው? | - የተማሪዎቹ እርስ በርሳቸው ደብተር እንዲለዋወጡ በማድረግ | 2 | 33.3% |
| | | - ደብተር ሰብስቦ በማረም | 3 | 50% |
| | | - በቡድን ከፋፍሎ ስህተታቸውን እንዲነጋገሩ በማድረግ | 1 | 16.67% |
| 3 | ተማሪዎችዎ የጽሕፈት መልመጃዎችን እንዲሰሩ ሲያደርጉ የጻፉትን ነገር ደጋግመው በማንበብ የተሳሳቱትን በማረም እንደገና ለመጻፍ ያላቸው ልምድ | በጣም ከፍተኛ | - | - |
| | | ከፍተኛ | - | - |
| | | መካከለኛ | 2 | 33.3% |
| | | አነስተኛ | 4 | 66.67% |

በሰንጠረዥ 9 ላይ በግልጽ እንደሚታየው ለተማሪዎች የሚሰጠውን የጽሕፈት መልመጃ ተከታትለው የሚያርሙ መምህራን ቁጥር አነስተኛ ነው። በአሃዝ ሲገለጽም ሁል ጊዜ እና አብዛኛውን ጊዜ የማያርሙ ሲሆን አልፎ አልፎ እናርማለት በማለት መልስ የሰጡት 66.67% ያህል ሲሆን እርማቱን የምንሰጠው በጥቂቱ ነው ያሉት ደግሞ 33.3% ያህል ናቸው። በዚህም መምህራን የተማሪዎቻቸውን የጽሕፈት መልመጃ አያርሙም ወደሚል ድምዳሜ ያደርሰናል።

ከዚህ በተጨማሪ እርስዎ የተማሪዎችን የጽሕፈት መልመጃ የማያርሙ ከሆነ ምክንያቱን ይግለጹ ለሚለው ክፍት ጥያቄ የሰጡት መልስ ሰዋስውን በሚመለከት እንጅ የጽሕፈት ክሂልን

በሚመለከት ተንሳሽነቱ የለኝም፣ የእጅ ጽሑፋቸው አለመነበብ፣ የቋንቋ ስርዓትን ጠብቆ አለመጻፍ ወዘተ. የሚሉ ምክንያቶችን ጠቅሰዋል፡፡

መምህራኑ እልፎ እልፎ ለሚያርሟቸው የጽሕፈት መልመጃዎች እርማቱን የሚያካሂዱበትን ዘዴ ሲጠየቁም የሰጡት መልስ 33.3% ያህሉ የተማሪዎቹን ደብተር እርስ በርስ በማቀያየር፣ 50% የተማሪዎቹን ደብተር ሰብስቦ በማረም እና 16.67% ደግሞ ተማሪዎቹን ከፋፍለው ስህተታቸውን እንዲነጋገሩ በማድረግ እንደሚያርሙ ጠቅሰዋል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ተማሪዎቹ የጻፉት መልመጃ ስህተት መሆኑን ተረድተው የተሳሳቱትን በማረም እንደገና ለማስተካከል ያላቸውን ልምድ በሚመለከት ለተጠየቁት ጥያቄ መካከለኛ ነው በማለት የመለሱት 33.3% ያህል ሲሆኑ 66.67% ያህሉ ደግሞ አነስተኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡

በአጠቃላይ መምህራኑ የተማሪዎቻቸውን የጽሕፈት መልመጃ የማረምና ተማሪዎችም የተሳሳቱትን ጽሑፍ እንደገና ለማስተካከል ያላቸው ልምድ አነስተኛ መሆኑን መምህራን በሰጡት የጽሑፍ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

Celce Murcia (1991) አዘውትሮ የሚጽፍ ተማሪ የሚጽፈውን ይዘት እየከለሰ ይመረምራል፣ የአገላለጽ ስልቱን ያዳብራል፣ የራሱን ሀሳብ ማደራጀት ይማራል፡፡ ነገር ግን ስህተታቸውን ካላረምናቸው በየደረጃው በመጠቆም እንዲያስተካክሉ ካላደረግናቸው የጽሕፈት ክሂልን ማስተማር አመርቂ አይሆንም በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህም ለተማሪዎች የጽሕፈት ክሂል ዝቅተኛ መሆን እንደ ምክንያት የሚጠቀስ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል ለማዳበር በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ እንዲጽፉ የሚያደርግ ልምምድ መኖር አለበት፡፡ በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ሁሉም መምህራን ተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ እድሉን ማመቻቸትና ማበረታታት አለባቸው፡፡ ገንቢ የሆነና አስተማሪ ሂስ በመስጠት ተማሪዎቹ ከስህተታቸው እንዲማሩ ማድረግ ዋናው የመምህራን ግዴታ እንደሆነ (pollington and et al. 2001) ይገልጻሉ፡፡ በዚህም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ስህተታቸውን መጠቆም ካልቻሉ የተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሂል ብቃት እንደማይጎለብት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከመጠይቁ የተገኘው ውጤት ተማሪዎቹ ዓረፍተ ነገርና አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ በቋንቋው ህጎችና ስርዓተ ነጥቦች አለመጠቀም፣ ተገቢ የሆኑ ቃላት አለመምረጥ፣ የሰዋስው

አገባብ ስህተት፣ ሀሳብን ወስኖና አቀናብሮ መግለጽ ያለመቻል ችግራቸው የጎላ እና አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንዳለ መረጃዎቹ ይጠቁማሉ።

ከዚህ በተጨማሪ መምህራንም የጽሕፈት ክሒልን ለማስተማርና ተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሒላቸው የዳበረ እንዲሆን የሚያደርጉት እገዛ በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መረጃው የሚጠቁም ሲሆን የተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሒልም ሆነ አጠቃላይ አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ግን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከመጠይቁ ለመረዳት ተችሏል።

ሆኖም ከመጠይቁ የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛ ናቸው ብሎ ለመቀበል የተጠኝ ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ መለካት አስተማማኝ መረጃ ይገኝበታል ተብሎ ታምኖአል። የችሎታ መለኪያ ፈተናም ለተጠኝ ተማሪዎች ተሰጥቷል። ከመጠይቁ የተገኘውን ውጤት ለተማሪዎቹ ከተሰጠው የመጻፍ ፈተና ጋር ውጤቱ ተገናዝቦ ሲቀርብ የመረጃውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ይረዳል። ከዚህ በመቀጠል የተማሪዎቹን የፅሁፍ ፈተና እናያለን።

## 4.2. ከተማሪዎች የችሎታ መለኪያ ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.2.1. አንቀጽ

አንቀጽ ስለ አንድ ሃሳብ ብቻ የሚያወራ አንድ ሃይለ ቃል ያለው እና ሌሎች ዓረፍተ ነገሮች ሃይለ ቃሉን የሚደግፉና የሚያብራሩበት የጽሑፍ አነስተኛ ክፍል መሆኑ ይታወቃል።

አንቀጽን በጽሑፋችን ውስጥ የምንጠቀምበትን ምክንያት በተመለከተ ክለሳ ድርሳን ውስጥ እንደተገለፀው የአንባቢ ዓይን ድካም እንዳይሰማው እና በቅደም ተከተል የሚቀርቡት ሀሳቦች የተለየ ቦታ እንዲራቸውና በሌላ ፍሬ ሀሳብ ጣልቃ ገብነት ሳይድፈነፈኑ በሚገባ ዳብረውና ጎልተው እንዲወጡ ለማድረግ ነው

#### 4.2.1.1. የነጥብ አሰጣጥና የውጤት አቀራረብ ስልት

ተጠኝ ተማሪዎቹ የጻፏቸው አንቀጾች የተመዘኑትና ነጥብ የተሰጠው የሚከተሉትን መስፈርቶች በማውጣት ነው። ይኸውም፦

- የአጻጻ ጽሑፍ ተነባቢነት፣
- ለማስተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ መንደርደሪያ እና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይቶ ማቅረብ፣

- የሰዋስውን አገባብ ትክክለኛነት የመጠበቅ፣
- በስርዓተ ነጥቦች በአግባቡ የመጠቀም፣
- በአንቀጹ ለማቅረብ የተፈለገውን ሀሳብ በቃላት አመራረጥና በዓረፍተ ነገር አስካክ ሳይደበዝዝ በትክክል የማስተላለፍ እና
- በአንቀጹ ለማቅረብ የተፈለገውን ሀሳብ ከዋና ወደ ዝርዝር ወይም ከዝርዝር ወደ ዋና ሀሳብ በመሔድ ቅደም ተከተላዊ አኪሔድ የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህን ስድስት መስፈርቶች መሠረት በማድረግ የተጠኙ ተማሪዎቹን የአንቀጽ ውጤት ለማውቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የእያንዳንዱን አንቀጽ ውጤት አባሪ ላይ ማየት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 10፡፡ የአንቀጾቹን ብዛትና የአቀራረብ ስህተት አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ

| የናሙና ተማሪዎች ብዛት | የአንቀጾች ብዛት | የሀሳብ አንድነት የሌላቸው | የቅንብር ጉድለት ያለባቸው | የስርዓተ ነጥብ አለመሟላት የሚታይባቸው | ተያያዥነት የጎደላቸው | የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ | ሰዋስዋዊ አገባብ ያልጠበቁ | የሀሳብ ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 160 | 153 | 11 | 19 | 92 | 27 | 47 | 10 | 45 |

አንቀጽ እንዲጽፉባቸው ከተሰጡት ርዕስ ጉዳዮች መካከል አንዱን በመምረጥ ከተጻፉት አንቀጾች መረዳት እንደሚቻለው የተጠኙ ተማሪዎቹ ከፍተኛ ችግር የሆነው የስርዓተ ነጥብ አለመሟላት ሲሆን ይህም ከ153 ተማሪዎች ውስጥ 92 ተማሪዎች ስርዓተ ነጥብን በአግባቡ መጠቀም ያልቻሉ ናቸው፡፡ የዚህም ስሌት 0.60 ነው፣ ከዚህ በተጨማሪም በአንቀጾቹ ላይ በከፍተኛ ደረጃ የታየው ስህተት የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ ነው፡፡ ይህም 47/153 ከአንድ መቶ ሃምሳ ሶስት አርባ ሰባት ያህል ሲሆን የዚህም ስሌት 0.55 ነው፡፡

ለትንተና የቀረቡት አንቀጾች የተመረጡትም ፣ ከመቶ ሃምሳ ሶስት አንቀጾች ውስጥ ሃያ ስምንት ያህሉ የማይነበቡ በመሆናቸው ተወግደዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የተወሰኑትን አባሪ 4 ላይ መመልከት ይቻላል፡፡ ከቀሩት መቶ ሃያ አምስት አንቀጾች ውስጥ ሃያ አምስት ፐርሰንቱን (25%) ለመውሰድ ብድግ ብድግ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም 32 (ሰላሳ ሁለት) አንቀጾችን በናሙናነት መውሰድ ተችሏል ፡፡

ጠቅለል ባለ ሁኔታ እንዲህ ካየን የተጠኝ ተማሪዎቹ አንቀጽ የመጻፍ ችሎታ የቱን ያህል እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት አንቀፆች ናሙናነት ዝርዝር ጉዳዮችን በመመርመር በእያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ ጎልተው የሚታዩትን ስህተቶች እንመለከታለን።

### 4.2.1.2 የፊደል ገድፈት፣የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ የሚታይባቸው አንቀጾች ትንተና

አንቀጽ 1



ይህ አንቀጽ ከሁለት ረጃጅም እና ከሦስት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች የተዋቀረ ሲሆን የፊደልና የቃላት ገድፈት፣ የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ ጎልቶ ይታይበታል። በአንቀጹ ውስጥ የሚታዩት ስህተቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

ይህ አንቀጽ በርዕሱ መጻፊያ ላይ ርዕሱ ከተጻፈ በኋላ አንቀጹ በአዲስ መስመር "በመጀመሪያ ጊዜ ትምህርቱን ሲጀምር በአቅራቢያ ካለው የቆሎ አስተማሪ ባለበት ትምህርት ይጀምራል..." በማለት ተጽፏል። በዚህ በመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ያለው ባለበት ማን ነው? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። በእርግጥ ባለቤቱ "የቆሎ ተማሪ" እንደሆነ ከርዕሱ ለመገንዘብ ቢቻልም አንቀጹ ሲጀመር ግን "የቆሎ ተማሪ" የሚለው ቃል መፃፍ ነበረበት። በዚህም የቃላት ግድፈት የታየ ሲሆን ይህ ቃል በመገደፉ ምክንያትም የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ብቻ ሳይሆን የአንቀጹ ሀሳብ በሙሉ የተሟላ አይደለም።

የፊደል ገድፈትን በተመለከተም "ትምህርቱን ሲጀምር፣ ትምህርት ይጀምራል፣ በስማምን፣ ናትተከን፣ ካወቀ፣ እደዚ እያለ" የሚሉት ቃላትና ሀረጋት ከአንቀጹ ላይ ማየት እንደሚቻለው የፊደላትን ቅጥያ መተው /የፊደላት ትክክለኛ ቅርፅ አለመያዝ/ እና የፊደላት ግድፈት ችግሮች

ይታዩበታል። ለምሳሌ፡- የፊደላት ግድፈትን ብናይ "በስመአብ" ለማለት "በስማም"፣ "ነአኩተከ" ለማለት "ናኩተከ"፣ "እንዲህ ወይም እንደዚህ" ለማለት "እደዚ" ተብሎ የተጻፉትን ማስተዋል ይቻላል።

የቃላት ምርጫን በተመለከተም "የቆሎ አስተማሪ" ከሚባል "የአብነት መምህር" ቢባል የተሻለ በመሆኑና "የቆሎ አስተማሪ" የሚባል ባለመኖሩ የቃላት ምርጫ ስህተት ታይቶበታል።

በመጨረሻም ድግግሞሽን በተመለከተም በዚህ አጭር አንቀጽ ውስጥ "ትምህርቱን ሲጀምር" የሚለው ሀረግ ሁለት ጊዜ፣ "ከዚያም" የሚለው ቃል ሁለት ጊዜ እና "ይማራል" የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ፣ ተደጋግመዋል። እነዚህ የተደጋገሙ ቃላትና ሀረጋት አግባብነት የሌላቸው ሲሆን በሌላ ቃል በመተካት እና ድግግሞሹን በማስወገድ ማስተካከል የሚቻል ሲሆን ለምሳሌ፡- "ይማራል" የሚለውን ቃል ድግግሞሽ ለማስወገድ በመጀመሪያ በስመአብን፣ በመቀጠልም ነአኩተከን ይማራል በማለት ማስተካከል ይቻላል።

አንቀጽ 2



በዚህ አንቀጽ ስለ እናት እርግዝና፣ ጡት ማጥባት ለመግለጽ የተሞከረ ሲሆን ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦች ለይቶ ማቅረብ ያልተቻለበት ጽሁፍ ነው።

የፊደል ግድፈትን በምናይበት ጊዜ ከላይ በአንቀጽ 2 ላይ ማየት እንደሚቻለው "እርግዛ፣ የምታሳድግ፣ በደንብ፣ እንዳይርባቸው፣ እየተቆጣጠረች፣ እንዳያመን" የሚሉትን ቃላት ብንመለከታቸው የአማርኛ ፊደል ናቸው? አይደሉም? የሚለውን ለማወቅ ያስቸግራል። የእነዚህ ፊደላት ትክክለኛ ትርጓሜውን አለመያዝም በአንቀጹ ላይ የሚፈጥረው የተነባቢነት ችግር በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪም "የምታሳድግ" የሚለው ቃል በዚህች አንቀጽ ውስጥ አራት ጊዜ፣"በደንብ" የሚለው ቃል ሶስት ጊዜ በመደጋገማቸው አንቀጹ አሰልችና መልዕክቱም የደበዘዘ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

አንቀጽ 3



ይህ አንቀጽ በሚጻፍበት ጊዜ ማስተሳሰሪ የተፈለገውን ሀሳብ ቅደም ተከተል የጠበቀ አይደለም፡፡ ሲጀምር "እናት ማለት ከእጇ ማር ያላት ከደረቷ ወተት ያላት ስትሆን..." ከተባለ በኋላ ሀሳቡ ሳይቋጭ በመካከል ወደ ሌላ ዓረፍተ ነገር በመሔድ ከልጅነት ጀምሮ አጥብታ፣ አጥባ፣ እኔን አዝላ ወጥ ሰርታ አሳድጋኛለች" በማለት ይቀጥላል፡፡

አንቀጹ በተተኳሪነት የፊደላትን ትክክለኛ ቅርጽ አለመያዝ፣ የቃላት ምርጫ ስህተት እና ድግግሞሽም ይታይበታል፡፡

የፊደላትን ትክክለኛ ቅርጽ አለመያዝን በተመለከተ "እናት ማለት ከእጇ" በሚለው ሀረግ "ጇ"፣ "አሳድጋኛለች" በሚለው ቃል "ኛ"፣ "የምትጠላ" በሚለው ቃል ውስጥ ደግሞ "የ" እና "ላ" ትክክለኛ ቀርጻቸውን ያልያዙ ናቸው፡፡

የቃላት ምርጫ ስህተትን በተመለከተም "ከደረቷ ወተት ያላት" የሚለው ቃል ትክክል አይደለም፡፡ ስለ እናት ገለጻ የሚደረግ ከሆነ ወተት ያላት ከጡቷ እንጅ ከባዶ ደረቷ ላይ አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር የቃላት ምርጫ ስህተት እንዳለም በአንቀጹ ውስጥ የሚታይ ነው፡፡

ድግግሞሽን በተመለከተ ደግሞ በዚህ አንቀጽ ውስጥ "እናት" የሚለው ቃል አራት ጊዜ፣ "ልጆቿ" የሚለው ቃል ሁለት ጊዜ እና "ቢሰድቧት" የሚለው ቃል ደግሞ ሁለት ጊዜ ተደጋግመዋል፡፡

በአጠቃላይ ይህ አንቀጽ የፊደላት ተከከለኛ ቅርጻቸውን ጠብቀው አለመጻፍ፣ የቃላት ምርጫ ስህተት እና ድግግሞሽ እንዲሁም ለማቅረብ የተፈለገውን ሀሳብ ቅደም ተከተላዊ ሂደት በማቀበት አንቀጹ ተነባቢ እንዳይሆንና የሀሳብ ፍሰቱን እንዳይጠብቅ በማድረግ ተፅዕኖ ያሳደሩ ችግሮች ሆነው ታይተዋል።

አንቀጽ 4



በዚህ አንቀጽ በርካታ ርዕስ ጉዳዮችን ለማንሳት የተሞከረ ሲሆን እነዚህም፡- ባህል፣ ወግ፣ ጨዋታ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ልምድ፣ ወዘተ. ናቸው። ይሁን እንጅ የተለያዩ ርዕሶችን በማንሳት ስለ አንዱ ርዕስ ጉዳይ እንኳን ደጋፊና አብራሪ ዓረፍተ ነገሮች ሳይኖሩት ወደ ሌላ ርዕስ ጉዳይ ይሸጋገራል። ለምሳሌ፡- ስለ ባህልና ወግ ለማተት ይፈልግና በመካከል ሀሳቡን ሳይቋጭ ወደ መልክዓ ምድራዊ ገጽታ ይሸጋገራል። የሀሳቡ ፍሰትም ቅደም ተከተላዊ ተዋረድን የጠበቀ አይደለም።

ይህ አንቀጽ የተመረጠው የፊደል ግድፈት፣ የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽን ለማሳየት ታስቦ በመሆኑ ወደዚያው እንለፍ።

የፊደል ግድፈትን በምናይበት ጊዜ "ማዕረግ" ለማለት "ማረግ" ተብሎ የተጻፈውን ማየት ይቻላል።

የቃላት ምርጫን በተመለከተ ደግሞ "ሀገር የተለያዩ የጸታ ልዩነት እና አንድነት ያላቸውን ቤተሰቦች አቅፋና አጥብቃ" በመባል የተጻፈውን ስንመለከት "አጥብቃ" ምንን ለመግለጽ ታስቦ እንደገባ ግልጽ አይደለም። በተጨማሪም በአንቀጹ የመጨረሻ መስመር ላይ "አሻራ፣ አቅፋ፣ መገቢ" የሚሉት ቃላትም እንዲሁ በአንቀጹ መተሳሰፍ ስለተፈለገው መልዕክት ምን ለማለት ተፈልጎ እንደገቡ ግልጽ አይደለም። የእነዚህ ያልተፈለጉ ቃላት መኖር የአንቀጹ ሀሳብ ግልጽና ጥርት ያለ እንዳይሆን እንቅፋት ፈጥረዋል።

ድግግሞሽን በተመለከተ ደግሞ "ስርዓት" የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ፣ "ያላቸው" የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ፣"እናት ሀገር" የሚለው ሀረግ ሁለት ጊዜ፣"ሀገር ማለት" የሚለው ሀረግም ሁለት ጊዜ በመደጋገም ይህን አንቀጽ ድሪቶ ያስመሰሉ ቃላትና ሀረጋትን አይተናል። እነዚህ የተደጋገሙ ቃላትና ሀረጋት አንቀጹን ድሪቶ ከማስመሰላቸውም በተጨማሪ የአንቀጹ ሀሳብ ለሁለት የተከፈለ እንዲመስል ማለትም የሀሳብ አንድነት የሌለው እና የትርጉም /የፍቺ/ ለውጥ እንዲያመጣ በማድረግ በአንቀጹ ላይ ያሳደሩትን ጫና መመልከት ይቻላል።

አንቀጽ 5



ይህ አንቀጽ ስለ ሀገር ለማተት ተፈልጎ እንደተጻፈ ከርዕሱ ለማወቅ ይቻላል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የቃላትና ሀረጋት ድግግሞሽ ጎልቶ የሚታይ ሲሆን ለማስተላለፍ ስለተፈለገው ሀሳብ መንደርደሪያና ዝርዝር ሀሳቦች ለይቶ ማቅረብ ያልተቻለበት አንቀጽ ነው። ለምሳሌ፡- "የሰላም

ተምሳሌት፣ የንጸንት እርግጥ ከተባለ በኋላ "የድል ሰራዊት የሰፈነባት" በማለት የተለያዩ ሀሳቦችን በአንድ ላይ በማጣመር ቀርቧል።

በዚህ ጽሑፍ ዋናው ችግር የቃላትና ሀረጋት ድግግሞሽ ሲሆን "ኢትዮጵያ ሀገሬ" የሚለው ሀረግ አምስት ጊዜ፣ "ቢሔር ቢሔረሰቦች" የሚለው ሀረግ ደግሞ ሁለት ጊዜ በመደጋገም በተለይ "ኢትዮጵያ ሀገሬ" የሚለው አንቀጹን የብያኔ ድርድር አስመስሎታል።

አንቀጽ 6



ይህ አንቀጽ እናት ለልጆቿ ያላትን አሳቢነት በተመለከተ የተጻፈ ሲሆን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች የተዘበራረቁና የተቆራረጡ ናቸው።

የዚህ ጽሑፍ ሌላው ችግር የፊደላት ግድፈትና ትክክለኛ ቅርጻቸውን አለመያዝ ሲሆን "እናቴን ከራሴ አበልጣታለሁ" የሚለው "ከራሴ" የሚለው ቃል ከአገባቡ ተረዳነው እንጅ ከራሴ የሚለውን ቃል የሚገልጽ አይደለም። "ህይወቴን እሰዋለሁ" ለማለት ተፈልጎ " ህወቴን" ተብሎ የተጻፈ ሲሆን "ይ" የምትለው ፊደል ተገድፋለች። በተጨማሪም "ትምህርት አስገብታ" የሚለው ሀረግም "ትምህርት" ለማለት "ትምህት" ተብሎ በመጻፍ "ር" ፊደልን ግድፈት ማንሳት ይቻላል። እነዚህ የፊደላት ትክክለኛ ቅርጻቸውን አለመያዝ እና ግድፈቶች ለአንድ ጽሑፍ የትርጉም ለውጥ በማምጣት ሊያስከትሉ የሚችሉት ችግር ይህ ነው የሚባል አይደለም።

የቃላት ድግግሞሽን በተመለከተ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "እናቴ፣ ለእናት፣ እናቴን፣ እናት፣ የእናቴ" በማለት "እናት" የሚለውን ቃል አምስት ጊዜ፣ "ውለታዋ" የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ እና "ህይወት" የሚለው ቃል ደግሞ ሁለት ጊዜ የተደጋገሙ ሲሆን የጽሑፉ ሀሳብ ቅንብርና አንድነት የጎደለው እንዲሆን በማድረግ የሀሳብ ተደራሽነቱንና የጽሑፍን ለዛ አደብዝዘውታል።

አንቀጽ 7



ይህ አንቀጽ ስለ ሀገር የተጻፈ ሲሆን የፊደላት ግድፈት፣ ትክክለኛ ቅርፅ አለመያዝ የቃላት ድግግሞሽ፣ የጎረፍተ ነገሮች የቅንብር ጉድለት ወዘተ. ተዝቆ የማያልቅ ችግር ያለበት ጽሑፍ ነው። እነዚህንም ችግሮች ለይቶ ለማሳየት ይቻል ዘንድ አንድ በአንድ ለማየት እንሞክር።

የፊደል ግድፈትና ትክክለኛ ቅርጻቸውን አለመያዝ በምናይበት ጊዜ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ገና ከመጀመሪያው "ኢትዮጵያ" ለማለት "ኢትዮጳያ" ይህም ብቻ ሳይሆን በጽሑፉ ውስጥ "ኢትዮጵያ" ለማለት ፈልገው የተለገጹት ቃላት በተለይ "ጵ" የምትለው ፊደል ትክክለኛ ቅርጿን የያዘች አይደለችም። በመቀጠልም "ድንቅ ድንቅ የታሪክ መገኛ ናት" ለማለት ተፈልጎ "ድንቅ" "ድ" በ "ደ"፣ "ቅ" በ "ቃ" የተገለጹ ይመስላሉ። የታሪክ መገኛ" የሚለው ደግሞ "የትረክ መገኝ" በመባል ተጽፏል።

የቃላትና ሀረጋትን ድግግሞሽን ስናይም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "ሀገሬ ኢትዮጵያ" የሚለው ሀረግ ሦስት ጊዜ፣ "ኢትዮጵያ ሀገሬ" የሚለው ሀረግ ሁለት ጊዜ፣ "ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል ሁለት ጊዜ፣ "ያላት" የሚለው ቃል ሁለት ጊዜ፣ "ናት" የሚለው ቃል እንዲሁ ሁለት ጊዜ በመደጋገም አንቀጹ የቃላትና ሀረጋት መደጋገም የበዛበት እንዲሆን በማድረግ ተያያዥነት እንዲጎለው፣ የሀሳብ አንድነቱን እንዳይጠብቅ፣ በአጠቃላይ የሀሳብ ፍሰቱ የተዘበራረቀ እንዲሆን በማድረግ የአንቀጹ ሀሳብ የተምታታና መልዕክቱ የደበዘዘ እንዲሆን አድርጎታል።

በመጀመሪያው መስመር ላይ "ሀገሬ" የሚለው የአንቀጽ ርዕስ የተጻፈው ከአንቀጹ መግቢያ ጋር ተያይዞ ነው። ይህ ደግሞ "ሀገሬ" የሚለው ቃል ተደጋጋሚ ስለሚሆን በአንባቢ ላይ የመደናገርና ግራ የመጋባት ስሜትን ይፈጥራል።

አንቀጽ 8



ይህ አንቀጽ የእጅ ጽሑፍ ተነባቢነት ያለው ሲሆን የፊደል ግድፈት፣ የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ ጎልቶ ይታይበታል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "ትምህርት ቤት" የሚለው ሀረግ አምስት ጊዜ የተደጋገመ ሲሆን የጽሑፉን መልዕክት ለማስተላለፍ ለተዘረዘሩት ዓረፍተ ነገሮች የተቆራረጠ መሆን በምክንያትነት ይጠቀሳል። ከዚህ በተጨማሪ "እውቀት የሚሸመትበት፣ እውቀት ለመሸመት" የሚሉት ሀረጋት አንድ ሀሳብ ለመግለጽ የገቡ የቃላት ድሪቶዎች ናቸው።

የቃላት ምርጫን ስናይ ደግሞ በአንቀጹ የመጨረሻ መስመር "የቤታችን አመልና ቅማል" የሚል አገላለጽ አለ። በጽሑፍ ቋንቋ ፀያፍ ቃላትን መጠቀም አንባቢ ጽሑፉን እንዳያነብ ስለሚያግደውና ቃላቱን በጽሕፈት ጊዜ መጠቀም የጽሑፉን ለዛና ውበት ስለሚቀንሰው እንዲህ አይነት ቃላትና ሀረጋትን መጠቀም እንደሌለብን ብዙ ጸሐፍት አትኩሮት ሰጥተው ይናገራሉ።

በአጠቃላይ በዚህ አንቀጽ ውስጥ የስርዓተ ነጥብ፣ የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ የሚታይበት ሲሆን የጽሑፉ መልዕክት የተቆራረጠና የሀሳብ አንድነት የጎደለው እንዲሆን አድርጎታል።

አንቀጽ 9




ይህ አንቀጽ ሀገርን በተመለከተ የተጻፈ ሲሆን "ሀገር ማለት" በማለት የሀገርን ብያኔ ለማተት የፈለገ ይመስልና ስለ "ሀገር" የተወሰነ ነገር ከገለጸ በኋላ ስለ ትምህርት አሰጣጥ፣ ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ፣ ምርጥ ዘር ወዘተ. ይገልጻል። በዚህም ይህ አንቀጽ የሀሳብ አንድነት ችግር ይስተዋልበታል። ከዚህ በተጨማሪም የፊደላት ግድፈት፣ የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ ችግር ጎልቶ ይታይበታል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የፊደላት ትክክለኛ ቅርጻቸውን አለመያዝን በተመለከተ በሁለተኛው መስመር "ምስጢር ደብቃ" ለማለት "ሚስጢር ደብቀ"፣ ሦስተኛው መስመር ላይ ደግሞ "ገዴታ" ለማለት "ግደተ"፣ በአራተኛው መስመር "አስከብራ" ለማለት "አስከበና"፣ ስደስተኛው መስመር ላይ ደግሞ "የአስተራረስ" ለማለት "የአስተናንስ" በመባል የተገለጹትን መጥቀስ ይቻላል።

ድግግሞሽን በተመለከተ ደግሞ "ሀገር ማለት" እና "ሀገር ናት" የሚሉት ሀረጋት ሁለት ጊዜ ተደጋግመው እናገኛቸዋለን።

በአጠቃላይ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የፊደላት ትክክለኛ ቅርጻቸውን አለመያዝ፣ የቃላትና ሀረጋት መደጋገም እንዲሁም የጎረፍተ ነገሮቹ በሀሳብ አለመዛመድ ችግር ይስተዋልበታል። የአንቀጹ ሁነብ በጅምር የቀረ ነው ማለትም አልተቋጨም። ስለዚህ የዚህን ጽሑፍ መልዕክት ለመረዳት አስቸጋሪና የተወሳሰበ እንዲሆን ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

አንቀጽ 10



ይህ አንቀጽ የእጅ ጽሑፉ ተነባቢ ቢሆንም የፊደል ግድፈት፣ የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ ችግር ይታይበታል።

የፊደል ግድፈትን በተመለከተ ሁለተኛው መስመር ላይ "... ሀገሬ ለእኔም ሆነ ለሁሉም ሰው" ለማለት ተፈልጎ "ሀገሬ ነኚ ሞሆን ለሁለ ሰው" በመባሉ "ለእኔም" ለማለት "ነኚም" የሚለውን ስህተት ጨምሮ ከፍተኛ የሆነ የፍቺ ለውጥና የሀሳብ መዛባት ችግር ያስከትላል፡፡

ድግግሞሽን በተመለከተ ደግሞ "ሀገር ማለት"፣ "የምንኖርባት"፣ "በሰላም፣ በፍቅር" የሚሉት ቃላትና ሀረጋት ሁለት፣ ሁለት ጊዜ በመደጋገማቸው አንቀጹን ድግግሞሽ የተጠናወተው አስመስለውታል። ድግግሞሽ ትኩረትን በአጽንኦት እንድናየው የሚረዳበት ጊዜ ቢኖርም በዚህ አንቀጽ ውስጥ ግን አላስፈላጊና መልዕክቱን የሚያደበዝዝ ነው፡፡

አንቀጽ 11



ይህ አንቀጽ እናት ለልጆቿ የምታደርገውን እንክብካቤ ለማስረዳት ተፈልጎ የተጻፈ ሲሆን በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀሙ ጥሩ የሚባል ነው። ድክመቶቹንም እንደሚከተለው እንይ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "እንችን ካጣሁ ይርበኛል፣ ይጠማኛል፣ ውስሽ እስከምትገቢ በጣም እናፍቃለሁ" በሚለው አገላለጽ የተሰመረባቸው ቃላት ፊደል ትክክለኛ ቀርጻቸውን ያልያዙ ሲሆን "እስከምትገቢ" የሚለው ደግሞ "እስከ ምትገቢ" ተብሎ በመጻፍ አንዱን ቃል ሁለት እንዲመስልና ሀሳቡ እንዲቆረጥ ሆኗል። በተጨማሪም አራተኛው መስመር ላይ "... እሾህ ቢወጋኝ እኔን ይውጋኝ፣ ብወድቅ እኔ ድፍት ልበል..." የሚለው አገላለጽ ከተራ ንግግር የማይለይ ነው። ሀሳባችን በጽሑፍ በምናስተላልፍበት ጊዜ በተመረጡ ውብና ማራኪ ቃላት መገለጽ ሲኖርብን ይህን ሳናደርግ ከቀረበ አንባቢ የመሰልቸትና ጽሑፉን አንብቦ ላይጨርሰው ይችላል፤ በዚህም ማስተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ሳይተላለፍ ይቀራል ማለት ነው።

አንቀጽ 12


ሀገሬ

ይህ አንቀጽ የሀገርን አኩሪ ባህል መነሻ በማድረግ የተጻፈ ሲሆን የፊደላትን ቅጥያ መተው፣ የፊደላት ግድፈት፣ የስርዓተ ነጥብ፣ የቃላት ድግግሞሽ ችግር ይታይበታል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የፊደል ግድፈትና ቅጥያዎችን የመተው ችግር በከፍተኛ ደረጃ የሚታይበት ሲሆን ዘርዘር አድርገን ስናያቸውም የመጀመሪያው መስመር ላይ "ሀገሬ" የሚለው

"ሬ" አትመስልም። በዚሁ መስመር "ታዋቂ" ለማለት ተፈልጎ የተጻፈውንም ብናየው አስመስሎ ለመጻፍ እንኳን አስቸጋሪ ነው። አሁንም በመጀመሪያው መስመር መጨረሻ አካባቢ "ይህች ሀገር" ለማለት ተፈልጎ "ች" ተብሎ ተጽፏል። ሁለተኛው መስመር ላይም "... አንድ ዓመት በቅኝ ቅዛት ሳትያዝ..." ለማለት "አንድ ዓመት በቅኝ ገዥነት ሳትያዝ" በመባል ተጽፎ እናየዋለን። አምስተኛው መስመር ላይም "አሁንም በርትቼ" ለማለት "አሁንም ተርትቼ"፣ ስምንተኛው መስመር መጀመሪያ ላይ ደግሞ "ሊስትር" ለማለት "ቢስትር"፣ አስራ አንደኛው መስመር ላይም "...አሁን እስክጨርስ..." ለማለት "አሁን እስጨረስ" በማለት የተገለጹትን ማየት በቂ ነው። ድግግሞሹን ስናይም "ሀገሬ ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ የተደገመ ሲሆን አግባብነት የሌለው ነው።

በአጠቃላይ ይህ አንቀጽ ብዙ ችግሮች ቢኖሩበትም የፊደላት ግድፈትና ቅጥያዎችን መተው ችግር ጎልቶ ይታይበታል። በዚህ ችግርም የአንቀጹ ሀሳብ የተቆራረጠና ለአንባቢ አስቸጋሪ ሁኔታን የሚፈጥር ነው።

አንቀጽ 13


ትምህርት ቤት

አንቀጹ ትምህርት ቤት የእውቀት መሰረት እንደሆነ የሚገልጽ ሲሆን የቃላትና የሀረጋት መደጋገም ችግር ጎልቶ ይታይበታል።

ድግግሞሹን ስናይም በዚህች አጭር ጽሑፍ ውስጥ "ትምህርት ቤቱ" የሚለው ሀገር አራት ጊዜ፣ "ስትሆን" የሚለው ቃል አራት ጊዜ፣ "ሃፈጠረች" የሚለው ቃል ሁለት ጊዜ በመደጋገም

ጎልተው ይታያሉ። በአንቀጹ ውስጥ ያሉት ዓረፍተ ነገሮች የተቀናበሩ ቢሆኑ ኖሮ ድግግሞሹ አይከሰትም ነበር። ነገር ግን ዓረፍተ ነገሮች የቅንብር ጉድለት ስላለባቸው እነዚህ ከላይ የተቀጠሱት ቃላትና ሀረጋት ተደጋግመዋል።

ከላይ ያየናቸው አንቀጾች የፊደላት ግድፈት፣የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽን ለማሳየት ተመረጡ እንጂ የቅንብር፣የሃሳብ አንድነት፣ሰዋስዋዊ እና ስርዓተ ነጥብን የተመለከቱ ችግሮች የሉባቸውም ማለት አይደለም።

### 4.2.1.3 የቅንብር ጉድለት የሚታይባቸው አንቀጾች ትንተና

አንቀጽ 14



ትምህርት ቤት ማለት

1. ትምህርት ቤቴ ማለት ከቤተሰቦቼ ጋር ከመረፅኩ ዉ፣ ሁሉ
ትምህርት ቤት ከመጣ፡ እውቀትን፣ የሥነ-ምግባር ትምህርቶ
ስሚችን ማግኘበር፣ የከወቶ ቤተሰቦችን ለማሟሟቅ፣ እንዲሁም
ትምህርት እውቀትን ለማግኘት፣ መምህሮችን፣ ቤተሰቦቼን፣ መንገን
ሀገሬን እና ሕዝቡን ለማስደሰት፣ የልፋት ዋጋን ለመክፈል
እንዲሁም ወደፊት ሀገሬን በተማረ አእምሮ ለማስተዋወቅ ጥረት
አደርጋለሁ።

ይህ አንቀጽ "ትምህርት ቤት ማለት ..." ብሎ ይጀምርና ስለትምህርት ቤት ብያኔ ለመስጠት ታስቦ የተጀመረ ቢመስልም ስለ ብያኔው ምንም የሚገልጽ ነገር ሳይኖር አንቀጹ ተቋጭቷል።

አንቀጹ በሰባት መስመር የተጻፈ ሲሆን ሰባቱም መስመር በአንድ ዓረፍተ ነገር ነው የተጻፈው። እንኳን የመጻፍ ልምዱ ላልዳበረ ሰው ይቅርና የጽሕፈት ብቃት ያለው ሰው እንኳን አንድን አንቀጽ በአንድ ዓረፍተ-ነገር በተዋጣለት መልኩ ለመጻፍ የሚያስቸግር ነው። በመሆኑም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አንድ አንቀጽ በአንድ ዓረፍተ-ነገር በመገለጹ ብቻ ሃሳቡን አደብዝዞታል ማለት ሳይሆን ዓረፍተ-ነገሩ በራሱ ሊጣጣሙና አብረው ሊሔዱ በሚችሉ ቃላትና ሀረጋት እንዲሁም አያያዥ ቃላትን ተጠቅሞ የተጻፈ ባለመሆኑ አንቀጹ የቅንብር ችግር እንዳለበት ማየት ይቻላል።

አንቀጽ 15



ይህ አንቀጽ ስለ ትምህርት ቤት የሚያወራ ሲሆን ከመጀመሪያው ትምህርት ቤት የእውቀት መሰረት እንደሆነ ይገልጽና ከዛ በኋላ ትምህርት ቤትን ህይወት እንዳለው ነገር በመቁጠር “… እንደ እናት እንደ አባት ሳስተማርሽ …” በማለት ከመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር የተለየ ሀሳብ አቅርቧል። የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገርና ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር በሀሳብ የተለያዩ የመሰሉት ደግሞ በአንቀጹ ውስጥ ያሉት ዓረፍተ-ነገሮች ከአንዱ ወደ አንዱ በሚሸጋገሩበት ጊዜ ሊያያይዙ በሚችሉ አያያዦችና ተስማሚ ቃላትን ባለመጠቀም ነው። በመሆኑም ይህ አንቀጽ በውስጡ የያዛቸው ዓረፍተ-ነገሮች እርስ በርስ የተጣጣሙና የተዛመዱ ባለመሆናቸው አንቀጹን መልዕክቱ የደበዘዘ እና ሙሉ መልዕክት ማስተላለፍ የማይችል እንዲሆን አድርጎታል።

አንቀጽ 16



ይህ አንቀጽ ስለ ሀገር የተጻፈ ሲሆን የእጅ ጽሑፉ ተነባቢ ነው። ይሁን እንጂ ብዙ ችግሮች ቢኖሩበትም ጎልቶ የሚታየው የቅንብር ጉድለት ነው።

ይህን ጽሁፍ ከቅንብር አንጻር በምናይበት ጊዜ በስምንት መስመር የተጻፈ ሲሆን ምንም አይነት የማያያዥ ቃላትና አቻ ቃላትን ባለመጠቀሙ አንቀጹን አሰልቺ እንዲሆን አድርጎታል።ጽሁፉ በሚገባ ቢቀናበር ኖሮ ግን ከእጅ ጽሑፉ ተነባቢነት ጋር ተዳምሮ መልዕክቱን አፍክቶና አጉልቶ ያሳየው ነበር። ጽሑፉን ስናነብም ዓረፍተ-ነገሮቹ ተቀናብረው ባለመቀረባቸው የአንድ ዓረፍተ-ነገር ያህል ነው ስሜት የሚሰጡት እንጅ በአንድ አንቀጽ ውስጥ ያለውን ሀይለ ቃል የሚደግፉና የሚያብራሩ ዓረፍተ-ነገሮች ያሉት አይመስልም። በዚህም አንቀጹ የመልዕክቱ ተደራሽነት አነስተኛ ሆኗል።

አንቀጽ 17



ይህ አንቀጽ በአንድ ዓረፍተ ነገር የተጻፈ ሲሆን በውስጡ በርካታ ቁርጥራጭ ሀረጎች ይገኛሉ። እነዚህን ሀረጎች አያያዥ ቃላት ተጠቅመን ወይም ደግሞ ከአንዱ ሀረግ ወደ ሌላኛው ሀረግ በሚሸጋገርበት ጊዜ ተገቢነት ባለው መልኩ ቢዋቀሩ አንቀጹ ሙሉ መልዕክት ማስተላለፍ ይችል ነበር። ነገር ግን ይህ ባለመሆኑ በዝርው የተጻፈ የግጥም ሀረግ እንዲመስል አስገድዶታል። ይህ ጽሑፍ ከላይ ያነሳነው ጉዳይ ዋነኛ ችግሩ ቢሆንም ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ችግሮችም ይታዩበታል።

አንቀጽ 18



ይህ አንቀጽ ስለ ሐገር የተጻፈ ሲሆን ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይቶ ለማወቅ የሚያስቸግር፣ ስርዓተ ነጥቦች በተገቢው ቦታ የሌሉት፣ የአተራረክ ችግር ያለበት እና ጽሑፉን ለማንበብ የሚያስቸግር ነው።

ጽሑፉ ከስድስት ዓረፍተ ነገሮች የተገነባ ሲሆን እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር እንኳን ምን ለማለት ተፈልጎ እንደተጻፉ ለማወቅ አይቻልም። የእነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ቅንብር ደግሞ መላቅጡ የጠፋበት ጽሁፍ እንዲሆን አድርጎታል።

ይህን አንቀጽ በምናነብበት ጊዜም ስለ ሀገር እንደሆነ ከርዕሱ እና በውስጡ ባሉት ዓረፍተ ነገሮች ለመረዳት ብንችልም አንድ ሰው አፉን ባልፈታበት ቋንቋ የሚናገረውን አይነት ንግግር የሚመስል ነው። በዚህ ምክንያት የአንቀጹን ሀሳብ ለመረዳት የሚያስቸግር ቅንብር የጎደለው አንቀጽ አድርጎታል።

አንቀጽ 19



አንቀጹ ሐገራችን ኢትዮጵያ የሰላምና የዲሞክራሲ ሀገር መሆኗን የሚገልጽ ሰባት መስመር በአንድ ዓረፍተ ነገር የተገለጸበት፣ የእጅ ጽሑፉ ተነባቢነቱ አስቸጋሪ የሆነ፣ ተገቢው ስርዓተ ነጥብ የሌለው ጽሑፍ ነው።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከላይ በአንቀጹ ላይ ለማየት እንደሚቻለው ፊደላቱ ትክክለኛ ቅርጻቸውን ያልጠበቁ፣ የፊደል ግድፈት ያለበት ነው። ከዚህ በተጨማሪም በጽሑፉ ውስጥ ያሉት ሀረጋት እርስ በእርሳቸው የተዋሀዱ ባለመሆናቸው አንቀጹ ቅንብር ያለው እንዳይሆን አድርጎታል። በእነዚህ ምክንያቶች ጽሑፉ መልዕክቱ የደበዘዘና ለዛ ያጣ ሆኗል።

ከላይ በቅንብር ጉድለት ስር ያነሳናቸው አንቀጾች ችግራቸው የቅንብር ብቻ አይደለም።ሌሎች ችግሮችም ይታዩባቸዋል። ነገር ግን የቅንብር ችግር ጎልቶ ስለሚታዩባቸው በዚህ ርዕስ ስር ተተንትነዋል።

### 4.2.1.4 የሀሳብ አንድነትን ያልጠበቁ አንቀጾች ትንተና

አንቀጽ 20



ይህ አንቀጽ ከስምንት ዓረፍተ ነገሮች የተገነባ ሲሆን በጹሑፉ ውስጥ የሚነሱት ጉዳዮች ዋናውን ሀሳብ የሚያብራሩና የሚደግፉ ከመሆናቸው ይልቅ ራሳቸውን ችለው ሌላ ደጋፊ ዝርዝር ሀሳቦች የሚያስፈልጋቸውና ሌላ አንቀጽ ሊያስጽፉ የሚችሉ ናቸው።

ለምሳሌ፡ በመጀመሪያ "ሀገር ማለት ህዝብ ነው" በማለት የሀገርን ብያኔ ከገለጸ በኋላ ሀገርና ህዝብ ስላላቸው ቁርኝት መግለጽ ይገባል እንጅ አንዱን ከአንዱ ማበላለጥ ተገቢ አይደለም። በዚህ ጽሑፍ ግን "... ለማንኛውም ነገር ሀገር ትበልጣለች።" በማለት የመጀመሪያውን ብያኔ ሲያፈርስ እናያለን።

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ አንቀጽ ውስጥ ያሉት ሰባት ዓረፍተ ነገሮች የሀሳብ አንድነት ያላቸው ማለትም በመጠኑም ቢሆን ተቀራራቢነት ያላቸው ሲሆን የሚገልጹትም ሀገር ሰላም እንድትሆን ህዝቦቿ እንደሚያስፈልጓትና ህዝቦች ደግሞ መብትና ግዴታቸው የሚከበረው ሀገራቸው ሰላም የሰፈነባት ስትሆን እንደሆነ ሲሆን የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር ግን "ሀገሬን እወዳለሁ የሚል ዜጋ ጠንክሮ መስራት ግዴታው ነው።" የሚል ነው። ይህም ከላይኛው ሀሳብ ጋር ተያያዥነት የሌለው ነው። ይህ በመሆኑም አንቀጹ አንድነት የሌለው እንዲሆን አስገድዶታል።

አንቀጽ 21



ይህን አንቀጽ በምናይበት ጊዜ በመጀመሪያ ተግባር ተነሳ፤ እንዲህ በመባል ፡እናቴ እኔን የወለደች በቤተሰብ ውስጥ ተንከባክባ ያሳደገች" ከዚህ ቀጥሎ ያለው ዓረፍተ ነገር ደግሞ

ከመጀመሪያው ሀሳብ በመውጣት ስለተክለ ሰውነቷ "... ጠየም ያለች፣ ወገቧን በመልካም መቀነት የታጠቀች፣ ፀጉሯን የተሰራች፣ ስትራመድ ቀጭ ቀጭ የምትል" በመባል ተገልጿል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ሌላ ሀሳብ ሲቀርብ እናያለን። ይህም "... ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማህፀኗ የያዘች..." የሚል ነው። ይህ ዓረፍተ ነገር የመጀመሪያውን ዓረፍተ ነገር የሚደግፍ ቢሆንም በመካከል ግን ሌላ ሀሳብ ያለው ዓረፍተ ነገር አይተናል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያሉት ዓረፍተ ነገሮች ተዘበራርቀው የቀረቡ ከመሆናቸው በተጨማሪ ፣ የአጆ ጽሑፍ አለመንበብ፣ ከዋና ሀሳብ ወደ ዝርዝር ወይም ከዝርዝር ሀሳቦች ወደ ዋናው ሀሳብ መገለጽ ያልተቻለበት ነው። በመሆኑም ጽሁፉ የተንዛዛ፣ የሀሳብ ይዘቱ የተዘበራረቀ እንዲሁም አንድነቱ የተፋለሰ ነው።

አንቀጽ 22



ይህ አንቀጽ ከዘጠኝ ዓረፍተ ነገሮች የተገነባ ሲሆን ተማሪው አንቀጽ መጻፉን የዘነጋው ይመስላል። በዚህ ጽሑፍ የተላለፈው መልዕክት እናት ልጆቿን ተንከባክባ የምታሳድግ መሆኗን፣ ተምሮ ስራ ስለመያዝ፣ ስለ አኗኗር ሁኔታ እና የገቢ ምንጭ በማንሳት አንቀጹን የብዙ ሀሳቦች ጥርቅም ሆኗል።

አንቀጽ ደግሞ ስለአንድ ሀሳብ የሚያትት፣ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦች ያሉት፣ በተመረጡ ቃላትና አገላለጽ የሚጻፍ የድርሰት አነስተኛ ክፍል ነው። ይሁን እንጅ የአንቀጽን አላማና ተግባር በመዘንጋት በዚህ ጽሑፍ ካንድ በላይ ርዕሰ ጉዳዮች ተገልጸዋል። በዚህም ጽሑፍ አንድነት የጎደለው ነው ማለት ይቻላል።

አንቀጽ 23



በዚህ አንቀጽ የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ የቆሎ ተማሪን በተመለከተ ሲሆን በውስጡ ያሉት ገለጻዎች ግን የቆሎ ተማሪን የሚያመለክቱ አይደሉም። ገና ከመጀመሪያው አጻጻፉን ብናይ ሁለቱ መስመር በግጥም መልክ የተጻፈ ሲሆን ከዚያ በኋላ ያሉት ደግሞ በአንቀጽ መልክ ለመጻፍ ሙከራ ተደርጎበቸዋል።

በዚህ ጽሑፍ "አንድ ተማሪ የቆሎ ተማሪ መባል የሚገባው በመጀመሪያ የሚከተሉትን ሲያሟላ ነው።" በማለት ይጀምርና ከዚህ ዓረፍተ ነገር በታች ያሉት ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮች ግን የቆሎ ተማሪን የቆሎ ተማሪ የሚያሰኙ አይደሉም።

ለምሳሌ፡ የቀሉ ተማሪን ተማሪ ከሚያስኙት ነጥቦች "የቤት እና የክፍል ስራዎችን መስራት" የሚለው ተጠቃሽ ዓሪፍተ ነገር ነው። በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች አንቀጹ አንድነት የጎደለው ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪም ከስምንተኛ ክፍል ተማሪ የማይጠበቅ የእጅ ጽሑፍ ተነባቢ አለመሆን፣ የፊደላት ገድፈትና ትክክለኛ ቅርጻቸውን አለመጠበቅ፣ የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ፣ የስርዓተ ነጥቦች በተገቢ ቦታቸው አለመቀመጥ ችግር የታየ ሲሆን ከጽሑፍ ማየት እንደምንችለው አንድ አንቀጽ ጻፍ ተብሎ ታዞ ተማሪው ግን በሁለት አንቀጽ ለመጻፍ ሞክሯል።

ከላይ ያየናቸው አንቀጾች የፊደላት ገድፈት፣የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ፣የስርዓተ ነጥቦች፣ስዋስዋዊ እና የቅንብር ችግሮች የሉባቸውም ማለት ሳይሆን ጎልቶ የሚታይባቸው የሃሳብ አንድነትን አለመጠበቅ ችግር በመሆኑ ነው።

## 4.2.1.5 የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችግር የሚታይባቸው አንቀጾች ትንተና

አንቀጽ 24



ይህ አንቀጽ ስለጓደኛሞች የሚተርክ ሲሆን በውስጡ ሰባት ዓረፍተ ነገሮች ይገኙበታል። በነዚህ ዓረፍተ ነገሮችም ስለ ጓደኞች ጥሩነት፣ ስነስርዓት፣ የትምህርት ፍላጐት፣ ፍቅር እና ድጋፍ ለመግለጽ የተሞከረ ሲሆን የዚህ ምክንያት ደግሞ ጥሩ ሰው መሆናቸው እንደሆነ በአንቀጹ መግቢያ ላይ ተጠቅሟል።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ባሉት ዓረፍተ ነገሮች በአንዱም እንኳ ምንም አይነት ስርዓተ ነጥብ አልተቀመጠም፡፡ የዚህ ችግርም የአንቀጹ መልዕክት ለአንባቢ ያለውን ተደራሽነት ከመቀነሱም በላይ ትጠሉ ተመልምሎ ግንዱ ብቻ እንደቆመ ዛፍ አስመስሎታል፡፡ ይህ አንቀጽ ስርዓተ ነጥቦችን ቢኖሩት ኖሮ እንደሚከተለው ይጻፍ ነበር፡፡

"ጓደኞቼ በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም፡- ስነ-ስርዓት እና የትምህርት ፍላጎት አላቸው፡፡" ወዘተ. በማለት ማስተካከል ይቻላል፡፡

አንቀጽ 25


ርዕስ ፡ እናት

በዚህ አንቀጽ እናት ለልጆቿ የምታደርገውን እንክብካቤ ለመግለጽ የተሞከረ ሲሆን ከዝርዝር ጉዳዮች በመነሳት ወደ አጠቃላይ በመሔድ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ሀሳቡ በሰፊው ካለመገለጹም በተጨማሪ ስርዓተ ነጥቦችን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በአግባቡ ሲጠቀሙ አላየንም፡፡ ለምሳሌ፡- "እናት ማለት ዘጠኝ ወር አርግዛ፣ ሦስት ዓመት አጥብታ፣ አዝላ፣ ሽንት /ቆሻሻን/ በማጠብ…." ወዘተ የሚሉትን ሀሳቦች በነጠላ ሰረዝ መለየት ማለትም ነጠላ ሰረዝን በተገቢው ቦታ መጠቀም ሲገባ ባገኘው አንቀጽ ውስጥ ግን ይህን አላየንም፡፡



ይህ አንቀጽ በአራት ዓረፍተ ነገሮች ተያያዥነት እና አንድነቱን በጠበቀ መልኩ የተጻፈ፣ ከአሁን በፊት ለትንተና ከቀረቡትም ሆነ ለትንተና ካልቀረቡት አንቀጾች አንጻር ሲታይ በተጠቀሙባቸው ቃላት፣ የሀሳቡን ምሉእነት ለማሳካት በተቀናበረ መልኩ ከመገለጹ ወዘተ. ጉዳዮች አንጻር አንቀጹን ከሌሎች አንቀጾች ለየት ያደርገዋል። ይሁን እንጅ ይህ ጽሑፍ ከሌሎች ለየት ይላል ማለት ምንም አይነት ችግር የለበትም ማለት አይደለም፤ ይኸውም አልፎ አልፎ የፊደል ግድፈት እና ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም ላይ ችግር ማስተዋላችን አልቀረም።

ስርዓተ ነጥብን በተመለከተም ነጠላ ሰረዝ በሚያስፈልጋቸው ቦታዎች ያለመጠቀም ችግር የታየ ሲሆን ይህ ቢሟላ ኑሮ ግን የአንቀጹን ሀሳብ አፍክቶና አጉልቶ ለማቅረብ አመቺ ይሆን ነበር። ነጠላ ሰረዝ በመቅረቱ ግን የአንቀጹን ሀሳብ አደበዝዞታል። ይህም እንዲህ ይስተካከል ነበር።

"ኢትዮጵያ ሀገሬ ከአፍሪካ በስተ ምስራቅ የምትገኝ የአፍሪካ ቀንድ በመባል የምትታወቅ ሀገር ስትሆን፣ በሰሜን ኤርትራ፣ በምዕራብ ሱዳን፣ በደቡብ ኬንያ እና በምስራቅ ጅቡቲ ያዋስኗታል።"

አንቀጽ 27



ይህ አንቀጽ ስለ እናት የተጻፈ ሲሆን ከአራት አረፍተ ነገሮች ተዋቅሯል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥም የታየው ስህተት በከፍተኛ ደረጃ የስርዓተ ነጥብ ችግር ነው።

ይህ ጽሑፍ ከመጨረሻው ዓረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ ብቻ አራት ነጥብ የተቀመጠ ሲሆን ከላይ እንደሚታየው በሌሎቹ ዓረፍተ ነገሮች ምንም አይነት ስርዓተ ነጥብ አልተቀመጠባቸውም። በመሆኑም ይህ አንቀጽ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመን ስናስተካክለው እንደሚከተለው ይሆናል።

“እናት ማለት ከቶውንም በጎውንም ሰምታ የምታሳድግ ስትሆን ዘጠኝ ወር አርግዛ፣ ሦስት ዓመት አጥብታ፣ የሚበላ፣ የሚጠጣ፣ የሚለበስ ወዘተ. ፈልጋ ሁሉን ነገር የምታሟላ ናት።”

አንቀጽ 28



ይህ አንቀጽ ስለ እንዋር፣ አብርሃም፣ ይበልጣል እና ግሩም የተባሉ ጓደኛሞች የሚያወራ ሲሆን አራት ነጥብን በየግሬፍት ነገሮቹ መጨረሻ ላይ መጠቀም ባለመቻሉ በአንቀጹ ውስጥ ያሉት ግሬፍት ነገሮች እንደባቡር ፍርጎዎች የተቀጣጠሉና ረጃጅም እንዲመስሉ ተደርገዋል። ጸሐፊው አራት ነጥብን በየግሬፍት ነገሮቹ መጨረሻ ላይ ቢጠቀም ኑሮ ግን ይህን አንቀጽ የገነቡት ግሬፍት ነገሮች የተቆጣጣሩ ይሆኑ ነበር።

አንቀጽ 29


ል እናት ፡ እናት ማለት ከፍተኛ ክብርና ምስጋና
የሚሠጣት ናት ። እናት ዘጠኝ ወር በሆዷ እዐ
መዛ ሶስት ቀን አምጣ ሰባት ቀን በአላ
ጋ ላይ ተኝታ አራት ዓመት ጡቷን አጥብታ
አራት አመት በማጓቀዋ አዝላ ቢወድቅባት
አንስታ ቢታመምባት አስመርምራ ልጇን
ሽክሟ የምታሣድግ እናት ናት ስለዚ
ህ ለእናት ከፍተኛ ክብርና ምስጋና ሊሰጣት
ይገባል

ይህ አንቀጽ እናት ልጅ በማሳደግ ሂደት ውስጥ የምትወጣቸውን ሀላፊነቶች ለመግለጽ የሞከረ ሲሆን እነዚህን ነገሮች በሚዘረዝሩበት ጊዜ ግን ምንም አይነት የመለያ ስርዓተ ነጥብ ግስተመጥ ባለመቻሉ የአንቀጹን ሀሳብ አደብዝዞታል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያለው የስርዓተ ነጥብ ችግር ሲስተካከልም አንቀጹ ይህን የመሰለ ቅርጽ ይኖረዋል።

"እናት ከፍተኛ ክብርና ምስጋና የሚሰጣት ናት። ምክንያቱም ዘጠኝ ወር በሆዷ ተሸክማ፣ ሦስት ቀን አምጣ፣ ሰባት ቀን በአልጋ ላይ ተኝታ፣ አራት ዓመት ጡቷን አጥብታ፣ አራት ዓመት በማጓቀዋ /በጀርባዋ/ አዝላ፣ ቢወድቅባት አንስታ፣ ቢታመምባት አስመርምራ ልጇን ሸክፋ የምታሳድግ በመሆኗ ነው። ስለዚህ ለእናት ከፍተኛ ክብርና ምስጋና ሊሰጣት ይገባል።"

ተብሎ ቢጻፍ የተሻለ ይሆን ነበር። ነገር ግን የስርዓተ ነጥቦች መቅረት በዚህ አንቀጽ ውስጥ ስለሚታዩ የሀሳቡን ብሩህነት የደበዘዘ እንዲሆን አድርገውታል።

የስርዓተ ነጥብ ችግር ያለባቸው አንቀጾች ትንተና በሚለው ርዕስ ስር የተተነተኑት አንቀጾች ሌላ ችግር የለባቸውም ማለት ሳይሆን ከፍተኛው ችግር የስርዓተ ነጥብን በተገቢው ቦታ አለመጠቀም በመሆኑ ነው።

### 4.2.1.6 የስዋስዋዊ አገባብ ስህተት የሚታይባቸው አንቀጾች ትንተና

አንቀጽ 30



ይህ አንቀጽ ስለ እናት ለልጆቿ ያላትን አሳቢነት በተመለከተ የተጻፈ ሲሆን የሀሳብ ቅደም ተከተሉ የተጣበ እና የቃላትና ሀረጋት መደጋገም እንዲሁም ስርዓተ ነጥቦች የሌሉት ነው፡፡ የፊደል ገድፈትና ትክክለኛ ቅርጻቸውን አለመያዝ ችግርም ጎልቶ ይታይበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ አለመስማማት ችግር ይታያል፡፡ የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ሲስተካከልም "እናት ማለት ሲርብ የምታበላ፣ሲጠማ የምታጠጣ ናት፡፡" ተብሎ መስተካከል ይችላል። ነገር ግን ከላይ ያየነው የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ስምምነት ያልተፈጠረው "እናት ማለት "ሲርበኝ የምታበላኝ"፣ "የምታጠጣኝ" የሚሉት ቃላት "እናት" ከሚለው ቃል በተጨማሪ ማሰሪያ አንቀጽን የሴቱ ማሰሪያ እንዲሆን ያስገድዱታል። ነገር ግን ይህ ባለመሆኑ ዓረፍተ ነገሩ ስሜት የማይሰጥ ከመሆኑም በተጨማሪ ተገቢነቱ እንዲቀንስ ሆኗል።

አንቀጽ 31



ይህ አንቀጽ የፊደላት ግድፈትና ትክክለኛ ቅርጻቸውን አለመያዝ፣ የቃላት ምርጫ ስህተትና ድግግሞሽ፣ የስርዓተ ነጥቦች በተገቢ ቦታቸው አለመኖር፣ ስዋስዋዊ አገባብን አለመጠበቅ ወዘተ ችግሮች ይታዩበታል። እነዚህን በተወሰነ መልኩ ለማየት እንሞክራለን።

"ትምህርት ቤቴን ከምንም በላይ የምወዳት የእውቀት መሰረቴን ያዳበረልኝ ስለሆነ ነወ የወደድኩት" የሚለውን የመጀመሪያውን ዓረፍተ ነገር ብናይ "የምወዳት" የሚለው ቃል ከእሱ በኋላ ከተዘረዘሩት ቃላት ማለትም "ያዳበረልኝ፣ የወደድኩት" ከሚሉት ቃላት ጋር አብሮ ሊሄድ አይችልም። ወይም ደግሞ "የምወዳት" የሚለው ቃል "የምወደው" ቢሆን ኖሮ ከሌሎቹ ቃላት ጋር በመቀናጀት የዓረፍተ ነገሩ ቅንብር የተዋጣ /እንከን የሌለው/ ይሆን ነበር። በምሳሌነት የተወሰደው ዓረፍተ ነገር ሲስተካከልም "ትምህርት ቤቴን ከምንም በላይ የምወደው የእውቀት መሰረቴን ያዳበረልኝ ስለሆነ ነው።" ተብሎ ሊጻፍ ይችላል።

አንቀጽ 32



በዚህ አንቀጽ ውስጥ ያለውን ችግር ስናይ ስለ ሀገር ገለጻ እየተደረገ ሀገርን አንዴ ሲሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ ስትሆን በማለት የተገለጸ ሲሆን በተጨማሪም "ሀገር" በሴት ጾታ የምትጠራ ሲሆን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ግን በወንድ ፆታ ተገልፃ እናያለን። ይህ ደግሞ የባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ አለመስማማትን ይፈጥራል። በዚህም የአንቀጹ ሀሳብ የተምታታና ግራ የሚያጋባ ገጽታ እንዲያዝ አድርጎታል።

ለምሳሌ፡ "ሀገር ማለት የአንድ ህዝቦች መገለጫ ሲሆን ልክ እንደ እናት ሁሉንም ገመና ሸፍኖና አቅፎ የያዘ ነው።" ይህ ዓረፍተ ነገር የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ፣ የቁጥር አለመስማማት ችግር አለበት። እነዚህም "የአንድ" ብሎ "ህዝብ" መባል ሲገባ "ህዝቦች" መባሉ ለቁጥር አለመስማማት ችግር ምክንያት ሲሆን "ሀገር" ተብሎ ለተነሳው ይህ ዓረፍተ ነገር ማሰሪያ አንቀጹ "ናት" መባል ሲኖርበት "ነው" በመባሉ ዓረፍተ ነገሩ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ አለመስማማት ችግርን ፈጥሯል። ይህ ዓረፍተ ነገር ሲስተካከልም፡- "ሀገር የአንድ ህዝብ መገለጫና እንደ እናት ሁሉንም ገመና ሸፍናና አቅፋ የያዘች ናት።" ቢባል የተሻለ ይሆናል።

እነዚህ በስዋስው ርዕስ ስር የታዩት አንቀጾች ችግራቸው የስዋስው ብቻ ሆኖ ሳይሆን ይበልጥ ስዋስዋዊ ችግሮች ስለሚታዩባቸው ነው።

## 4.2.2. የሥርዓተ-ነጥቦች አገባብ

ስርዓተ ነጥቦች በጽሁፍ የሚቀርብን ሀሳብ በአረፍተ ነገሮች ከፋፍሎ ለማቅረብ፣ ዓረፍተ-ነገሩ መቋጨቱን ለማመልከት፣ የሚዘረዘሩ ነገሮችን ለመለየት፣ ጸሐፊው ለማስተላለፍ የሚፈልገውን ሀሳብ ስሜት ለመረዳት ከፍተኛ የሆነ አገልግሎት አላቸው። በጽሁፍ የሚቀርብ ሀሳብ ጸሐፊው ማስተላለፍ የፈለገውን መልእክት አንባቢ የሚረዳው የስርዓተ ነጥቦችን አጠቃቀም እና ሁኔታ በመመልከት ነው። ከዚህ በተጨማሪም በጽሁፍ የሚቀርብ ሀሳብ ትክክለኛነት ከሚለካባቸው መስፈርቶች ውስጥም ስርዓተ ነጥብ ዋነኛው ጉዳይ ነው።

ስርዓተ ነጥቦች በተግባቦት አንቀጾች ውስጥ ተዳስዋል በድጋሚ ማንሳቱ ለምን አስፈለገ? ሲባል ይችላል። በድጋሚ ማንሳት ያስፈለገበት ምክንያት በክለሳ ድርሳኑ ላይ እንደተገለፀው የመማር አጥጋቢ ብቃት በሚለው ሰነድ ላይ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸውን ስርዓተ ነጥቦች መመርመር ስለተፈለገ ነው። በዓይነቸው አንቀፆች ውስጥ ግን የመማር አጥጋቢ ብቃት በሚለው ሰነድና በመርሀ ትምህርቱ የተጠቀሱት ስርዓተ ነጥብን የተመለከቱ ዝርዝር ነጥቦች ላይካተቱ ይችላሉ ብሎ በማሰብ ነው።

የተጠኚ ተማሪዎች ስርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማወቅ ስርዓተ ነጥብ ማሟላት የሚያስፈልጋቸውን ዓረፍተ-ነገሮችን የተሰጡ ሲሆን በዚህ ፈተና የተገኘው ውጤትም የሚከተለውን ይመስላል።

ሠንጠረዥ 11፦ የተጠኚዎቹ ተማሪዎች ስርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማወቅ የስርዓተ ነጥብ ማሟላት ጥያቄ /ፈተና/ የተገኘው ውጤት

| የተማሪ ብዛት | ያመጡት ውጤት |
|---|---|
| 51 | 4 |
| 33 | 6 |
| 20 | 2 |
| 21 | 0 |
| 15 | 8 |
| 13 | 10 |

ከላይ በሰንጠረዥ እንደሚታየው የተማሪዎቹ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ ማስቀመጥ ውጤት ከተፈታኝ ተማሪዎቹ ውስጥ ዜሮ /ባዶ/ ያገኙ ተማሪዎች ቁጥር በሁሉም ትምህርት ቤቶች 21/153 /ከመቶ ሃምሳ ሶስት ተፈታኞች ውስጥ ሀያ አንድ/ ያህል ሲሆኑ የዚህ ስሌት 0.13፣ ሁለት ነጥብ ያገኙም 20/153 / ከመቶ ሃምሳ ሶስት ተፈታኞች ውስጥ ሃያ/ ያህል ተማሪዎች ሲሆኑ የዚህ ስሌት በተመሳሳይ 0.13፣ አራት ነጥብ ያገኙ ተማሪዎች ቁጥር 51/153/ ከመቶ ስልሳ ተፈታኝ ተማሪዎች ሃምሳ አንድ/ ያህል ሲሆኑ የዚህ ስሌት 0.33፣ ስድስት ነጥብ ያገኙ ተማሪዎች 33/153 /ከመቶ ሃምሳ ሶስት ተፈታኝ ተማሪዎች ሰላሳ ሶስት/ ያህሉ ሲሆኑ የዚህ ስሌት 0.21፣ ስምንት ነጥብ ያገኙ ተማሪዎች 15/153 / ከመቶ ሃምሳ ሶስት ተፈታኝ ተማሪዎች ውስጥ አስራ አምስት/ ያህል ሲሆኑ የዚህ ስሌት 0.09 እና አስር ነጥብ ያገኙ ተማሪዎች ቁጥር 13/153 /ከመቶ ሃምሳ ሶስት ተፈታኝ ተማሪዎች ውስጥ አስራ ሶስት/ ያህል ናቸው። የዚህም ስሌት 0.08 ነው።

በጠቅላላው ከመቶ ሃምሳ ሶስት /153/ ተማሪዎች ውስጥ ሰባት እና ከዚያ በላይ ያገኙ ተማሪዎች ቁጥር 28/153 / ከመቶ ሃምሳ ሶስት ተማሪዎች ሰላሳ አንድ/ ብቻ ናቸው፡፡ ይህን በማመጣከን ስሌት 0.18 ነው።

ከዚህ በአጠቃላይ አማካኝ ስሌቱን እንደተመለከትነው የተጠኚ ተማሪዎቹ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ ያሳያል። ከዚህ መረዳት የሚቻለውም ተማሪዎቹ ስርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ አስቀምጡ የሚል ትዕዛዝ ተሰጥቶአቸው ነጥቦቹን በትክክለኛ ቦታቸው ማስቀመጥ ካልቻሉ ይህ ትእዛዝ ሳይሰጣቸው /ሳይተላለፍ/ የሚጽፏቸው ጽሑፎች ምን ያህል አንባቢን ግራ ሊያጋቡና የጽሑፉን መልእክት እንደሚያደበዝዙ መገመት አያዳግትም።

በአጠቃላይ እስከ አሁን ድረስ በምእራፍ አራት የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሃሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሁፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ተጠኝ ተማሪዎቹ የጻፏቸውን አንቀጾች መነሻ በማድረግ ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙትን ምላሾች በመጨመር ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በምዕራፍ አምስት በዚህ ጥናት የተደረሰበትን ውጤትና አስተያየት ለማቅረብ ይሞከራል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሐሳብ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሌቦ ከምከም ወረዳ የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሀሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጹሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ መስጠት ነው። ከዚህ ዋና /አቢይ/ አላማ በተጨማሪም ጥናቱ የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች አሉት። እነዚህም፡ በተንባቢ የእጅ ጽሑፍ ሀሳባቸውን ማቅረብ አለማቅረባቸውን መፈተሽ፣ በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የገቢ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ማወቅ፣ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን አንቀጽ መጻፍ አለመጻፋቸውን መለየት እና ሰዋስዋዊ ስርዓቱንና የሀሳብ ቀደም ተከተልን አስተካክለው መጻፍ አለመጻፋቸውን መለየት የሚሉት ናቸው።

በዚህም መሰረት በተተኳሪው የክፍል ደረጃ ለሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በማዋላት እና ለስምንተኛ ክፍል ተጠኚ ተማሪዎች ደግሞ የችሎታ መለኪያ ፈተና በመስጠት ያላቸውን የጽሕፈት ክሂል ብቃት ለመመርመር መረጃ ተሰብስቧል። የተሰበሰቡትን መረጃዎችም ለትንተና አመች በሆነ መንገድ ትንተና የተካሄደ ሲሆን ከተንተናው ሂደትም የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል።

### 5.1. ማጠቃለያ

- የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ የጽሕፈት ክሂልን ለማስተማር ያለው ሚና ዝቅተኛ መሆኑን ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በተደረገው ምርመራ ለማወቅ ተችሏል።
- ተጠኚ ተማሪዎቹ ጽሕፈትን ለመማርና ክሂሉን ለማዳበር ያላቸው ፍላጎትም እንዲሁ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል።
- በሌቦ ከምከም ወረዳ የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽሕፈትን ለማስተማር የሚያደርጉትን ጥረት በተመለከተ ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በመካከለኛ ደረጃ ጥረት እንደሚያደርጉ የገለጹ ቢሆንም ተጠኚ ተማሪዎቹ ግን በቋንቋው አፈ-ፈት በመሆናቸው፣ እንዲሁም ለቋንቋው ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ሲነጻጸር የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ ነው። በተጨማሪም ከቋንቋ ክሂሎችም ለፅህፈት ክሂል የሚሰጡት ቦታ ዝቅተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።
- የተጠኚ ተማሪዎቹ የእጅ ፅሁፍ ተነባቢ አለመሆኑን ለናሙና ከተረቡትም ሆነ ካልቀረቡት አንቀፆች ለማየት ተችሏል ።

- ተጠኚ ተማሪዎቹ አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽማቸው ስህተቶች ብዙ ቢሆኑም ተገቢና ተስማሚ ቃላትን አለመጠቀም፣ በቋንቋው ህጎችና ስርዓተ ነጥቦች በአግባቡ አለመጠቀም፣ የቃላትና የሀረጋት መደጋገም እና ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽን አስማምቶ አለመጠቀም ችግር ጎልቶ እንደሚንፀባረቅባቸው ተረጋግጧል።
- በተተኳሪው የክፍል ደረጃ የሚገኙ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የጽሕፈት መልመጃ የማረምና ተማሪዎችም የተሳሳቱትን ጽሑፍ እንደገና ለማስተካከል ያላቸው ልምድ ዝቅተኛ መሆኑን መምህራን በሰጡት የጽሑፍ ምላሽ ተረጋግጧል።
- መምህራን ለተማሪዎቻቸው ጽሕፈት ተኮር ተግባራትን እንደሚያለማምዱ ቢገልጹም የተማሪዎቹ የጽሕፈት ውጤት ግን ዝቅተኛ ነው።
- በተጠኚ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ በተለይ ደግሞ የጽሕፈት ትምህርትን በትኩረት ባለመከታተል የጽሕፈት ክሂላቸው ዝቅተኛ መሆኑን ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል።

ለተማሪዎች የጽሕፈት ክሂል ዝቅተኛ መሆን ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችንም እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል፤

- የተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሂልን ለመማርና ያላቸውን እውቀት ለማዳበር ተነሳሽነት አለመኖር። በዚህም ከሌሎች ክሂሎች በበለጠ ትኩረት አለመስጠታቸው ችግሩን ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል።
- ተማሪዎቹ የሚሰጣቸውን የጽሕፈት ክሂልን የሚያሳድጉ የክፍልና የቤት መልመጃዎችን ትኩረት ሰጥተው አለመስራት፤
- መምህራን የዲፕሎማ ምሩቃን መሆናቸው፤
- መምህራን የጽሕፈት መልመጃዎችን ተከታትለው የማያርሙ በመሆኑ እና አንዳንዴ /አልፎ አልፎ/ እንኳን ቢያርሙ ስህተታቸውን በሚነግር /በሚያሳይ/ መልኩ አለማረም ለጽሕፈት ክሂል ዝቅተኛ መሆን እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ።

በአጠቃላይ የተማሪዎቹ ሐሳባቸውን በጹሑፍ የመግለጽ ብቃት ማነስ፣ የእጅ ጽሑፍ አለመነበብ፣ የቃላት ምርጫ፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የግድፈተ ነገር አለካከ፣ የአንቀጽ አንድነት ጥምረት እና ውህደት፣ የባለቤትና ግስ አለመጣጣም ችግር እንዳለባቸውና የተማሪዎቹ ችሎታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መረጃው አሳይቷል።

## 5.2. የመፍትሔ ሃሳብ

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሔ ሃሳቦች ቀርበዋል፤

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሕፈት ክሒል ትምህርት ያለውን ጥቅም ለተማሪዎቻቸው ቢያሳውቁ የችግሩን አሳሳቢነት በመጠኑ ለመቀነስ ያስችላልና ይህንን ቢያደርጉ፣
2. በጽሕፈት ክሒል ዙሪያ ተማሪዎች ተከታታይነት ያለው ልምምድ እንዲያደርጉ በመምህራን በኩል ማበረታታት ቢደረግ፤
3. የቋንቋ መምህራኑ የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሒል የሚያሳድጉ የክፍልና የቤት መልመጃዎችን በመስጠት ከጓደኞቻቸው ጋር እርስ በርስ እርማት እንዲሰጣጡ ጥረት ቢያደርጉ፤
4. ከተማሪዎች ዝቅተኛ የጽሕፈት ክሒል ተነስቶም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ስህተት ቀጥተኛ የሆነ እርማት በመስጠት የጽሕፈት ክሒላቸው እንዲሻሻል ጥረት ቢያደርጉ፣
5. የጽሕፈት ክሒል በትምህርት ቤት ቆይታ ወቅት በተከታታይ ልምምድና በመምህራን እገዛ የሚዳብር በመሆኑ መምህራን ለጽሕፈት ክሒል ትኩረት በመስጠት የችግሩ ሰለባ የሆኑ ተማሪዎችን በመደበኛውና መደበኛ ባልሆነ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለተማሪዎች እገዛ ቢሰጥ፣
6. ለመምህራን የፅህፈትን ትምህርትና አቀራረቡን በተመለከተ የሙያ ላይ ስልጠና ቢሰጥ የሚሉት ነጥቦች በመፍትሔ ሀሳብነት ቀርበዋል።

## ዋቢ ምንጮች (References)


ሥ/ት/ዝ/ፕ/ም/ ኢንስቲትዩት ::1995:: *ከ5ኛ-8ኛ ክፍሎች አጥጋቢ የመማር ክህሎት*::አዲስ አበባ፤ተባዝቶ የተጠረዘ:: ሥ/ት/ዝ/ፕ/ም/ ኢንስቲትዩት ::1996:: *የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ስምንተኛ ክፍል*:: አዲስ አበባ፤ተባዝቶ የተጠረዘ::

ሰይድ ይመር:: 1993:: "ለ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻሕፍት የቀረቡትን የጽሕፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ (የመማር ማስተማር ሂደት) ግምገማ::"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ለማስተር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ::(ያልታተመ)::

በድሉ ዋቅጅራ:: 1996:: *በስነ ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር*:: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

ባዬ ይማም:: 1987:: *የአማርኛ ሰዋስው*:: አዲስ አበባ፤ የት.መ.ማ.ማ.ድ::

አለማየሁ ተመስገን:: 1998 :: "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሁለት የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሕፈት ክሂል ብቃት ንጽጽራዊ ጥናት":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ:: (ያልታተመ)::

አማረ ማሞ:: 1976 :: *የቀለም ጠብታ*:: አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

ክፍሌ ሃብተማሪያም:: 1986 :: "የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ::"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ለማስተር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ::(ያልታተመ)::

የሻው ተሰማ:: 1996 :: *ልሳን ብዕር ከመልሳኑ ሰብዕ*:: አዲስ አበባ፤ ብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

የኔስ አድማሱና ሌሎች:: 1966:: *አማርኛ ለከፍተኛ ደረጃ*:አዲስ አበባ፤ አርትስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ቀዳማዊ ኀይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ::

ደረጀ ገብሬ:: 1996:: *ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ*:: አዲስ አበባ፤አብ ጌት ማተሚያ ድርጅት::

______::2007::"የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሃሳባቸውን በደረጃ የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? በሶስት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የተደረገ ናሙናዊ ጥናት::" The Ethiopia Journal of Education Vo.xxvii No.1.

Barr, R.and Barbara,J. 1997. *Teaching Reading and Writing In Elementary Classroom*. New York: Longman. .

Brandy,D. 1988.*Teaching Writing Skill*. London: Longman.

Byrne, D. 1988.*Teaching Writing Skills*. London: Longman.

Celce- Murcia, M. (ed.). 1991. *Teaching English as a Second Language*, Bosten: Heinle and Heinle Publishers.

Doff, A. 1988. *Teach English: A Trainning Course For Teachers*. Cambridge: Cambridge University Press.

Edge,J.1989.*Mistakes and Correction*. London and New York: Longman.

Edwards, S. 1999.*Writinng for All*.David Fulton Publisher, London.

Fenton, N. 2003. *Improve Your Technical Writing Skills*, Versoon 4.1; 25 september.

Harmer,J. 1991.*The Practice of English Language Teaching*. New York: Longman.

Heaton, J. B. 1991.*Writing English Language Tests*.(New Edition). New York:Longman Uk. Ltd.

Hedge, T. 1988. *Writing* . Oxford: Oxford University Press.

Herrero, A. H. 2007. *A Tool to Improve Students Writing Skills*, volume 7, Number 1.

Kelly, W. J. and Deborah, L. L.(1988). Odyssey: *a Guide to Better Writing*. New York: Allyn and Bacon.

Kroll,B. 1990.*Second Language Writing*. New York: Cambridge University Press.

Lee, M. and I.L.1997. "Guidelines: A Periodical for Classroom Language Teachers." In SEAMEO (ed).Facilitating In the language Classroom. Vol. 19, No.2 pp. 73-103. Oxford: Oxford Graphic printers Ltd.

Moore,C.1995. *Reading and Writing in Elementary Classrooms*. London; Longman.

Norrish, J.1983.*Language Learners and Their Errors*.Hong Kong; Essential Learning Series.

Nunan,D.1989.*Designing Tasks for the Communicative Classrom*. Cambridge: Cambridge University.

Perskey, D. J. 2003.*National Assessment of Educational Progress (NAEP)*.US Department of Educational Sciences.

Pincas, A.1982.*Teaching English Writing*. London: Macmillan Press Ltd.

Pollington,M.et al.2001.*Self Perception in Writing: the Effects of Writing Workshop and Traditional Instruction on Intermediate Grade Students*.Reading Psychology, 22, pp 249-265.

Raimes,A.1983.*Techniques in Teaching Writing*. Oxford: Oxford University press.

Reid, J. M. 1993.*Teaching ESL Writing*. New Jersey: Prentice hall Reagents.

Richards,J.C.1990.*The Language Teaching Martrix*. Cambridge; Cmabridge University Press.

Rivers, W. M. 1981.*Teaching Foreign Language Skills*, Chicago: University of Chicago Press.

Silva ,T. 1990. *A Synthesis of Research on Second Languagage Writing in English*.New York: Routledge.

Trimmes,J.F. and James, M. M. 1988.*Writing With a Purpose*. Boston: Houghton Mifflin Company.

Ur, P.1996.*A Course in Language Teaching*. Cambridge: Cambridge University press.

White, R. 1980.*Teaching Writing English*. London: By Hazell Watson & Viney Ltd, Aylesbury Bucks.

Widdowson, H. 1978.*Teaching Language as Communication*. Oxford: Oxford University Press.

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር**

**በመምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፤**

ውድ መምህር፣ ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ ሰባት ት/ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማም በሊቦ ከምከም ወረዳ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በጽሑፍ የመግለፅ ብቃት አላቸው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት እና ችግሮች ካሉም ችግሮቹ የሚስተካከሉበትን መንገድ ለመጠቆም ነው፡፡

መጠይቆቹ በአንድ በኩል የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመገምገምና በሌላ በኩል ጽሕፈትን በማስተማሩ ረገድ ያሉትን ችግሮች በዝርዝር ተመልክቶ የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ ያስችላሉ፡፡

ከመጠይቁ የሚገኘው ውጤት ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ ግብ መምታት ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና አንብበው ትክክል ናቸው ብለው የሚገምቷቸውን መልሶች እንዲሰጡኝ ስጠይቅዎት መጠይቁን ሞልተው በመመለስ ለሚያደርጉልኝ ትብብር ልባዊ ምስጋናዬ ላቅ ያለ መሆኑን በቅድሚያ እየገለጽሁ ነው፡፡

ማሳሰቢያ፡- ስም መጻፍ አስፈላጊ አይደለም፡፡

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ መረጃ

1.1 ጾታ፡- ሀ. ወንድ ------- ለ. ሴት -------

1.2 ዕድሜ --------------- ዓመት

1.3 የትምህርት ደረጃ

ሀ. ሰርተፊኬት

ለ. ዲፕሎማ

ሐ. የመጀመሪያ ዲግሪ

መ. ሌላ ካለ ይጠቀስ ----------------------------------------

1.4 አማርኛን በማስተማር ሰልጥነዋል?

ሀ. አዎ                ለ. አልሰለጠንኩም

1.5 በተራ ቁጥር 1.4 ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጡት መልስ "አዎ" የሚል ከሆነ

ሀ. አብይ ------------------------------------------------------------

ለ. ንዑስ ------------------------------------------------------------

1.6 ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመን -------------------- ዓመት

1.7 8ኛ ክፍል አማርኛን በማስተማር ስንት ዓመት አገለገሉ? ---------- ዓመት

1.8 በሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ /8ኛ ክፍል/ በሳምንት የሚያስተምሩት የክፍለ ጊዜ ብዛት --
------- ፣ የክፍል /ሴክሽን/ ብዛት ---------------

1.9 የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም ----------------------------------------------

1.10 በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉ የተማሪዎች አማካይ ብዛት -------------

<u>ክፍል ሁለት</u>

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል፡፡ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ትክክለኛ ነውናቸው ብለው የሚያምኑበትን ፊደል በመክበብ ይመልሱ፡፡

2.1 የመማሪያ መጻሕፍቱ አቀራረብ ጽሕፈትን ለማስተማር ይረዳል?

ሀ. በአብዛኛው ሐ. በመጠኑ

ለ. በከፊል መ. በጥቂቱ

2.2 በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት

ሀ. በጣም ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ

ለ. ከፍተኛ መ. እንስተኛ

2.3 ተማሪዎችዎ የአማርኛን ጽሕፈት ለመማር ያቸው ፍላጎት

ሀ. በጣም ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ

ለ. ከፍተኛ መ. እንስተኛ

2.4 ተማሪዎችዎ የፅህፈት መልመጃዎችን ለመስራት ያላቸው ፍላጎት

ሀ. በጣም ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ

ለ. ከፍተኛ መ. እንስተኛ

2.5 እርስዎ ጽሕፈትን በተመለከተ የሚሰጧቸውን የክፍል ወይም የቤት መልመጃዎች ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩት ተማሪዎች ቁጥር

ሀ. በጣም ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ

ለ. ከፍተኛ መ. እንስተኛ

2.6 ተማሪዎቹ የጻፉትን ነገረ መልሰው የማስተካከል ልምዳቸው

ሀ. በጣም ከፍተኛ ነው ሐ. መካከለኛ ነው

ለ. ከፍተኛ ነው መ. እንስተኛ ነው

2.7 እርስዎ ጽሕፈትን ለማስተማር የሚያደርጉት ጥረት

ሀ. በጣም ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ

ለ. ከፍተኛ መ. እንስተኛ

2.8 የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር የሚረዱ መልመጃዎችን ይሰጣሉ?

ሀ. ሁል ጊዜ ሐ. አልፎ አልፎ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ መ. በጥቂቱ

2.9 እርስዎ የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸውን ለማሻሻል ወይም ለማዳበር የሚያደርጉት ድጋፍ/እገዛ

ሀ. በጣም ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ

ለ. ከፍተኛ መ. አነስተኛ

2.10 እርስዎ ተማሪዎችዎን አንቀጽ እንዲጽፉ ያደርጋሉ?

ሀ. ሁሌ ጊዜ ሐ. አልፎ አልፎ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ መ. በጭራሽ

2.11 እርስዎ ተማሪዎችዎን ስለ አንቀጽ አጻጻፍ ስርዓት ተግባራዊ ልምምድ ያደርጋሉ?

ሀ. ሁሌ ጊዜ ሐ. አልፎ አልፎ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ መ. በጭራሽ

2.12 እርስዎ ተማሪዎችዎን ስለ አግርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ተግባራዊ ልምምድ ያደርጋሉ?

ሀ ሁሌ ጊዜ ሐ. አልፎ አልፎ

ለ አብዛኛውን ጊዜ መ. በጭራሽ

2.13 እርስዎ የቃላትን ምርጫና አጠቃቀምን በተመለከተ ተማሪዎችዎን ያለማምዳሉ?

ሀ ሁሌ ጊዜ ሐ. አልፎ አልፎ

ለ አብዛኛውን ጊዜ መ. በጭራሽ

2.14 እርስዎ ለተማሪዎችዎ የተለያዩ የስርዓተ ነጥቦችን አገልግሎትና አጠቃቀም ያለማምዳሉ?

ሀ ሁሌ ጊዜ ሐ. አልፎ አልፎ

ለ አብዛኛውን ጊዜ መ. በጭራሽ

2.15 አንቀጽ /ድርሰት ሲጽፉ

ሀ የሀሳብን አንድነት አይጠብቁም

ለ በአንቀጹ ውስጥ ያሉት ዓረፍተ ነገሮች የአንቀጹን ዋና ሀሳብ ብቻ እንዲያብራሩ አድርጎ አለመጻፍ

ሐ የአንቀጹን ሀሳብ ተያያዥነት እዲኖረው አለማድረግ

መ የአንቀጹን ሀሳብ አቀናብሮ ለማቅረብ አለመቻል

2.16 እርስዎ ለተማሪዎችዎ የሚሰጧቸውን መልመጃዎች ተከታትለው ያርማሉ?

ሀ ሁሌ ጊዜ ሐ. አልፎ አልፎ

ለ አብዛኛውን ጊዜ መ. በጭራሽ

2.17 እርስዎ እርማቱን የሚያካሂዱት

ሀ. ተማሪዎቹ እርስ በርሳቸው ደብተራቸውን እንዲለዋወጡ በማደረግ

ለ. የተማሪዎችን ደብተር ሰብስቦ በማረም

ሐ. ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሎ ስህተታቸውን እንዲነጋገሩ በማድረግ

መ. ሌላ ካለ ይገለፁ ...................................................................................

2.18 እርስዎ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ሲጽፉ ወይም መልመጃዎችን እንዲሰሩ ሲያደርጉ የጻፉትን ነገር ደጋግመው በማንበብ የተሳሳቱትን በማረም እንደገና ለመጻፍ ያላቸው ልምድ

ሀ. በጣም ከፍተኛ
ሐ. መካከለኛ

ለ. ከፍተኛ
መ. አነስተኛ

2.19 የጽሕፈት ክሂልን በተመለከተ ተማሪዎቹ የተማሩትን በተግባር ለመጠቀም መቻላቸውን ለመመዘን የሚያስችል ሙከራ /መልመጃ/ ይሰጣሉ?

ሀ. ሁል ጊዜ
ሐ. አልፎ አልፎ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ
መ. በጭራሽ

2.20 ተማሪዎችዎ ጽሕፈትን በተመለከተ ሲፈተኑ የሚያገኙት ውጤት

ሀ. በጣም ከፍተኛ
ሐ. መካከለኛ

ለ. ከፍተኛ
መ. አነስተኛ

## ክፍል ሦስት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብበው በክፍት ቦታዎች ላይ የራስዎን አስተያዬት ይስጡ፡፡

3.1 የትምህርቱ አቀራረብ ወይም ይዘት ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል ብለው ያምናሉ? ያብራሩ፡፡

..................................................................................................................

..................................................................................................................

..................................................................................................................

3.2 ተማሪዎችዎ ጽሕፈትን ለመማር ወይም ክሂሉን ለማዳበር ያላቸውን ፍላጎት ወይም ዝንባሌ እንዴት ይገልፁታል?

..................................................................................................................

..................................................................................................................

..................................................................................................................

3.3 የ፱ኛ ክፍል ማስተማሪያ መጽሐፍ የጽሕፈት ክሂልን ለማስተማር ያለውን ብቃት ይግለጹ፡፡

..................................................................................................................

..................................................................................................................

..................................................................................................................

3.4 እርስዎ የተማሪዎችን ድርሰት የማያርሙ ከሆነ ምክንያቱን ይግለጹ፡፡

..................................................................................................................

..................................................................................................................

..................................................................................................................

3.5 የ፱ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት፣ አንቀጽ፣ ዓረፍተ ነገር ሲጽፉ ለሚፈጽሟቸው የተለያዩ ስህተቶች ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው የሚላቸውን ይግለጹ፡፡

..................................................................................................................

..................................................................................................................

..................................................................................................................

3.6 በአጠቃላይ ጽሕፈትን በተመለከተ በትምህርት ቤት ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃና አተገባበር ያለዎትን አስተያዬት ይግለጹ፡፡

..................................................................................................................

..................................................................................................................

..................................................................................................................

# አባሪ ሁለት

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩመኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር በተማሪዎች የሚመለስ የጽሑፍ ፈተና፤**

ውድ ተማሪ፦ ይህ ፈተና የተዘጋጀው በሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ ሁለት ት/ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

የፈተና ዋና ዓላማም በሊቦ ከምከም ወረዳ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለፅ ብቃት አላቸውን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለማግኘትና በዚህ ረገድ ችግሮች ካሉ የሚቀረፉበትን መንገድ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ለማሳወቅ ነው።

ማሳሰቢያ፦ ስም መጻፍ አስፈላጊ አይደለም።

ክፍል አንድ

ክፍት ቦታዎችን በተገቢ መረጃ ሙላ/ይ።

1 ዕድሜ ........................................ 3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ..............................

2 ፆታ ............................................ 4. የትምህርት ቤቱ ስም ..........................

ክፍል ሁለት

ሀ ከዚህ በታች የቀረበው ጥያቄ በየጊዜው ከሚሰጡት ፈተናዎች ጋር ግንኙነት የሌለው ስለሆነ ውጤቱ አብሮ አይደመርም። ስለዚህ ምንም ዓይነት ስጋት ሳያድርብህ/ሽ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በትዕዛዙ መሰረት መልስ/ሽ።

ተገቢ ከ "ሀ — ሠ" ከተሰጡት ቃላትና ሐረጋት ውስጥ አንዱን ብቻ በመምረጥ አንቀጽ ጻፍ/ፊ።

ሀ. የቀሉ ተማሪ

ለ. ትምህርት ቤቴ

ሐ. እናት

መ. ጓደኞቼ

ሠ. ሀገሬ

ለ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ተገቢው ስርዓተ ነጥብ የላቸውም። ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በማስገባት እንደገና ጻፏቸው።

1. የትምማግድ ባለፈው ዓመት ለተማሪዎች በቂ መጽሐፍትን አቀረበ
2. በጣሪው ዕለት አበበ ካሳ ከበደና በለጠ ትምህርት ቤታቸውን ወክለው የጥያቄና መልስ ውድድር ላይ ይሳተፋሉ
3. ጎሽ ንጽህናህን ጠብቀህ ውለሃል ለዚህ ምን ዓይነት ሽልማት ይዘጋጅልህ
4. ቆስጣ ሰላጣ ቃሪያ እና ትርንጎ ብርቱካን ሎሚ ለጤናችን ያስፈልጉናል
5. ትምህርት እማ ትምህርት ነው አሉ ጋሽ አማረ

## ሀ. የተጠኝ ተማሪዎች አንቀጽ የመጻፍ ውጤት

| ተ.ቁ | አዲስ ዘመን ት/ቤት | | | አላቦ ት/ቤት | | | አበባዬን ት/ቤት | | | ይፋግ ት/ቤት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ.1 | አ.2 | አ/ውጤት | አ.1 | አ.2 | አ/ውጤት | አ.1 | አ.2 | አ/ውጤት | አ.1 | አ.2 | አ/ውጤት |
| 1 | 5 | 6 | 5.5 | 3 | 4 | 3.5 | 7 | 6 | 6.5 | 4 | 5 | 4.5 |
| 2 | 4.5 | 5 | 4.25 | 8 | 7 | 7.5 | 4 | 4.5 | 4.25 | 3 | 3.5 | 3.25 |
| 3 | 5 | 5 | 5 | 6 | 5 | 5.5 | 7 | 6.5 | 6.75 | 4 | 5 | 4.5 |
| 4 | 2 | 3 | 2.5 | 3 | 2.5 | 2.75 | 3 | 4 | 3.5 | 4 | 5.5 | 4.75 |
| 5 | 4 | 5 | 4.5 | 3 | 3 | 3 | 4.5 | 3.5 | 4 | 3 | 4 | 3.5 |
| 6 | 3.5 | 2.5 | 3 | 2 | 3 | 2.5 | 5.5 | 5 | 5.25 | 4 | 4.5 | 4.25 |
| 7 | 4 | 5 | 4.5 | 6 | 7 | 6.5 | 4.5 | 3.5 | 4 | 5 | 5.5 | 5.25 |
| 8 | 6 | 6.5 | 6.25 | 7 | 6.5 | 6.75 | 3 | 4 | 3.5 | 2 | 2.5 | 2.25 |
| 9 | 3 | 4 | 3.5 | 5 | 4 | 4.5 | 3.5 | 2.5 | 3 | 4 | 4 | 4 |
| 10 | 8.5 | 8 | 8.25 | 7 | 6 | 6.5 | 7.5 | 8 | 7.75 | 4 | 5 | 4.5 |
| 11 | 4 | 4.5 | 4.75 | 3 | 4 | 3.5 | 2 | 3 | 2.5 | 5 | 4 | 4.5 |
| 12 | 6 | 6 | 6 | 7 | 6.5 | 6.75 | 5 | 6 | 5.5 | 6 | 7 | 6.5 |
| 13 | 3 | 4 | 3.5 | 5 | 6 | 5.5 | 5 | 5 | 5 | 7 | 7 | 7 |
| 14 | 5 | 6 | 5.5 | 7 | 7.5 | 7.25 | 6 | 6.5 | 6.25 | 5 | 5.5 | 5.25 |
| 15 | 4 | 3.5 | 3.75 | 6 | 7 | 6.5 | 5 | 6 | 5.5 | 6 | 6 | 6 |
| 16 | 4.5 | 5.5 | 5 | 5.5 | 6 | 5.75 | 3.5 | 4 | 3.75 | 7.5 | 8 | 7.75 |
| 17 | 4.5 | 4 | 4.25 | 3.5 | 4 | 3.75 | 6 | 5.5 | 5.75 | 6 | 6.5 | 6.25 |
| 18 | 6.5 | 6.5 | 6.5 | 5 | 6 | 5.5 | 7 | 6 | 6.5 | 4 | 5 | 4.5 |
| 19 | 3.5 | 4.5 | 4 | 3 | 4 | 3.5 | 2 | 3 | 2.5 | 6 | 7 | 6.5 |
| 20 | 3 | 3 | 3 | 4,5 | 4 | 4.25 | 5 | 5.5 | 5.25 | 6.5 | 5 | 5.75 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | 5 | 6 | 5.5 | 5.5 | 6 | 5.75 | 3.5 | 4.5 | 4 | 6 | 6.5 | 6.25 |
| 22 | 4.5 | 5.5 | 5 | 3.5 | 4 | 3.75 | 6 | 7 | 6.5 | 4 | 5 | 4.5 |
| 23 | 4 | 5 | 4.5 | 2 | 3 | 2.5 | 4.5 | 4.5 | 4.5 | 6 | 5.5 | 5.75 |
| 24 | 5 | 6 | 5.5 | 6 | 5 | 5.5 | 7.5 | 6.5 | 7 | 4 | 5.5 | 4.75 |
| 25 | 5.5 | 6 | 5.5 | 3.5 | 4 | 3.75 | 5 | 6.5 | 5.75 | 4.5 | 3.5 | 4 |
| 26 | 4 | 3 | 3.5 | 5 | 4 | 4.5 | 5.5 | 4.5 | 5 | 3.5 | 3.5 | 3.5 |
| 27 | 2.5 | 3.5 | 3 | 4 | 3 | 3.5 | 2 | 3 | 2.5 | 2.5 | 3 | 2.75 |
| 28 | 4 | 2.5 | 3.25 | 3 | 3.5 | 3.25 | 6 | 6 | 6 | 7.5 | 6.5 | 7 |
| 29 | 3 | 3 | 3 | 5 | 4 | 4.5 | 2 | 3 | 2.5 | 4 | 3 | 3.5 |
| 30 | 4.5 | 4 | 4.25 | 3.5 | 3.5 | 3.5 | 5 | 5 | 5 | 4.5 | 4 | 4.25 |
| 31 | 3.5 | 3 | 3.25 | 4.5 | 5 | 4.25 | 6.5 | 5 | 5.75 | 3 | 4 | 3.5 |
| 32 | 4.5 | 3.5 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3.5 | 2.5 | 3 | 4 | 5 | 4.5 |
| 33 | 3.5 | 4 | 3.75 | 4 | 5 | 4.5 | 3 | 4 | 3.5 | 3 | 2 | 2.5 |
| 34 | 4.5 | 4 | 4.25 | 5 | 6 | 5.5 | 4 | 5 | 4.5 | 5 | 5.5 | 5.25 |
| 35 | 4 | 5 | 4.5 | 7 | 7.5 | 7.25 | 7.5 | 8 | 7.75 | 6.5 | 7 | 6.75 |
| 36 | 4.5 | 3 | 3.75 | 4 | 3 | 3.5 | 5 | 6 | 5.5 | 4 | 5 | 4.5 |
| 37 | 2.5 | 3.5 | 3 | 5 | 5.5 | 5.25 | 6 | 5 | 5.5 | 7.5 | 6 | 6.75 |
| 38 | 8 | 7.5 | 7.75 | 4 | 4.5 | 4.25 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2.5 | 2.75 |
| 39 | 3.5 | 4 | 3.75 | 2.5 | 3 | 2.75 | 6.5 | 7 | 6.75 | 5 | 4 | 4.5 |
| 40 | 3 | 3.5 | 3.25 | 4.5 | 4 | 4.25 | 6.5 | 6 | 6.25 | 4 | 4.5 | 4.25 |

መግለጫ፡ አ.1 = አራሚ አንድ ፣ አ.2 = አራሚ ሁለት ፣ አ/ውጤት =አማካይ ውጤት

## ለ. የተጠኝ ተማሪዎች የስርአተ ነጥብ ማሟላት ጥያቄ (ፈተና) ውጤት

| ተ.ቁ | አዲስ ዘመን ት/ቤት | አላቦ ት/ቤት | አበባዬን ት/ቤት | ይፋግ ት/ቤት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 6 | 8 | 0 | 2 |
| 2 | 10 | 2 | 6 | 8 |
| 3 | 0 | 4 | 4 | 4 |
| 4 | 6 | 10 | 4 | 0 |
| 5 | 2 | 4 | 6 | 8 |
| 6 | 8 | 8 | 4 | 4 |
| 7 | 4 | 2 | 0 | 0 |
| 8 | 6 | 10 | 0 | 8 |
| 9 | 4 | 4 | 6 | 2 |
| 10 | 10 | 0 | 4 | 6 |
| 11 | 6 | 2 | 8 | 6 |
| 12 | 2 | 6 | 4 | 6 |
| 13 | 6 | 4 | 0 | 2 |
| 14 | 10 | 8 | 4 | 4 |
| 15 | 2 | 4 | 10 | 4 |
| 16 | 0 | 4 | 2 | 10 |
| 17 | 8 | 4 | 0 | 4 |
| 18 | 4 | 4 | 10 | 2 |
| 19 | 2 | 6 | 0 | 4 |
| 20 | 8 | 4 | 4 | 10 |
| 21 | 4 | 4 | 6 | 4 |
| 22 | 6 | 2 | 4 | 2 |
| 23 | 0 | 4 | 6 | 10 |
| 24 | 10 | 6 | 4 | 4 |
| 25 | 2 | 4 | 4 | 6 |
| 26 | 6 | 0 | 8 | 0 |
| 27 | 6 | 4 | 4 | 6 |
| 28 | 0 | 6 | 0 | 2 |
| 29 | 4 | 4 | 4 | 6 |
| 30 | 6 | 4 | 6 | 2 |
| 31 | 0 | 6 | 4 | 8 |
| 32 | 10 | 6 | 4 | 6 |
| 33 | 0 | 4 | 0 | 4 |
| 34 | 2 | 6 | 4 | 10 |
| 35 | 6 | 4 | 8 | 6 |
| 36 | 4 | 6 | 4 | 0 |
| 37 | 8 | 2 | 4 | 6 |
| 38 | 4 | 4 | 8 | 0 |
| 39 | 0 | 2 | 4 | 4 |

አባሪ አራት፡- የእጅ ጽሁፍ ተነባቢነት የሌላቸው



